## እንበሳሜ

«ልጆች መጀመርያ ጣሪያው ይጽዳ። ታዩታላችሁ? ውስጥ እሳት ሲነድበት ነበር ማለት ነው:: ቆርቆሮው በጢስ ጠቁሮ ጥቀርሻ ለብሷል» አለች ትሩፋት:: ከድልነሳ ጓደኞች ጋር የተከራየቻትን ትንሽ ቤት በማፅዳትና በማዘጋጀት ላይ ናቸው::

«ጣራ ላይ በምን ይወጣል?» አለ ድልነሳ «ትምህርት ከድል በኋላ» በሚለው የኢሕአፓ መሪ መፈክር መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ ማለት ይቻላል ተዘግቷዋል። ተማሪው ሁሉ ወደየቤተሰቡ ተበታትኗል። ራሔልና ድልነሳ እንበሳሜ ከትሩፋት ጋር ናቸው:: ራሔል አስራ አንደኛ- ድልነሳ ደግሞ አስረኛ ክፍል ደርሰው ነበር:: እንበሳሜ ከተማ እስከ ሰምንተኛ ክፍል ድረስ በመኖሩ ሌሎቹ እህቶቿ--- ብሩክታይት፣ ዛብሽና ኢያል እዚሁ እሷ ጋር ሆነው ይማራሉ::

«መሰላል እዚህ እጎረቤት ከነአባ አበጀ ቤት ተዋሱና አምጡ። አንድ ልጅ በመሰላሉ ጣራ ላይ ይውጣ:: ያን ታዩታላችሁ?» አለች ትሩፋት በጠቋሚ ጣቷ ወደ ጣራው እያመለከተቻቸው::

«አዎ አይቼዋለሁ:: ያን ትልቅ የተጋደመ ግንድ አይደል የምትይው?» አለ አንዱ የድልነሳ ጓደኛ::

«አዎ እሱን ነው:: በመሰላሉ የሚወጣው ልጅ እዚያ ከተጋደመው ግንድ ላይ ሲቆም ጣራው ይቀርበዋል። ጨርቅ በውሃና በሳሙና እየነከራችሁ እቀብሉት:: ቀጣዩ ሥራ እንዳትወድቁ ወራጅና ማገር እንጨቱን በአንድ እጅ በመያዝ በሌላኛው እጅ ደግሞ ቆርቆሮውን ማሸት ይሆናል» አለች ትሩፋት። የቤቷን የውስጥ ጣራ አንጋጣ እየተመለከተች::

«መስፍን ነይ አንቺ መሰላሉ ላይ ውጭ ከሁላችንም አንቺ ቀጠን ረዘም ትያለሽ» አለ ድልነሳ መዘፍዘፊያው ላይ ውሃና አሞ እየጨመረ መስፍን እንደ ተባለው የተነከረ ጨርቅ ይዞ መሰላል ላይ ወጣ። ከተጋደመው ግንድ ላይ ቆሞ የቆርቆሮውን ማገር በአንድ እጁ ጨብጦ በሌላኛዉ እጁ ጣራውን ማሸት ጀመረ። ድልነሳና ሌሎች ጓደኞቹ መሬት ላይ ሆነው ስለ ወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ያወራሉ፤ በስሜት--በእፍላ የወጣጥነት ግለት።

«እኔ የምለው ይሄ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚሉት መቼ ተቋቁሞ ነው ትምህርታችን የምንቀጥለው? ጊዜው እኮ እንደ ዋዛ እየሄደ ነው» አለ እንዷለም

«እውነቱን እኮ ነው እንዷለም:: ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ያልተቋቋመ እንደ ሆን እኛ ደንቁረን ልንቀር ማለት ነው? ያኔ ውስጥ ውስጡን ቅስቀሳ ሲደረግና ወረቀት ሲበተን





ሕዝባዊ መንግሥቱ ወዲያው የሚመሰረት ነበር የሚመስለው:: ተማሪው እስከ እሁን መቆየቱን ቢያውቅ ኖሮ ትምህርቱን አቋርጦ የትም አይበታተንም ነበር» አለ ዘርይሁን

«እኔን አንድ ጊዜ ሰሙኝማ አንድ የሚገርመኝና ያልገባኝን ጥያቄ ልጠይቃችሁ:: ይሄ ሕዝባዊ መንግሥት የሚሉት ነገር ከመጀመርያውም ምኑም አልገባኝም:: ለመሆኑ ሕዝብ በሙሉ መንግሥት ከሆነ ተገዥው ማን ሊሆን ነው?» አለ ዓለሙ የሚሉት ልጅ:: ሁሉም አንድ ላይ ሳቁ::

«የእውነቴን እኮ ነው:: ምን ያስቃችኋል?» ሲል ደግሞ የባሰውን ተሳሳቁ::

«ሕዝባዊ መንግሥት ማለት እንደ አፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት የሰሎሞናዊው ዘር ተብሎ የዘር ሐረግ እየተመዘዘ ሳይሆን ወይ ደግሞ እንደ ደርግ መንግሥት ሰልጣንን በመሳርያ ኃይልና በጉልበት መንጠቅ ሳይሆን በሕዝብ ፍላጎት የተመረጠ መንግሥት ማለት ነው:: ለይስሙላም ቢሆን ደርግ የቀበሌ ሥራ አመራሮችን ሕዝብ ሰብስቦ አስመርጦ እንደሚያስተዳድሩት ማለት ነው» አለ ዘመድኩን የሚባለው ልጅ አረጋ ብሎ::

«ለመሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ የሚሰበሰብ እንኳን እዳራሽ ሜዳስ ይገኛል?» ሌሎቹ አሁንም እንድ ላይ አውካኩ::

«አለማወቅ ያስቃል? አዋቂ ለመምሰል ነው እንጂ እርግጠኛ ነኝ እያንዳንድሽ የዚህ የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አመሰራረትና ዓላማ ምኑም አልገባሽም:: ፈተና ቢኖረው ኖሮ ሁልሽም ወዳቂ ነበርሽ!» አለ ዓለሙ ተናዶ::

«እውነቱን ነው ዓለሙ ምን ያስቃችኋል? ሰው ግልጽ ያልሆነለትን ሲጠይቅ የማወቅ ኢዮማሱን ለማስፋት ስለሆን ሊደነቅ ይገባዋል» አለ ዘመድኩን ሁሉም ጸጥ አሉ::

«ነገሩ እንዲህ ነው ዓለሙ» አለ ዘመድኩን:: «ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚኖርበት አካባቢ ወይም ቀበሌ ይሰባሰባል:: ከዚያም ይጠቅመኛል፤ በሀቅ ሰርቶ ያሳድገኛል፤ እኔን ሆኖ ጉዳዬን ያስፈጽምልኛል የሚለውን ተወካይ በማንም ተፅዕኖ ሳይሆን በራሱ ፍላጎት ይመርጥና ለወረዳ ይልካል:: በወረዳ ደረጃ የተመረጡት ደግሞ ተሰባስበው ከሁሉም ይበልጥ የተሻለ ይሰራል የሚሉትን ተወካይ መርጠው ለአውራጃ ይልካሉ:: ምርጫው እንደ ገና በአውራጃ ደረጃም ይካሄዳል:: ከየአውራጃው የተመረጡት ደግሞ ይሰባሰቡና በከፍለ ሀገር ደረጃ ምርጫ ያካሂዳሉ:: የከፍለ ሀገሮቹ ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ይሰባሰቡና የአገር አቀፉን ምርጫ ያካሂዳሉ:: በዚህ መልኩ ከሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች በሕዝብ ተመርጠው የመጡት ደግሞ በብቃቱና በችሎታው ተወዳድሮ አገሪቱን በሞላ ሊያስተዳድር የሚችል ጠንካራ ሰው ይመርጣሉ:: እንግዲህ ሕዝባዊ መንግሥት የሚያሰኘው በዘር ሐረግ እየቆጠሩ ወይም በመሳርያ ኃይል በጉልበት ስልጣን መያዝ ሳይሆን ከታች ከቀበሌ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ድረስ በሕዝብ ነፃ ፍላጎትና ምርጫ

የተመረጠ መንግሥት በመሆኑ ነው::» ዘመድኩን ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጠ:: ሁሉም በጽሞና ነበር ያዳመጡት:: መሰፍን እንኳ ጣራ ላይ ሆኖ አንድም ነገር አላመለጠውም:: ወጣቶቹ ስለ ሕዝባዊ መንግስት ትንሽ ፍንጭ ያገኙ መሰላቸው::

«ልጆች ሌላ ኢንፎርሜሽን ደግሞ ልንገራችሁ:: የወረዳው ተላላኪ ጆሮ መሆኑን ታውቃላችሁ? ጓደኛ መስሎ እንዳያጠምዳችሁ ተጠንቀቁ» አለ ድልነሳ:: የወሬው ርዕስ ተቀየረ::

«ለካ ለዚህ ነው! ሲያየን አኮ ዐይኑ ነው የሚቀላው::»

«የአንበሳሜን ወጣት በአንድ ላይ ጨርሶ ቢባል አኮ ከመጨረስ አይመለሰም» ጨመረ ዘርይሁን የሚሉት::

«አፉማ አፍ እንዳይመስላችሁ:: እንደ አባብ መንታ ምላሰ ነው ያለው:: ድንገት ካገኘህ እኮ ለፍልፎ ሊያስለፈልፍህ የማይቀባጥረው ነገር የለም» አለ ዓለሙ::

«ይህን የፈረደበት ገበሬ ሁሉ ቁም ስቅሉን ሲያሳየው እኮ ግፍ አይፈራም:: ለእሱ ቅቤና ዶሮ አንጠልጥሎ ያልመጣ ገበሬ ምንም ቢሆን አስተዳደር ገብቶ ጉዳዩን ማመልከት አይችልም:: አንዴት መሰላችሁ የሚያስቃያችው» አለ አንዷለም::

«ለምን ማስጠንቀቂያ አይሰጠውም» ጨመረ ወንድሙ::

ጣራውን የሚያጸዳው መሰፍን እላይ ሆኖ ጨርቅ እንዲቀይሩለት ቢወተውትም የሰማው አልነበረም።

«እናንተ ልጆች ወሬ መንዛታችሁንና ጉራ መቸርቸራችሁን አቁማችሁ እባካችሁ ጨርቁን ቀይሩልኝ» አለ መሰፍን:: ከጣራው አግዳሚ ግንድ ላይ ተንጠልጥሎ ቁልቁል እያያቸው:: ድምጹ አልተሰማም:: በእነሱ ጩኸት ተውጦ ቀረ::

«ድሌ፣ ዘሬ፣ አንዱዬ... ኧረ እባካችሁ በፈጠራችሁ አዳምጡኝ!» የሰማው የለም:: የፖለቲካው ወሬ ጆሯቸውን ደፍኖታል::

«ወይ በምድር ያለ ሰው!» አለ ተማሮ:: እባባሉ ትሩፋትን ከልቧ አሳቃት::

«ድሌ ምን እየሰራችሁ ነው? ጨርቁን ውሀ ንከሩና ቀይሩለት እንጂ ደግሞስ እንዲህ በየሜዳው ነው እንዴ አፋችሁ እንዳመጣላችሁ የምትቀባጥሩት? መንጋ ቀባጣሪ ሁሉ! ከወረዳው ተላላኪ ጥግ ከመድረሳችሁ በፊት እኔ እዚሁ እንዳላሳፍሳችሁ!» አለቻቸው ትሩፋት ቆጣ ብላ። ሁሉም ፀጥ አሉ:: ትክክል እንዳልሆኑ ገብቷቸዋል:: «በመንገድ አላፊ





አግዳሚው ሰው ሁሉ ሲሰማ ይችላል:: የተባለው ነገር ከወረዳው ተላላኪ ጆሮ ከደረሰ ደግሞ የሚያስከትለው መዘዝ ቀላል አይሆንም:: ትምህርት ቤት ተከፍቶ እስኪሄዱ ድረስ አደብ ገዝተው መቀመጥ ይኖርባችዋል:: ወጣቶቹ ወደ ስራው አተኮሩ::» አለች ተቆጥታ ያችን አንዲት ከፍል ቤት ሦስት መልክ አስይዘዉ ሳሎን፣ ዕቃ ቤትና መኝታ ቤት አድርገው አዘጋጁት:: ::

ቤቷ ለዋና ቤቱ መኝታ ቤት ተብላ የተዘጋጀች ነበረች። በሰተኋላ በር አውጥተው ለኪራይ አውለዋታል። ደርግ የቤት አከራይንና ተከራይን ግንኙነት በአዋጅ ቢሽርም ሕብረተሰቡ በውስጥ ለውስጥ ለምምነት ያከራያል--ይከራያል:: የቤቷ አከራይ በይፋ የሚናገሩት ለትሩፋት ዘመዷ እንደ ሆኑና ለጊዜያዊ ማረፊያነት ከፍሏን እንደ ሰጧት ነው:: የኪራዩ ርክክብ የሚፈጸመው ማንም ሳያውቅ በከፍተኛ ምሥጢር ተጠብቆ ነው::

ይቺው አንዲት ከፍል ቤት ሰባት ሰው እንዴት ይኖርባታል ቀንኑስ እንደ ነገሩ ይዋላል አለች:: የአዳሩ ነገር ሲታሰበው ትሩፋት የበለጠ ጨነቃት:: በኋላ ባወጣችው ድልድል ድልነሳ ከጓደኞች ጋር ሆነው፣ ሰራተኛዋ ከቤቷ ባለቤት ጋር፣ ብሩክታይት፤ ዛብሽና እያል ቀኑን ውጭ በሚውል ፍራሽ ማታ አስገብተው ወለል ላይ ዘርግተው ተኙ:: ትሩፋትና ራሔል አዳራቸው ዘጠና ሴንቲሜትር ሰፋት ባለው በባለ አግሩ የሸቦ አልጋ ላይ ሆነ ::

አንበሳሜ የሳር ጎጆ የሚበዛባት ትንሽ የገጠር ከተማ ናት። የገጠር ቀበሌ ብትባል ይቀርባታል። ቤቶቿ የገበያውን ጥግ ጥግ ከበው የተሰሩ ናቸው። የገበያው ቦታ ሰፊ ነው:: ከአካባቢው ገበሬ ማህበር የሚመጣውን ገቢያተኛ ሁሉ ከትት አድርጎ ይይዛል:: ገበያው መሀል አንድ ትልቅ ዋርካ አለ:: ብዙ ጊዜ ቅቤ የያዙ ሴት ገበሬዎች ዙሪያውን ከበው የቅቤ ሽያጭ ያከናውኑበታል:: ገልዳ የሚባለዉ ትልቅ ወንዝ ባለቤትም ናት አንበሳሜ:: የገልዳ ወንዝ ባይኖር ኖሮ ምናልባት ከተማዋ ላትቆረቆር ትችል ነበር:: ልክ እንደ አዲስ ዘመን ከተማና ሸኒ ወንዝ::

ትሩፋት ከሁመራ ተዘዋውራ አንበሳሜ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመድባ በመስራት ላይ ትገኛለች:: አንበሳሜን ከሁመራ ጋር ስታወዳድር ከብርሀን ወደ ጨለማ እንደ መግባት ነበር የቆጠረችው። የመጀመሪያ የሥራ ቦታዋ ሱዳን ገዳሪፍ ጥግ የምትገኘዋ ሁመራ በስንት ጣዕሟ! ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግሥት ሰራተኛ ሆና ሁመራ ተመድባ የሄደችው በአይሮፕላን ነበር:: ከሁለት ዓመት አገልግሎት በኋላ ወደ አንበሳሜ ተዘዋውራ ስትመጣ ግን የእግር ጉዞ ነው ያጋጠማት:: ከሐሙሲት ተነስታ የሦስት ሰዓት መንገድ በእግሯ መኳተን ነበረባት:: አምደጽዮን ባይመጣ-- የቄሶችን ማንነትና የፖለቲካ ተልዕኮ ባታውቅ ኖሮ ሁመራን ለቃ እንኳን አንበሳሜ መሀል ጎንደር ከተማ እንኳ የመግባት ሐሳብ አልነበራትም::

በዚች ትንሽ የገጠር ከተማ የደርግ ወታደራዊ መንግሥት የሚጠራው የማያቋርጥ ስብሰባ ደግሞ ይበልጥ ሁመራን እንድትናፍቅ ያደርጋታል፡፡ ሁመራ እያለች የመንግሥት ስብሰባ ብሎ ነገር አይታወቅም ነበር፡፡ አንበሳሜ ግን ስብሰባው ያሰለቻል፡፡ በተለይ በየሳምንቱ አርብ አርብ ምንም ቢሆን የማይቀር አጠቃላይ የመንግሥት ሰራተኞች የውይይት መድረክ የሚሉት ስብሰባ ይካሄዳል፡፡ በትምህርት ቤቱ ግቢ በአንደኛው ክፍል ውስጥ ነው ስብሰባው፡፡ ትምህርት ቤቱን ኢሰቡ የተባለ የውጭ እርዳታ የሰራው በመሆኑ በመጠኑም ቢሆን የተሻሉ ወንበሮችና ዴስኮች አሉት፡፡ የወረዳ አስተዳደሩ ጽሕፈት ቤትም ሆነ ፖሊስ ጣቢያው ያሏቸው ክፍሎች ከስም በስተቀር ከከተማው ጎስቋላ ቤቶች በምንም አይሻሉም፡፡ ሁሉንም የመንግስት ሰራተኛ ሊይዝ የሚችለው ይኸው የትምህርት ቤቱ ክፍል ነው፡፡ አሉተ አርብ ከቀኑ 10:30 ሲሆን ስብሰባው ይጀመራል፡፡ ትሩፋት ገና ስብሳቢው ሳይገቡ ድካምና ማዛጋት ይጀምራታል፡፡ ስልችት እንዳላት እንዱንም ሳትሰማው ውይይቱ ያልቃል፡፡

«እኔና እንቺ ብንጋባ የምንወልዳቸው ቆንጆ ቆንጆ ልጆች አይታዩሽም ትሩፋት?» አለ ደሳለኝ። እንደ ተለመደው እንድ አርብ ቀን ለአጠቃላዩ ስብሰባ ከጎኗ እየተቀመጠ። ስምን መላዕክ ያወጣዋል እንዲሉ ደሳለኝ ሁሌ ደስ ያለው ይመስላል። ሁለመናው ይስቃል። ዘመኑ አንኳን ማላቅ ፈገግ የሚያሰኝ አልነበረም። ዘመነ ለውጥ–ዘመነ ነውጥ፡፡

«ሲታስተምርም እንዲህ እየሳቅህ ከሆነ እርግጠኛ ነኝ ተማሪዎቹ 'መምህር ሳቅ' ወይም 'መምህር ጥርስ ' ብለው ነው ቅጽል ስም የሚያወጡልህ። ተማሪ አንኳን ትንሽ ሰበብ አግኝቶ እንዲሁ ቅፅል ስም ለማውጣት አይቸገርም፡፡ እኔ እንኳን ሳይህ ጥርስህ ተከድኖ ያየሁበት ቀን ትዝ አይለኝም» ትሰዋለች ትሩፋት ደሳለኝን፡፡ የማይነጥፈው የሳቁ ምንጭ እየገረማት።

«ሳቅ የውስጣችን ቁስል መፈወሻ መድሀኒት ነው። ሳቅ ባይኖር ኖሮ ውስጣችን ቆስሎ ገምተን---ሸተን እንሞት ነበር፡፡ ኢታይም በቆሎ እንኳን ሲቆላ ወይ ሲጠበስ ሲያር ነው እየተንጣጣ የሚስቀው፡፡ ለምን ይመስልሻል? የውስጡን ሕመምና ስቃይ ለማስታገስ እኮ ነው» ይሏታል እሱም ሁልጊዜ። ዛሬ ደግሞ ከጎኗ ተቀምጦ በወሬ ጠምዷታል፡፡

«ልጅ በልጅነት ነው የሚያምረው፡፡ ብንጋባ.....» አቋረጠችው ትሩፋት፡፡

«ቆይ ግን አንተ--- አገባለሁ ስል ሰምተህ ታውቃለህ?»

«መቼም ቆመሽ አትቀሪ።»

«ማግባት የግድ ነው ያለህ ማን ነው?»

«ነጋሪ ባይኖረኝም ግድ እንደሆነ ግን አውቃለሁ።»





«በቃ አላገባም! ሳላገባ የሚሆነውን እያለሁ እኔ ደግሞ፡፡»

«ዋልድባ ሴቶች ገዳም ልትገቢ ወይም መንነሽ ዋሻ ልትዘጊ አስበሽ ከሆነ፡፡»

«እዚሁ ዐይንህ እያየ ሳላጋባ እኖራለሁ፡፡ የምን ዋልድባ! የምን ዋሻ መዝጋት!»

«መንኩሰሽ ቆብ ልትጭኝ ከሆነም ይቻላል፡፡»

«ሳላገባ እኖራለሁ ካልኩ አስገድዶ እንዳገባ የሚያደርገኝን ሕግ አስቲ አያለሁ!»

«እይ ትሩፋት! የዋህ ነሽ ለካ! አየሽ የሚያስገድድሽ ሕገመንግስት ላይ ወይም ፍተሃነገስት ላይ የሰፈረ ሕግ ብቻ አይደለም።»

«ደላለኝ ይልቅስ ሌላ የሚጥም ወሬ ብታመጣ ምን አለበት፡፡ የጋብቻን ነገር ለጊዜው አርሳው፡፡

«የሕይወታችን እንድ አካል እኮ ነው ትሩፌ! ያውም ቁጥር አንድ! እንዴት እረሳዋለሁ? አዳም ብቻውን በዚች ዓለም ላይ መኖር እንደማይችል አውቆለት እኮ ነው ፈጣሪ ሔዋንን የሰጠው፡፡ ደግሞ እደራሽን ከባድ ምሥጢር ነው የነገርኩሽ፡፡ የሶሻሊስት ካድሬዎች የፈጣሪ ስም ሲነሳ የተጠናወታቸው ሰይጣን ይቆጣል፡፡ ታስበይኛለሽ፡፡» አሳት ወደ ጆሮዋ ተጠግቶ እያንሾካሾከና እካባቢውን ገልመጥ ብሎ እየተመለከተ፡፡ የስብሰባ ሰዓቱ ገና ነው፡፡ የመጣው ተሰብሳቢ ሁሉ በየግል ወሬው ተጠምዷል፡፡

«የአንተ የራስህስ አቋም ምኑ ይታወቃል?» ልትለው አሰባ ከአፏ መለሰችው፡፡ «በቃ ተወኝ! እኔ ምንም ምሥጢር መስማት አልፈልግም» አለች ትሩፋት ተሰላችታ፡፡

«እኔ ብተውሽ የምትኖሪበት ማህበረሰብ ወግ፣ ልማድና ባሕል መቼ ይተውሻል፡፡ ማኅበረሰቡ ሳይጻፍ እንዲሁ በዘ-ልማድ የሚስማማበት ሕገ-ደንብ አለው። በዚያ ማኅበረ ሰብ ውስጥ የሚኖር ሰው ሁሉ ወዶም ይሁን ሳይወድ--አውቆም ይሁን ሳያውቅ ላልተጻፈው የልማድ ሕግ ተገዥ ይሆናል፡፡ ከማህበረሰቡ የልማድ ሕግ ውጭ ከሆንሽ ግን እንደ ነውረኛ ትቆጠሪያለሽ ወይም እንደ አፈንጋጭ፡፡»

«የግድ ካላገባሁ እንደ ነውረኛ የሚቆጥረኝ ካለ ነገሩ ሲገባው ይተወዋል አታስብ፡፡»

«አ! ያማ ብ---ዙ ጊዜ ይወስዳል፡፡ ገና የባህል አብዮት ተካሂዶ የባህል ለውጥ እስኪመጣ ድረስ፡፡ አሁን ባለው የአገራችን ሁኔታ ውስጥ እየኖርሽ ካላገባሽ ግን ችግር ይገጥምሻል፡፡ ለኅብረተሰቡ የሚጠቅም ሥራ ብትሰሪ እንኳን ከቁም ነገር የሚቆጥርልሽ አይኖርም፡፡

ጠቃሚ ሐሳብ ብታቀርቢ ሰሚ አታገኝም፡፡ ቁም ነገር እንደ ሌለሽ ተቆጥረሽ የማንም መሳቂያና መሳለቂያ ሆነሽ መዘባበቻ ተደርገሽ ትቀሪያለሽ። ልክ እንደ ጉዱ ካሳ፡፡»

«ይህን ሁሉ ማብራሪያ የምትሰጠኝ አንዳገባ ከሆነ እርምህን አውጣ ደሳለኝ አላገባም! እኔ ሳልፈልግ ተወልጄ ሳይደላኝ በምኖርባት ዓለም ላይ ሌሎች ፍጡራንን አምጥቼ አላሰቃይም፡፡ ሳይፈልጉ ተወልደው ሳይመቻቸውና ሳይደላቸው እንዲኖሩ አልፈርድባቸውም። ለዚያውም ገና ምኑም ምኗም ባለየላት በዚች አገር ሁሉም ነገር እያላት ሁሉንም ነገር ባጣች አገር፡፡

«የሚገርመው ግን እንዲህ ያፈጠጠ ችግር ውስጥ እየተኖረ እንኳን ማኅበረሰቡ ያልተጻፈውን ሕግና ደንብ ማክበሩን ቀጥሏል፡፡ ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጆቹን ይድራል፤ ይኩላል፡፡ በጎስቋላ ኑሮ ውስጥ እየተኖረም ይወለዳል ይከብዳል፡፡»

«ካለማወቅ ነው ደሳለኝ ይግባህ፡፡ በእድሉ ያድጋል ከሚል የዋህ አስተሳሰብ፡፡»

«ማኅበረሰቡ ያልቸገረውን ያንኑ ያልተጻፈ ሕግ መነሻ በማድረግ ወላጆቿን ወግ ማዕረግ ያላሳየች— ቆሞ ቀር—ወልዳ ያልሳመች—እንደ በቅሎ ዘሯን ያልተካች...... ኧረ ስንቱ በሄድሽበት ሁሉ መጠቋቆሚያ ያደርግሻል፡፡ መቆሚያ መቀመጫ ያሳጣሻል ትሩፌ» አላት ደሳለኝ ዐይን ዐይኗን እያየ፡፡

«ሁሉም አውርቶ — አውርቶ ሲበቃዉ አርፎ ይቀመጣል፡፡ ምን ያመጣል?»

«የስነ-ልቦና ጉዳቱስ? ፍቅር እስከመቃብርን አላነበብሽም እንዴ? አስቲ የሰብለወንጌልን አበላ አስታውሺ፡፡ ምንም ላይቸግራት ትዳር የመያዣ ጊዜዋ ስላለፈ ብቻ ነበር ማህበረሰቡን ተሳቃ አንገቷን ደፍታ እንድትኖር የተገደደችው፡፡ አንቺ መቼም እንደ ሰብለወንጌል ተሳቀሽ መኖር አትፈልጊም፡፡ ምን በወጣሽ? ለዚያውም እኔን የመሰለ ሸበላ እየተለማመጠሽ፡፡»

«አንተን ይሉ ሸበላ! ራስህን እንዴት ነው የምትወደው እባክህ? ግን ይግባህ ጉዱ ካሳም ሆነ ሰብለወንጌል የልብ ወለድ ፍጡራን ናቸው፡፡ በእውኑ ዓለም ያሉ እውነተኛ ሰዎች ኢታስመስላቸው፡፡»

«ሰብሳቢው ሳይገቡ በተለይ አናዳጁን ነገር ልንገርሽ ይልቅስ፡፡ አኩያሽ ያልሆነ ወንድ ሁሉ-- ወንድ ስለሆነ ብቻ መብቱ መስሎት ከመሬት እየተነሳ ይጠይቅሻል። ሸንበራ አሸትን አይቶ ማን ያልፋል? እንቡጥ ጽጌሬዳን አይቶ ቀጥፎ ለማሽተት የማይመኝ ማን ወንድ ይኖራል? ሁሉም እንዳሻው እየተነሳ ሲመኝሽ ደግሞ ሰው ነሽና መናደድሽ አይቀርም፡፡ ከዚህ ሁሉ ብን.....» ሐሳቡን ሳያጠቃልል ድንገት ከፍሉን ጸጥታ ዋጠው። በግል የነበረው ወሬ ሁሉ ፀጥ- ረጭ አለ። ዐይኖች ሁሉ ወደ መድረኩ ተወረወሩ።





«ጓዶች እንደ ምን ዋላችሁ?» አለ ሰብሳቢው ሁሉም አድምተኛ መገኘቱን ለማረጋገጥ ከፍሉን ከጥግ እስከ ጥግ እየተመለከተ፡፡

«የዛሬው የአብዮታዊ ንቃት ውይይታችን ርዕስ አብዮታችን ሰለ አስገኛቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ድሎች ይሆናል» ሲል ነጎድጓዳዊ ድምጹ ቤቱን ሞላው። ጉንጩ ተንጠልጥሎ ሊወድቅ የደረሰ ይመስላል፡፡ ጥይም ፊቱ በወዝ ተንጨፍጭፏል። በተናገረ ቁጥር አጁ ሲወናጭፍ ከለበሰው ሙሉ ሰማያዊ ልብስ በላይ የደረበው ጥቁር የቆዳ ጃኬት ከፈት ከፈት ሲል ጎኑ ላይ የሻጠው ፊሎቨር ሽጉጥ አሁንም አሁንም ይታያል። ያበጠ ትከሻው ለውን ሁሉ ቁልቁል ይሜናል። ሲናገር ፊት ለፊት ላለመገኘት ሰው ሁሉ ይሸሻል። እወደድ ባይ ብቻ ነው ላብ ያስቸገረው ይመስል ፊቱን በመሃረብ እስሬ እየጠረገ ቅርቡ የሚቀመጠው፡፡ "ዝናቡ" ይሉታል ሳይሰማ፡፡

የመንግሥት ሰራተኞች በሙሉ የሁለት ሰዓት ንቃት የሚወስድባት እለተ አርብ። አብዮቱ በሳላቸው ---ሰል ካድሬዎች ንቃቱ ከላይ ወደታች ያለማቋረጥ ይፈሳል። ሁሉም ተሰብሳቢ ዐይኑን ሳያራግብ መድረኩ ላይ ያፈጣል። ሁሉም ትንፍሽ ሳይል በንቃት የሚከታተል ይመስል እንጂ ሁሉም የሚያዳምጠው ግን የውስጥ ሐሳቡን ነው፡፡ ሁሉም ከራሱ ጋር ይወያያል፡፡

በር በቀስታ ተንኳኳ። «ይግቡ» አለ ሰብሳቢው አርፍዶ የመጣውን ደፋር ለማየት የቀሉ ትናንሽ ዐይኖቹን በሩ ላይ ስክቶ። ሰብሳቢው ብቻ ሳይሆን የሁሉም ታዳሚ ዐይኖች ወደ በሩ ተወረወሩ። አፍሮ ጸጉሩ ብን ብሎ የተበጠረ-- ረዘም ያለ አረንጓዴ ፊልድ ጃኬት ነጣ ካለ ጅንስ ጋር የለበሰ ወጣት ብቅ አለ። ሰፊ ትከሻውና ረጅም ወንዳወንድ ቁመናው በሩን ሞላው። ትሩፋት ልቧ ድንግጥ ያለ መሰላት።

«ሌላ ቦታ አይቼው ይሆን?» ለማስታወስ ሞከረች፡፡ እንግዳው ሰው ቀጥታ ወደ መድረከ ሄዶ ለሰብሳቢው የሆነ ደብዳቤ አሳየ። በሹክሹክታ ከተነጋገሩ በኋላ ባዶ ቦታ ላይ ሄዶ ተቀመጠ። ለትሩፋት ተቀምጦም ከሁሉም በላይ ጉብ ብሎ ታያት። ቶሎ ብላ ዐይኗን መለሰች።

«አንዴ ምን ሆኛለሁ!? ምን ነካኝ!» አለች በውስጧ፡፡ ስብሰባው የቀድሞ መልኩን ያዘ።

«ጓድ አብዮታዊ መሪያችን የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር፣ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አዛዥ.....» የስልጣን መዓት ደረደረ ሰብሳቢው፡፡

«አስመሳይ--አድርባይ ሁሉ!» አለች ትሩፋት ለራሷ፡፡ የልብን የሚያውቅ አለመኖሩ በጀት፡፡ አስመሳይና አድርባይ ሰው ስትጠላ ልክ የላትም፡፡ ከሰውነት በታች ወርዶ እንስሳ የመሆን ያህል ትቆጥረዋለች፡፡ የዚህ ሰብሳቢ ባዶ አስመሳይነትም አስጠላት፡፡ አልሰበሰብም የማለት

መብት ቢኖራት ኖሮ ብቅ ባላለችም ነበር፡፡ ግን ሳትፈልግ ተሰብሰባለች፡፡ ሳትፈልግ ታዳምጣለች፡፡ የሰዓቱን ማለቂያ ጊዜ እየቆጠረች፡፡

«ሀቀኛውና ቆራጡ አብዮታዊ መሪያችን እንዳሉት በፖለቲካው መስክ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግረናል። ይህ ድል የተገኘው እንዲሁ አይደለም። በቆራጡ መሪያችን ብስለትና አስተዋይነት ቆራጥ አመራር ነው። በፖለቲካው ያገኘነውን ድል በኢኮኖሚው መስክ ደግሞ መድገም ይኖርብናል። ለአረንጓዴው ዘመቻ ከወዲሁ ቆርጠን መነሳት አብዮታዊ ግዴታችን ነው፡፡ ዘውድ ናፋቂው ኢዲዩ---የኤርትራና የትግራይ ተገንጣይ ወንበዴዎችና ጠባብ ብሔርተኞች---አናርኪስቱ ኢሕአፓና ሌሎች ያልጠቀስናቸው የውስጥና የውጭ የአብዮታችንና የሰፊው ሕዝብ ጠላቶች በተባበረ የሕዝብ ክንድ ይደቆሳሉ! የፖለቲካውን ድል ያጎናጸፈን አብዮታችን በልማቱ መስክ በአረንጓዴው ዘመቻ ይደገማል! ለዚህም ያላሰለሰ ጥረት ከጓዶች ይጠበቃል። ዘር ከልጓም ይስባል እንዲሉ ፀረ-አብዮተኛ ሁሉ የመደብ ጀርባው እየሳበው አብዮቱን ለመቀልበስ የማይፈንቅሉት ድንጋይ--የማይፈጥሩት አሻጥር የለም። በፖለቲካው መስክ ከሸፍብቸዋል፡፡ ኢኮኖሚውን ለማሽመድመድና የአረንጓዴውን ዘመቻ ዕቅዳችን ለማሰናከል መሞከራቸው አይቀርም። ስለዚህ ነቅቶ መጠበቅ የሁሉም አብዮተኛ ዜጋ ግዴታ ነው። አገራችን ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ የዳቦ ቅርጫት እናደርጋታለን!...»

ንግግሩና መፈክሩ ያለማቋረጥ ከመድረከ ይዥጎደጎዳል። ከደርግ በስተቀር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም ድርጅቶች ፀረ-አብዮት ናቸው። ከደርግ በስተቀር ሁሉም ፀረ-ዲሞክራሲ ናቸው። ደርግ ባይኖር ኖሮ በአሁኑ ጊዜ ይቺ አገር ብትንትኗ ይወጣ ነበር፡፡ ለዚች አገር ህልውና እንዲሁም ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና ከደርግ መንግሥት በስተቀር የሚበጃት አንድም ድርጅት አልተፈጠረም። አይፈጠርምም፡፡ ራሳቸው ለራሳቸዉ መሰከሩ። ጠያቂ በሌለበት ለጥያቄዎች ሁሉ መልስ ሰጡ። ታዳሚ ሁሉ በተቀመጠበት ሳይንቀሳቀስ ህውልት መስሎ ጸጥ ረጭ ብሎ ያዳምጣል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ጊዜም እንዲሁ ነው የሚሆነው፡፡ መሳሪያ አንግቦ በትረ-ስልጣኑን ይዞ ቤተመንግሥት የገባ ሁሉ ፍጹም ነው፡፡ ራሱ ለራሱ መስካሪና ብይን ሰጭ ነው፡፡ መሳሪያ ሁሉንም ያደርጋል፡፡ ሳይማሩ ሳይንቲስት--- ዶክተር--- መሀንዲስ--- ዳኛ--- ኮሎኔል---ጀኔራል---ሜጀር ጀኔራል... ያደርጋል፡፡ መሳርያ ችሎታውና አቅሙ ሳይኖር የትልቅ አገርና የትልቅ ሕዝብ ገዥ እንዲሆኑ ሁሉ ያደርጋል፡፡ የውይይቱ ጊዜ ሁለት ሰዓት ቢሆንም የአካባቢ ትንንሽ ባለስልጣናት ደግሞ ቢያንስ ግማሽ ሰዓት ይጨምራሉ፡፡ ሰብሳቢው መፈክር አስምቶ ስብሰባው መጠናቀቁን አበስሮ ቀድሞ ወጣ፡፡ ትሩፋት ከባድ ሸክም የወረደላት ያህል በረጅሙ ተንፍሳ ወደ ቤቷ ለመሄድ ተነሳች፡፡

«ቆይ ቀስ ብለን እንወጣለን ምን ያስቸኩልሻል?» ብሎ እጇን ይዞ ወደ ኋላ ጎተት አደረጋት ደሳለኝ።





«መሽቷል፡፡ መብራት በሌለበት አገር በጊዜ መግባት ነው የሚያዋጣው» አለች ትሩፋት እጇን እያስለቀቀችው፡፡

«ቅድም የጀመርነውን የትዳር ጉዳይ አልቋጨነውም እኮ!» አሉ የምር አድርጎታል፡፡

«እውነቱን መስማት ትፈልጋለህ ደሳለኝ? የማገባም ቢሆን እንኳ ግዴታ አንተን መሆን የለበትም» አለችው ፈርጠም ብላ፡፡ ፈጠን ፈጠን ብላ እየተራመደች፡፡

«ምን ይወጣልኛል እባከሽ!? ኧረ ለመሆኑ የአንቺ ባል ለመሆን ምን ያንሰኛል!?» አለ ፊት ለፊቷ ተጋርጦ፡፡

«ልጅ አትሁን ደሳለኝ፡፡ ትልልቆች ነን!» አለች ትሩፋት፡፡ በተቆጣ ዐይኗ እየገረፈችው፡፡ ደሳለኝ ከፊቷ ገለል አለ፡፡

«ለትዳር ዋናው መሰረት ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ፍቅር ነው። የልብ የሆነ የጋራ ፍቅር! ያለፍቅር ትዳር--- ትዳር ሳይሆን ደባልነት ነው። ይህንን ስትል ፍቅሩ በአንደኛው የአዕምሮዋ ጓዳ ሲንጎዳጎድ ሰማችው፡፡

«እየተቀራረብን ስንሄድ አንቺም ታፈቅሪኝ ይሆናል። የመቀራረብ እድሉን አትንፈጊኝ አባክሽ ትሩፋት» አላት በልምምጥ፡፡

«ከተቀራረብን ቆየን እኮ። ከአንድ ትምህርት ቤት አብሮ ከመስራት በላይ መቀራረብ አለ እንዴ ደሳለኝ? እኔና አንተ ከዚህ በላይ ልንቀራረብ አንችልም፡፡» ስትለው ቀድሞ ከሚገኘው ከእሱ መኖሪያ ቤት ደርሰው ነበር፡፡

«እቤትሽ ድረስ ልሸኝሽ ባይሆን፡፡» ብሎ ሊከታላት ሲል

«ኧረ በሕግ አምላክ! የአንበሳሜ ቤት ደግሞ የቱን ያህል ተራርቆ ነው ሸኚ የሚያስፈልገኝ? ይልቅስ ደህና እደር» ብላው እየተቻኮለች ሄደች። ከዐይኑ እስከተሰወር ድረስ እንደ ቆመ ነበር። እሷ ወደ ቤቷ ስትገሰግስ ልቧ በበኩሉ ፍቅሩን ፍለጋ አስመራ ከተማን እያሰሰች ነበር። በማታውቃት ምጽዋ ከተማ ገብታ በፍለጋ እየባከነች።

«እውነት ፍቅሩ በሕይወት እያለ ይህን ያህል ጊዜ በእኔ አስችሎት ይቀመጣል? ሦስት ዓመት ሙሉ እዚህ ነኝ ሳይለኝ? ዝም ብሎ እልም--- ጥፍት ይባላል!? ብቻ ደህና በሆነ። አስችሎት ልቡ ከቆረጠለት ይሁንለት፡፡ ሌላም አፍቅሮ ከሆነ ያዝልቅለት፡፡ እንደ እኔ በአደራ ቃል የተቆለፈ ልብ ሳይሆን ለፍቅር የተከፈተ ልብ ያጋጥመው» አለች፡፡ ጥሩ አፍቃሪ ሴት እንዲገጥመውና መልካም ሕይወት እንዲኖር እየተመኘችለት፡፡

አብናት በታች አይሃ ማርያም በምትባል ገጠር ውስጥ በችጋር እየማቀቁ ስለሚኖሩት ቤተሰቦቿ የነገራት ሁሉ በልቧ ስር ሰቅጽበት ሽው ብሎ አለፈ:: ደግሞ ሌላ ሐሳብ በእዕምሮዋ መጥቶ ስንቅር አሰባት:: ተረበሸች። በሕይወት መኖሩ እጠራጠራት:: ሞቱን በፍጹም ማሰብ እትፈልግም:: በደለኘነት ይሰማታል ግን አይለቃትም።

«አኔን ብሎ--- አኔን ተከትሎ--- አሰመራ ባይመጣ ኖሮ---ባህር ኃይል ባይቀጠር ኖሮ.....» የባሕር ላይ ጦርነቶችን ራሷ ፈጥራ እዚያ ላይ--- በጥይት ሲመታ---ባህሩ ላይ ሲወድቅ--- ባህሩ በደም ሲበከል--- በልብወለድ መጽሐፍ ውስጥ እንዳነበበችው ሻርክ በባህሩ ውሰጥ ለውስጥ መጥቶ ሲበላው--- ዝግንን ይላታል። ወንጀለኛነት ይሰማታል። ፍቅሩን ባሰታወሰች ቁጥር የነዚያ ሚስኪን ቤተሰቦቹ ኑሮ ይታያታል:: ልቧ ቁስ–ል ትሳለች::

******

አንድ ቀን ጠዋት ከመኝታዋ ስትነሳ ጤንነት እልተሰማትም:: ሰውነቷን ይቀረጣጥፋታል:: ትኩሳት እላት:: ብርድ ብርድ ይላታል:: እንዲህ አይነት ስሜት የሚሰማው ወባ ስትይዝ እንደ ሆነ ሰምታለች:: ለማንኛውም ብላ ሐኪም ፍሰሃን ለማማከር ጤና ጣቢያ ማምራቷን ተያያዘችው::

«ትሩፋት-- የት እየሄድሽ ነው?» የሚል ድምጽ ሰምታ ዘወር አለች። በብስክሌት ላይ ነው።

«ጤና ጣቢያ::»

«ምነው አመመሽ እንዴ?»

«ትንሽ ትኩሳት ቢጤ ሲሰማኝ ጊዜ ወባ እንዳይሆን ሰግቼ ነው እንጂ ኧረ ደህና ነኝ!» አለች ቀለል አድርጋ።

«በብስክሌቷ ላድርስሽ?»

«ኧረ አያስፈልግም! ይሄ አይደል ጤና ጣቢያው» እለች በእገጯ ጭምር እያመለከተችው። ለራሷ ደግሞ «ታየኝ እኮ በአንበሳሜ ከተማ በብስክሌት ካንተ ጋር ስፈናጠጥ!» እለች። ከይነበብ ታሪኩ ጋር ትውውቃቸው በመንግስት ሰራተኝነታቸው ብቻ አይደለም። ሁለቱም በሕቡዕ የሚንቀሳቀሰው የአንበሳሜ ከተማ የኢሕአፓ የህዋስ እባል በመሆናቸው ጭምር እንጂ። ለአንበሳሜ ከተማና ለአካባቢዋ እንደ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ ከሚያገለግለው ቡድን ውስጥ አብረው ይሰራሉ። ይነበብ የግብርና መስሪያ ቤት የገበሬዎች አደራጅ ሰራተኛ ሆኖ የመጣው ለሽፋን ነው። ዋና ተልዕኮውና ተግባሩ በደራ ወረዳና በፎገራ ወረዳ በሚገኙ የገበሬ ቀበሌ ማህበራት ውስጥ የኢህአፓን መዋቅር መዘርጋትና ማጠናከር ነው::





«ስራ የለም እንዴ። በዚህ ሰዓት እንዴት ተገኘህ?» ጠየቀች ትሩፋት:: አብረው መታየታቸውን እየጠላች::

«ለመስክ ሥራ ልወጣ ነው::»

«ታድያ አይረፍድብህም? ሰዓቱ ሳይገፋና ፀሐይ ሳትበረታ መሄዱ አይሻልህም?»

«ነገ ጧት ነው የምወጣው። በታውም ሩቅ አይደለም:: አርባተንሳ ቀበሌ ገብሬ ማኀበር ነው» አላት:: የአርባተንሳ ቀበሌ ገበሬ ማኀበር በተነሳች ቁጥር በእበት እምራ የተለቀለቀችው የአያቷ ሳር ቤት፣ ዳሮ ያለችው የአቤ ዛፍና የአጫውቲት ምንጭ ትዝታ መቼም አይቀሩም:: ወድያው ዐይኗ ሥር ድቅን ይሉባታል::

«እግዜር ገነትን ሲፈጥር አብሮ ሳይፈጥራት አይቀርም» ትላለች ከአያቷ መንደር ሄዳ የአጫውቲትን ምንጭ ባየች ቁጥር:: ረጃጅም ዛፎች ዙሪያዋን ከብብ አድርገው እንደ ዳስ ሽፍን እድርገው ይዘዋታል:: የፀሀይ ጨረር እንኳን በጭላንጭል ነው የሚያገኛት:: ጦጣዎችና ጉሬዛዎች ዛፎቹ ላይ እየተንጠላጠሉ ሲዛላሉ ማየት ከቶም ቢሆን የማይጠግቡት የተፈጥሮ ትርዕይት ነው:: የተለያዩ ወፎች የሚያሰሙት ጡዕመ--ዜማ በዓለም ላይ ያለ የረቀቀ የሙዚቃ መሳሪያ እንኳ ከቶም ቢሆን ሊፈጥረው አይችልም:: በየሳምንቱ አርባተንሳ ብትሄድ አትጠላም:: ተፈጥሮን እንዳለች ታገኝበታለች:: እንዲህ ከምትወዳት የእያቷ መንደር ለመስከ ሥራ ይነበብ ሊወጣ ነው:: አገር ጉድ ባይል እብራው ብትሄድ በወደደች::

«ለነገም ቢሆን መዘጋጀቱ አይሻልም ታድያ አለችው:: አጠገቧ እንዳይሆን ፈለገች ነገር ግን የምትከፍተውን መንገድ ሁሉ እየዘጋ እሰቸገራት። አብረው መታየታቸውን ደግሞ በብዙ መልኩ አትወደውም። በደርግ ካድሬዎች ዐይን ውስጥ መግባት የለባቸውም። የደርጅታቸው ዲስፕሊንም አይፈቅድም:: ጓዶች በተቻለ መጠን በሆነ ባልሆነው አብረው እንዳይታዩ ታስጠነቅቃለች። በኗሪው ዘንድም ቢሆን የአንድ ሳምንት ቡና ማጣጫ መሆን አትፈልግም። ግን ብስክሊቱን በእጁ እየገፋ ተከተላት። ፍቅሩ ሰቅጽበት በሐሳቧ ብልጭ ብሎ ድርግም እለ።

ክሊኒክ ሲደርሱ ግቢው አዳፋ ጋቢ በለበሱ የአካባቢው ገበሬዎች ተሞልቶ ጠበቃቸው። ከእንጨት ርብራብ የተሰራችው መቀመጫ ምልታ በሽተኛው ሁሉ የውስጥ ሕመሙን እያዳመጠና እያቃሰተ ሜዳው ላይ ፈሷል። ባላገሩ ካልወደቀ በስተቀር ለቁም ሕመም ሐኪም ቤት እይመጣም። መነሳት ሲያቅተው በአራት ሰው ሸከም በቃሬዛ ሌሊቱን ሙሉ ሲጓዝ አድሮ ይደርሳል:: እዚያው ከሐኪም ቤቱ ግቢ ውሰጥ ወድቆ ወረፋውን ሲጠባበቅ ያነጋል::

«አትዬ ትሩፋት እግዜር ይማርሽ። ምነው ምን አመመሽ?» አላት የክሊኒኩ ዘበኛ። ሊይነበብ የእጅ ሰላምታ ሲሰጠው ደግሞ ሁለቱን ሊያገናኛቸው የሚችል ዝምድና እየፈለገ ነበር፡፡ አንድ ላይ መምጣታቸው ጥያቄ እንዳጫረበት መገረም የሚነበብበት ገጽታው ይመሰክራል፡፡

«ትንሽ አሞኝ ነው» አለችው ፊቱ ላይ ያየችው ሁኔታው እያሳቀቃት፡፡ «ትኩሳትና የመቀረጣጠፍ ስሜት ስለሚሰማኝ ወባ እንዳይሆን ሰግቼ ነው እንጂ ይህን ያህል የጠበቀ በሽታ አኳን አላመመኝም» አለች። የዚያን ሁሉ በሽተኛ ስቃይ ስታይ የእሷ የቅብጠት እየመሰላት።

«ዛዲያ ለዶክተር ፍስሃ ልንገርልሽ!» ብሎ መልሷን ሳይጠብቅ በችኮላ ሄደ። ባይና ተከተለችው። ከሊኒከ ተብየዋ የጭቃ ምርጓ ረግፏል፡፡ ማገሯና ቋሚ እንጨቷ እንደ ከሳ ሰው ጎን አጥንት ገጠዋል። የውስጧ ምርግ እንዳለ ቢሆንም የሐኪም ቤት ሁኔታ ሲያልፍም አልነካት። አንድ አሮጌ ጠረጴዛ ሰኔል ከለበሰው ወለል መሀል ላይ ይታያል። ከጠረጴዛው ኋላ ሐኪም ፍስሃ በረጅም ቀጭን ቁመናው ላይ ነጭ ጋዎን ደርቦ ወንበር ላይ በኩራት ጉብ ብሏል። እግዳሚ ጣውላ መሰል መቀመጫ ላይ የተቀመጠ አንድ ኮስማና በሽተኛ ያንጋግራል። የደም፣ የሽንት..... ምርመራ ብሎ ነገር መቼም አይታሰብም። ዶክተር ፍስሃ የመሰሰውን ከኒን ወይ መርፌ ያዛል። አብዛኛውን ጊዜ መርፌ ማዘዝ ይቀናዋል። የአካባቢው ኗሪ «እጁ መድሃኒት ነው» እያለ ሙገሳውን ይቸረዋል። ድሬሰር ቢሆንም "ዶክተር" ብሎ ይጠራዋል፡፡ እሱም ማዕረጉን የወደደው ይመስላል፡፡ ዘበኛው በፍጥነት እንደ ሄደ ሁሉ በፍጥነት ተመለሰ።

«አትዬ ትሩፋት ነግሬልሻለሁ፡፡ ውስጥ ያለው ታካሚ ሲወጣ አንቺ ትገቢያለች ነይ እንሂድ» አላት ዘበኛው፡፡

አዳፋ ጋቢውን ለብሶ ለመታከም ተራውን የሚጠባበቀው ባላገር የሚሆነውን ሁሉ በትዝብትና በዝምታ ይመሰከታል። በጨለማ እግሩን አንቅፋት እያነጎደው፣ እሾህ እየወጋውና ጋሬጣ እየገሸለጠው ደሙን እያዘራ ሲዳዝ አድሮ ነው ዶሮ ሳይጮህ እዚህ የደረሰው፡፡ የግፍ ግፍ ግን አንቅልፋቸውን ጨርሰው ፀሐይ ሞቅ ስትል በመጡ ከተመኞች ወረፋውን ይነጠቃል፡፡ ዘበኛው ቀድማ ገብታ እንድትታከም ይወተውታታል፡፡ እሷን ደግሞ ሐሳብ ባህሩ ውስጥ ከቶ ብቅ--ትልቅ እያደረጋት ነው፡፡

«ተማርን የምንል ወገኖች ሳይማር ያስተማረንን ገበሬ በማገልገል ፋንታ የምንገለገልበት በምን ሂሳብ ይሆን? እኛ እኮ አንዴውም ባለዳዎች ነን፡፡ ይባስ ተብሎ በአዳፋ ልብሱና በጎልዳፋ አንደበቱ ለምን እንንቀዋሰን? ሰለ ተማሩ ራስን እንደ ምርጥ ዜጋ መቁጠር መቼ ይቀር ይሆን?» እያለች ውስጧን በጥያቄ በመወጠር ላይ ነበረች፡፡





«ሌላ ሰው ከመግባቱ በፊት አንቺች እንድትቀጥይ ነይ አንጂ ቶሎ ቅረቢ» ዘበኛው ይወተውታል፡፡ እሷ ደግሞ ገና ለጥያቄዎቿ መልስ በመፈለግ ላይ ናት፡፡

«እንደሚገባኝ ከሆነ ይህ ያልተማረ የምንለው ገበሬ ነው በቆየ ልማዱ ይቺን አገር ዋልታና ማገር ሆኖ የያዛት። በበሬ ጉልበት እያረሰ። ተማርኩ ብሎ ራሱን የሚኮፍሰው ወገን አገርን ያዘመነ ምን አዲስ ነገር ፈጠረ? ወገንን ያበለጸገ ተግባር ምን ሰራ?» እያለች ሜዳ ላይ የተሰጣውን በሽተኛ እያየች በሐሳብ ስጥማለች። ዘበኛው ቶሎ ገብታ ቶሎ ህክምና እንድታገኝ ፈልጓል፡፡ ይነበብ ዝም ብሎ ይመለከታታል፡፡

ለራሷ ቅድሚያ ሰጥታ ይህን ሁሉ ሰው ጥሳ መግባት ከበዳት። የሕይወት መስዋእትነት እስከ መክፈል ድረስ ታግላ በሕዝባዊ መንግሥት እንዲመራ በሕቡዕ የምትታገልለት «ሰፊው ሕዝብ» ማለት ይኸ ከፊቷ የምታየው ነው። የራስ ወዳድነት ትንሽ ትልቅ የለውም። ከጨቋኝ መንግሥት ነፃ ልታወጣው የምትታገልለት ሰፊው ሕዝብ ለምትለው በትንሹም ቢሆን ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ መብቱን ልታከብርለት ይገባል፡፡ ሌሊቱን ሙሉ እንደ ጅብ ሲዳዝ አድሮ ቀድሟት ወረፋ የሚጠባበቀውን ሕዝብ ረግጣ ከገባች ትግሉስ ምኑን ትግል ሆነ? በተግባር ያልዋለ ዓላማስ ምኑን ዓላማ ሆነ? የራሷን ጥቅም ካስቀደመች ከጨቋኙ የደርግ ወታደራዊ መንግሥት በምን ትለያለች? ነፍስና ስጋዋ በመግባትና ባለመግባት መካከል ሙግት ገጠሙ።

«ምነው እትዬ ትሩፋት ፈዘሽ ቀረሽ እሳ? ህመሙ ጠናብሽ ይሆን? ትገቢያለሽ ብሎ እየጠበቀሽ እኮ ነው ዶክተር ፍስሀ» አላት ዘበኛው። «ወባ እኮ እናት ላይ ከወጣች አቅል አስታ ወፍፍ ታደርጋለች» አለ በውስጡ፡፡ ትሩፋት በወባዋ ምክንያት ራሷን የሳተች መስሎት እየሲጋ፡፡

«አይ አልገባም!» አለችው ቁርጥ አድርጋ። «ባይሆን ሰው ቀለል ሲል በኋላ እመለሳለሁ» ስትለው ዘበኛው ምን ለማለት ፈልጋ እንደሆነ ጨርሶ አልገባውም። ወባዋ እናቷ ላይ ወጥታ እየቃዠች ወይ ደግሞ ወፈፍ ያደረጋት ነበር የመሰለው። እስከ ዛሬ እንኳን የመንግሥት ሰራተኛ ሆኖ ይቅርና የዚያች ከተማ ኗሪ የሆነ ሰው ሁሉ ለባላገሩ ወረፋ ቅድሚያ ሲሰጥ አይቶ አያውቅም፡፡ ትሩፋት ተመልሳ ወደ ቤቷ መንገድ ጀመረች፡፡ ፊቷን አዞራ ስትሄድ ሁሉ አላመነም፡፡ ከኋላዋ በስጋት እየተመለከታት ነበር፡፡ ይነበብ አብሯት ባይኖር ኖሮ ከቤቷ ሳያደርስ ብቻዋን እምኖ እይለቃትም ነበር፡፡

«ለምን ገብተሽ አልታከምሽም ነበር? ገበሬውን እየረገጡ ያለወረፋ መግባት በአንቺ አልተጀመረም» አለ ይነበብ፡፡ እንደ ስጠ ሜዳው ላይ ከተዘረጋው በሽተኛ ላይ ዐይኑን ጥሎ።

«ገበሬውን እየረገጡ ያለወረፋ አለመግባት ደግሞ ዛሬ በእኔ ይጀምራል» አለች ፍዝዝ ብላ እሷም በሽተኞችን እየተለከተች::

«ውሳኔሽን አደንቃለሁ። እንዲት ጠብታ ውሃ ቀስ በቀስ በርሚል ትሞላለች ይባላል። እያንዳንዳችን ለጊዜያዊ ጥቅም ባንስገበገብና ለትክክለኛው አሰራር ራሳችንን ብናስገዛ ዛሬ የተጀመረ አስቸጋሪ የሚመስለን ጥሩ ነገር ሁሉ ቀስ በቀስ ይለመድና ነገ ባህል ይሆናል። «እኔ ባደርገው ሌላው አያደርገው» እያልን ተስፋ በመቁረጥ ድርጊቱ እዲቀጥል ካደረግነው ግን ማቆሚያ አይኖረውም።» አለ ይነበብ::

«ይህን ያህል አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለህ ነው?» አለች:: አሁንም አብረው መሆናቸውን እየጠላች::

«እየሽ ትሩፋት ዛሬ አንቺ ጀምረሽዋል:: ነገ እኔ እቀጥላለሁ። ከነገ ወዲያ ደግሞ ሌለው እየተከተልው እየሰፋ--እየሰፋ---ይሄዳል። አንድ ያልተለመደን ጥሩ ነገር እስኪለመድና እስኪታወቅ ድረስ የግድ አንድ ደፋር ጀማሪ ያስፈልገዋል። ዛሬ እንዲት የሴት ጀግና አግኝተናል» ብሎ ለሞካሻት። ከልቡ ነበር።

«ሙገሳው የበዛብኝ አይመስልህም?»

«የበዛ አልመሰለኝም» አላት ትኩር ብሎ እየተመለከታት:: «ትኩሳቱን እንኳ እንዲያስታግስልሽ አስፕሮን ብትወስጂበት ይሻላል:: ቆይ ሱቅ ውስጥ ገዝቼልሽ ልምጣ::»

«ኧረ ግድ የለም አትቸገር:: ሱቁ መንገዴ ላይ ነው:: ይልቅ ለነገ ጉዞህ ብትዘገጃጅ ይሻላል» አለችው:: እሷ የምትፈልገው አስፕሮን እንዲገዛላት አይደለም:: ከአጠገቧ እንዲሄድላት ነው:: ለሁሰተኛ ጊዜ ፍቅሩ በዐይነ-ሕሊናዋ ውልብ ብሎ አለፈ።

«አቤትሽ ላድርስሽ እንጂ እሞሽ የለም እንዴ? ምነው ሻይ ቡና እንዳትይ ፈራሽ?»

«እ--ይ! ለእሱ ሳይሆን አንተም ለነገ ጉዞ መዘገጃጀት ይኖርብሃል። እኔም ይህን ያህል የጠና ሕመም እላመመኝም ብዬ ነው» መልስ አልሰጣትም:: ዝም ብሎ አብሮ መጓዙን ቀጠለ። በር ላይም አልተመለሰም። ተከትሏት እቤት ገባ::

«ምን ዓይነት ጉድ ነው? የምን መሟዘዝ ነው? ተከትሎኝ እንዳይመጣ ከዚህ በላይ እንዴት ብዬ እንድነግረው ይፈልጋል?» አለች በውስጧ:: የምሳ ሰዓት ደረሰ:: ይነበብ አልሄደም:: ምሳ ተበላ። ይነበብ ቁጭ እንዳለ ነው:: ቀልጣፋዋ የትሩፋት ሰራተኛ የቡና እቃ ቶሎ አቀራረበች። ቡና እስከ በረካ ተጠጥቶ ካበቃ በኋላም ይነበብ አልተነቃነቀም። የባጥ





የቆጡን እያወራ ቆየ:: ተሰናብቷት ሲሄድ ጊዜው መሽቶ ላይን ያዝ አድርጎ ነበር። ትሩፋት ጋደም ካለችበት አልጋዋ ላይ በረጅሙ ተንፍሳ ተመቻችታ ተኛች።

******

ትሩፋት በእምባገነኑ የደርግ መንግስት ጭካኔ ማዘን የጀመረችው ገና በጠዋቱ የስልሳዎቹን የኃይለሥላሴ ባለስልጣናት ሞት በሬድዮ ከሰማችበት ጊዜ አንስቶ ነበር:: ያን ጊዜ ገና አዲስ ሥራ ጀማሪ ሆና ሁመራ ነበረች::

ፊውዳላዊው የዘውድ አገዛዝ እንዲለወጥ የአቅሟን ታግላለች:: ለብዙሀኑ ሕዝብ የተሻለ ሕይወት ማምጣት ያልቻለ መንግሥት---አገርን ያላሳደገና ያላዘመነ መንግሥት--ዲሞክራሲን ያላሰፈነ መንግሥት ከስልጣን መወገድ አለበት ብላ በጽኑ ታምናለች:: በአገሪቱ ውስጥ ዜጎች በእኩልነት፤ በወንድማማችነትና በሰላም አብረው እንዲኖሩ ከፍተኛ ምኞት አላት:: አብዮት ፈንድቶ አገሪቱን በሞላ እንደ ፈጥኖ ደራሽ ውሀ ሲያጥለቀልቃት ምኞቷ እውን ይሆን መስሏት በደስታ ነበር የተቀበለችው:: የስልሳዎቹ የቀድሞ ባለስልጣናት የጅምላ ግድያ ግን አስደነገጣት:: መሸነፋቸውን አምነው እጅ ከሰጡ በኋላ እንደ ባዕድ ወራሪ ጠላት በጭካኔ በጅምላ ተረሸነው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ አፈር መልበሳቸው በእጅጉ ዘገነናት--- በጣም አሳዘናት:: የቀድሞ ባለስልጣናቱ ከስልጣን አንወርድም ብለው ጦርነት እስከ አልገጠሙ ድረስ በአገራቸው ላይ እንደ ማንኛውም ተራ ሰው መኖርን ተከልክለው በጅምላ መገደላቸውን በፍጹም የምትቀበለው ነገር አልሆነም:: ለትሩፋት የደርግ የመጀመርያው አሰቃቂ የጭካኔ እርምጃው እዚህ ላይ ጀመረ:: ዜናውን በሬድዮ ስትሰማ ቀኑን ሙሉ እህል መብላት እንቢ ብሏት ዋለች::

የሜይዴይ በዓል ደግሞ ሌላ ሁለተኛውን ዙር የደርግ መንግሥትን ዐይን ያወጣ ጭካኔ ይዞላት ከተፍ አለ:: በደርግ መንግሥት ላይ ከፉኛ ቂም ቋጠረች:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ለመጀመርያ ጊዜ በጎንደር ሕዝብ በተለይ በአብዛኛው ወጣትና በደርግ መንግሥት መካከል ግብ ግብ የተፈጠረው ገና ከጅምሩ ነበር:: በሜይዴይ ክብረ-በዓል ጊዜ ለግል ጉዳይ ፈቃድ ወስዳ ትሩፋት ጎንደር ከተማ ውስጥ ነበረች:: አጋጣሚውን ተጠቅማ የሜይዴይ ሰልንፍን ለማየት ፒያሳ አደባባይ ተገኝታለች:: ከየጦሩ የተሰባሰበው ደርግ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የገባውን ቃል አክብሮ ወደ ካምፑ መመለስ ይገባዋል የሚሉ መፈክሮች ከየአቅጣጫው ብቅ ብቅ ሲሉ ተመለከተች:: በቀይ ቀለም የተጻፉ መፈክሮችን የያዙ ወረቀቶችና ቀይ ጨርቆች ከየኪሱ መመዘዝና መዘርጋት የጀመሩት የበዓሉ የክብር እንግዳ የሆኑት የወታደራዊው የደርግ መንግሥት ሙሉ አባልና የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ ገና ከስፍራው ሳይደርሱ ነበር::

የሕዝብ ስልጣን ለሕዝቡ!

ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ!

ወታደሩ ወደ ካምፑ!

በላባደሩ ስም አይነገድም!...

ፒያሳ በሚገኘው አደባባይ አየሱስ  በወጣቶች መፈክር ድብልቅልቋ ወጣ:: የደርግ ባለስልጣናት ዐይናቸው ደም ለበሰ:: አጸፋውም ጥይት ሆነ:: ድንገት ድብልቅልቅ ባለው ተኩስ ምክንያት ለሰልፍ የወጣው ሕዝብ ተተረማመሰ:: ሁሉም አግሩ ወደ መራው የነፍስ አውጭኝ ሩጫውን ተያያዘው:: ከፈጥኖ ደራሽ ወታደር ድብደባና ግድያ ለመዳን ከፍት ሆኖ በተገኘው የፒያሳ ሱቅ ሁሉ ዘው እያሉ መግባት ሆነ:: ወታደሩ ማሳደዱንና ዝም ብሎ እንዳገኘው መተኮሱን ቀጠለ:: ጎንደር ከተማ በተኩስ ተናጠች::

ትሩፋት እንዴት እንደ ገባች ባታውቅም ራሷን ያገኘችው ከጥቂት ወጣቶች ጋር ከአንዲት አሳቻ ቤት ውስጥ ነበር:: የቤቷ ባለቤት በሩን ከዘጉ በኋላ  እየተርበተበቱ «መሬት ያዙ! መሬት ያዙ» ሲሉ እንደ ህልም ነበር የሰማቻቸው:: ሁሉም ራሱን እየቀበረ ባለበት ለጥ ብሎ ተኛ:: ቀስ እያለ ተኩሱ እየበረደ መጣ:: በዚያ ድብልቅልቅ ጩኸት ፋንታ ጸጥታ ነገሰ:: አልፎ አልፎ ውር ውር ሲሉ ከሚታዩት ወታደሮች በስተቀር ጸጥ--ረጭ ያለው ከተማ የተወረረ መለሎ ያስፈራል::

በወጣቶቹ ድፍረት የተናደዱ ወታደሮች ድንገት ሲያገኙኝ ይችላሉ ብላ ትሩፋት አቶባርኮ አነራሔል ከሚኖሩባት ቤት ድረስ መሄድ አስፈራት:: ለዛሬ እዚሁ ቅርብ ቦታ ማደሪያ ቦታ ስታሰብ ቀድማ የመጣችላት ቀድርያ አህመድ ነበረች:: ፒያሳ ላይ የታወቀ  ትልቅ የልብስ ሱቅ አላቸው-- ቀድርያና ባሏ:: የራሔል እብሮ አደግ ጓደኛ ናት:: ሽኒ ወንዝ መልምላ ያሳደገቻት የአዲስ ዘመን ልጅ ቀድርያ:: ጓደኝነቱ የዝምድናን ያህል አድጎ ቤተሰባዊ ሆኗል::  ትሩፋት ጎንደር ብቅ ባለች ቁጥር  አልፎ አልፎ ቀድርያ ጋ ማረፏ የተለመደ ነው:: መኖሪያቸው ሱቁ በታች ያለው ምድር ቤት ነው:: በእንዲህ ያለ አስፈሪ ሰዓት ደግሞ ውስጥ ውስጡን ተሂዶ  በጀርባ በኩል ለመግባት  ያመቻል:: ከቀድርያ ቤት ሄዶ ከማደር ሌላ የተሻለ ምርጫ አልነበራትም:: ፈጠን ፈጠን እያለች ወደ ዚያው ገሰገሰች:: ከነቀድርያ ቤት ስትደርስ ግን የሆነውን ማመን አቃታት:: ነፍሰጡሯን ቀድርያ አሱቋ በር ላይ የሜይዴይ ጥይት በልቷታል:: ዘመድ አዝማድ ተሰባስቦ ይብላላል:: ራሔል ያዙኝ ልቀቁኝ ትላለች:: ትሩፋት በደርግ ላይ ከጥላቻ ያለፈ ቂም ቋጠረች::

******

በአንበሳሜ የገጠር ከተማ ውስጥ የኢሕአፓን መዋቅር ለመዘርጋት የተመለመሉት ጓዶች ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ ያን ያህል በንድፈ ሐሳብ የበሰሉና ሰፊ ዕውቀት ያላቸው አልነበሩም:: እንዲመለመሉ ያስቻላቸው ምክንያት ለመማርና ለማወቅ ያላቸው ጉጉት፤





የደርግ መንግስትን እምባገነናዊ አካሄድ ከድርጊቱ ጠንቅቀው ያወቁ መሆናቸውና ለለውጥ የተነሳሳ መንፈስ የተላበሱ መሆናቸው ተረጋግጦ ነበር:: በጠንካራ ዲሲፕሊን ከታነጹ-- ለኢሕአፓ ዲሲፕሊን ተገዢ የሆኑ ቆራጥ ታጋዮች ሊወጣቸው ይችላል ተብሎ ታምኖ ነው:: በንድፈ ሐሳብ ዕውቀት  ያላቸውን ክፍተት ለመሙላት ደግሞ ለአካባቢው እንደ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ የሚያገለግለው ስብሰብ ሌት ተቀን ተግቶ እየሰራ ይገኛል:: እያንዳንዱ አባል በስሩ ለመለመላቸው ወጣቶች   በየቀኑ   ትምህርት የመስጠት ግዴታ ተጥሎበታል::  ወይም እንደ ወቅቱ አጠራር የርዕዮተ-ዓለም ትጥቅ ማስታጠቅ ይጠበቅበታል:: ይህን ተግባር ለማከናወን መጀመርያ መልማዩ ራሱ ጥርት ያለ እውቀት መጨበጥ ይኖርበታል:: በተለይ የኅብረተሰብ እድገት ታሪክ አመጣጥን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠበቅበታል:: ሰለ ጥንታዊ ጋርዮሽ ኅብረተሰብ አኗኗር፣ ስለኀሳ አመሰራረት፣ ስለመደብ አመጣጥ፣ ስለመንግስት አፈጣጠርና ሰለ ፋሽስታዊ መንግሥት እነሳስና ተግባሩ የማያወላውል እውቀትና እቋም ሊኖረው ይገባል::

ትሩፋት ከቡድኗ ጋር ትምህርቱን በትጋት ወሰደች:: ከቡድኑ አባላት መካከል የአለቱን ትምህርት እንዲያስተምር የተመደበው አባል  እንደ ዲያሌክቲካዊ ማቴሪያሊዝም ከመሳሰሉ መጽሐፍት ውስጥ የሚያስፈልገውን ርዕስ ወስዶ ተዘጋጅቶ መጥቶ እንዲያስተምር ይደረጋል:: በተጨማሪም እያንዳንዱ አባል ቢያንስ በቀን ለሶስት ሰዓት ያህል በግሉ የማንበብ ኃላፊነት ይጣልበታል::

ምንጊዜም በስብሰባው ላይ መጀመሪያ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ይካሄዳል:: በተለይ ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ የተመደበው አባል ኢሕአፓ በአገሪቱ ውስጥ ምን እየሰራችና የትግሉ ሁኔታ ከምን ደረጃ ላይ እንደ ደረሰ ያለውን እንፎርሜሽን ያቀርባል:: ትሩፋት ከሁሉም በላይ በጉጉት የምትጠብቀው ይህንን የኢንፎርሜሽን ጊዜ ነበር:: እዚችው አንበሳሜ ከተማ ተቀምጦ እሷ ያልሰማችውን ወሬ ሁሉ ይህ አባል እንዴት እንደሚያገኘው ይገርማታል:: በይበልጥ ደግሞ ኢሕአፓ በየቀኑ የምታገኘውን ድልና የደረሰችበትን የእድገት ደረጃ ማወቅና መስማት ከምንም በላይ ያጓጓታል:: የደርግ ፋሽስታዊ መንግሥት ወድቆ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ቶሎ እንዲቋቋም ፍላጎቷ ከፍተኛ ነው:: በሚያስቾግሩ የመንግሥት ሰዎች ላይ ኢሕአፓ በምትወስዳቸው  የመልስ እርምጃ ምክንያት ደርግ  የሚወስደው የአጸፋ ምት ደግሞ ያሳስባታል፤ ያስጨንቃታል:: ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እመዝኖ ይታያታል::

አንድ ቀን በተለመደው ሰዓት ኮሚቴው ተሰባሰበ::  እንደ ሁልጊዜዉ መጀመርያ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ተካሄደ:: ለእለቱ የተመረጠው ትምህርት ቀጠለ:: ሰብሳቢው ዘመድኩን ከትምህርቱ በኋላ ተጨማሪ ሃሳብ ጠየቀ:: ከተጨማሪ ሃሳብ በኋላ  ጥያቄ ቀረበ:: ለጥያቄዎች  መረጃ መጽሐፍትን በማጣቀስ መልስ ተሰጠ:: ስብሰባው ከማለቁ በፊት አሁንም ሰብሳቢው ማላሰቢያ እንዳለ ጠየቀ:: ትሩፋት እጇን አወጣች:: የከተማ ግድያ ጉዳይ በአዕምሮዋ እየተመላለሰ ሲያስጨንቃት ቆይቷል:: በእለቱ ከተሰጠው

ትምህርት እርዕስ ጉዳይ ጋር ባይገናኝም ድርጅቱን አደጋ ላይ ይጥላል ብላ ሰግታለች:: ምላሹ ምንም ይሁን አባላቱ ሰምተውት ሐሳቧን እንዲጋሯት ፈልጋለች::

«እኔ ይሄ የከተማ ግድያ ቢቆም ይሻላል የሚል አስተያየት አለኝ። ምክንያቱም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዘነ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የደርግ ፋሽስታዊ መንግሥት 'የአንድ አብዮተኛ ደም በሺህ አናርኪስት ደም ይመነዘራል' የሚል መፈክር ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ሰውን ሁሉ በጅምላ እያፈሰ ለእስር እየዳረገ ነው። አንድ የደርግ አባል ሲገደል በአካባቢው የተገኘ ሰው ሁሉ ሕጻናት፣ እናቶች፣ አባቶች፣ አሮጊትና ሽማግሌ ሳይለይ ጅምላ ጭፍጨፋ የተፈጸመ ነው:: ብዙ ንጹሃን ወገኖቻችን በነፃ እርምጃ ስም የደርግ ታጣቂዎች ሰለባ ሆነዋል። ብዙ ጓዶቻችን ታፍሰው በየጣቢያውና በየወህኒ ቤቱ ተወርውረዋል:: ለመናገር በሚከብድ ታይቶና ሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በፋሽስታዊ ቶርቸር ፍዳ መከራ እየተቀበሉ ይገኛሉ:: በየቦታው የህዋስ መረቦቻችን መገናኘት እስኪያቅት ድረስ ተበጣጥሰው ችግር ላይ ወድቀናል። በዚህ የከተማ ግድያ ምክንያት መስራት የሚገባንን ያህል እያከናወን አይመስለኝም። በዚህ የከተማ ግድያ ከድርጀታችን ይልቅ ደርግ በእጅጉ ተጠቃሚ እየሆነ መጥቷል። ፋሽስታዊ ተልዕኮውንም ለመተግበር የድርጅታችንን የአልሞት ባይ ተጋዳይነትን የመከላከል እርምጃ ጥሩ አጋጣሚ የሆነለት ይመስለኛል:: እንደሚታየው የጥፋት ተልዕኮውን ለመወጣት ተጠቅሞበታል:: ስለሆነም ይህ የከተማ ግድያ ለድርጅታችን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አመዝኖ ታይቶኛል:: ጉዳዩ ለበላይ አካል ቀርቦ አስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጠው እሳስባለሁ» አለች::

ከወር በፊት በአንድ የአብዮት ጥበቃ ኃላፊ ሞት ምክንያት ጎንደር ከተማ ላይ የተካሄደዉን ነጻ እርምጃና የደረሰውን የሕዝብ እልቂት አይታለች:: አሁንም ያ ከፉ ትዕይንት ከፊቷ መጥቶ ድቅን አለ:: ሰውነቷን ሰቅቅ አደረጋት:: የዚያን ቀን በዚያ ጦሰኛ የአብዮት ጥበቃ ኃላፊ ሞት ምክንያት የጎንደር ሕዝብ በነጻ እርምጃ ተፈጀ:: እድሜ ፣ጾታ፣ ሀይማኖት፣ ዘርና ቋንቋ ሳይለይ የተገኘው ሁሉ በተገኘው ቦታ እንደ ቅጠል ረገፈ::

የአብዮት ጥበቃ ኃላፊው ደም የጠማው ከፉ ሰው ነበር:: ወጣት የሆነ ሁሉ የኢሕአፓ አባል ይመስለዋል:: ወጣቱ ኃይል በሙሉ ቢያልቅ የደርግ መንግሥት ተጠናክሮ በሁለት እግሩ የሚቆም የሚመስለው ከንቱ ሰው ነበር:: በሰበብ አስባቡ ብዙ ሰው አሳሰረ፣ አስገረፈ፣ አስገደለ፣ አገር ጥሎ እንዲሰደድ ምክንያት ሆነ:: ከዚህ እኩይ ተግባሩ እንዲቆጠብ ተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢደርሰውም ሊታረም አልቻለም:: የነጻ እርምጃው እዋጅ ደግሞ ለጅምላ አፈሳውና ግድያው የተመቻቸ አጋጣሚ ፈጠረለት:: በስመ ወጣት ያገኘውን ሁሉ ያጭደው ጀመር:: እሱም አልቀረለት ስም የለሽ ሞት ሞተ:: በእሱ ጦስ ግን የብዙዎች ሕይወት ተቀጠፈ:: እንደ ዚያን ቀን ጎንደር ከተማ በልጆቿ በደም ታጥባ አታውቅም::





እንደ አለመታደል ሆኖ ትሩፋት በዚያ የአብዮት ጥበቃ ሞት ምክንያት የተካሄደው የነጻ እርምጃ ከፉ ትዕይንትም አላለፋትም:: ሕይወቷን ሙሉ እንደ ዚያች እለት የሚዘገንን ሁኔታ መቼም ቢሆን የሚያጋጥማት አይመስላትም:: ወታደሮች አንድም ሰው በጎንደር ከተማ አይቅራችሁ የተባሉ ነበር የሚመስሉት:: እንደ እበደ ውሻ እየተሯሯጡ ያገኙትን ሰው ሁሉ በአውቶማቲክ መሳሪያ ጥይት ጭንቅል ጭንቅላቱን እየበረቀሱ አነጠፉት:: ደም ያሰከራቸው --ደም የጠማቸው ወታደሮች ሬሳ በሬሳ ላይ እየተረማመዱ-- ከወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ የወገናቸውን ነፍስ እንደ ቅጠል ቀጠፉ::

ትሩፋት ለራሷ እንኳን ተዓምር እስኪመስላት ድረስ ከነጻ እርምጃው እልቂት ያመለጠችው ለጥቂት ነበር:: ወደ ጎንደር የመጣችበትን ተልኮዋን ፈጽማ-- መያዝ የሚገባትን ማቴሪያል ይዛ ወደ እውቶብስ ተራ እየገሰገሰች ነበር:: ሳታስበው የተኩስ እሩምታ በአንዴ አካባቢውን አናወጠው:: ደመነብሷን ስትሮጥ ሄዳ ከፍት ሆኖ ተሳፋሪ ይጠባበቅ ወደ ነበረ እውቶብስ ውስጥ ዘላ ጥልቅ አለች:: ጥቂት ተጓዦች ውስጡ ነበሩ:: ድንገት በተፈጠረው ድብልቅልቅ ተኩስ የደነገጠች ድርጭት መሰለዋል:: በደመነፍስ ሄዳ ባዶ ወንበር ላይ ተቀመጠች:: ረዳቱ ከየት እንደ ሆነ አይታወቅም ሲበር መጥቶ የአውቶብሱን በር በድንጋጤ በሚንቀጠቀጥ እጁ ስቦ ከረቸመው:: እንደ ተተኮሰባት ሚዳቆ ዓይኑ ፈጧል:: ከላይ ከላይ ያለከልካል::

ትሩፋት በአውቶብሱ መስታወት እሻግራ አውቶማቲከ መሳሪያቸውን አቀባብለው የሚሯሯጡትን ወታደሮች ተመለከተች:: አንዲት እናት እየተርበተበቱ ከቤታቸው ሲወጡ አየቻቸው:: በራቸው ላይ ደሙ እንደ ጅረት እየተንጀረጀረ በግንባሩ ድፍት ካለ ሬሳ ላይ በቁማቸው ዘፍ ብለው ሲወድቁ እሷም «እ!---» የሚል ድምጽ እሰምታ ፊቷ ካለው የወንበሩ መደገፊያ ላይ በግንባሯ ደፋ አለች:: የወንበሩ መደገፊያ ብረት ሲመታት እንኳ አልታወቃትም:: በደም ከተበከለው ሬሳ ላይ የወደቁትን እናት ሲሮጥ የደረሰ ወታደር ጀርባቸው ላይ የጥይት ዶፍ አርከፍከፎባቸው ኢቃ የጠፋው ሳይመስለው ጥሏቸው በፍጥነት ወደ ሌላ አለፈ:: እናትና ልጅ ሳይሆኑ አይቀሩም-- ሬሳቸው ተነባበረ:: ትሩፋት ሁለት እጆቿን አደራርባ በሀዘን ጦር ተወግታ ከቆሰለች ልቧ ላይ አሳረፈቻቸው:: ዘገነናት-- ሆዷ ተገለባበጠ:: ሲያስታውካት ፈለገ:: እጇን ከልቧ ላይ አንስታ ሆዷን ጭብጥ አድርጋ ያዘች:: ከአውቶብሱ ወርዳ ከተማውን «ኡ!-ኡ!-ኡ!» እያለች መዞር አሰኛት:: የአውቶብሱ ረዳት

«ራሳችሁን ዝቅ- ዝቅ አድርጉ እንዳትታዩ! ራሳችሁን ከወንበሩ ስር ቅበሩ! እንዳታስፈጁን!-- እንዳታስጨርሱን» አለ በሚርበተበት ድምጹ:: እሱም ራሱን በሁለት እጁ ይዞ ወንበር ስር እየቀበረ:: ትሩፋት ሀሞት በአፏ የመጣ መሰላት:: ምርር ሲላት ታወቃት:: እንደ እለት የከበደ ሀዘን ልቧን ተጭኖት-- ቁጭትና ንዴት ናላዋን አዞሮት ሆዷን በእጇ ጭብጥ አድርጋ እንደያዘች ማልቀስ ፈለገች:: እንባዋ ደርቋል:: በደርግ መንግሥት ላይ ያላት ጥላቻ ግን ልቧ ላይ አድጎ-- አድጎ ቋጥኝ አከለ:: የደርግ ጭካኔ ተነግሮ የማያልቅ ተተርኮ

የማያበቃ ሆነባት:: የዚችን አገር ትውልድ ጨርሶ አጥፍቶ ከመጥፋቱ በፊት የአምባገነኑን ደርግ መንግስትን ውድቀት ማፋጠን ተገቢ መሆኑን ከልቧ አመነች::

«አምባገነን መንግሥት በሕዝብ አመጽ መደምሰስ አለበት!!» የሚለው የዘመድኩን የዘወትር አባባል በሕሊናዋ አስተጋባ:: ከሁሉም በላይ ግን የእኚያን እናት አወዳደቅ ዛሬም--ነገም-- ለዘለዓለምም አትረሳውም::

ከዚያን ቀን በኋላ ኢሕአፓ የምትወስደው የከተማ ግድያ በጣም እያሳሰባት ተቸገረች:: በእውቀትም ሆነ በልምድ ከሷ የበለጡ ጓዶች ከላይ አመራሩ ውስጥ እንዳሉ ታውቃለች:: ከእሷ የበለጠ ሁኔታውን እንደሚረዱት ትገነዘባለች:: በዚህ የከተማ ግድያ ሰበብ ሰው እንደ ቅጠል መርገፉን እየተመለከቱ አንድ ውሳኔ አለማስተላለፋቸው ግን ያሳሰባት--- ያስጨንቃት ጀመር:: የእኚያ እናት አሳዛኝ አወዳደቅ በአየለቱ የምታስታውሰው የማይረሳ ሰቀቀን ሆነባት:: የትውልድ እልቂት መሆኑ አንገበገባት:: ሆነም ቀረ እሷ ለምትገኝበት ቡድን ሁኔታውን አሳውቃ ጭንቀቷን አካፈለች::

«ትሩፋት ያቀረበችው ሐሳብ ማሳሰቢያም ቢሆን ጠንከር ያለ አቋም መያዝ የሚያስፈልገው ነው:: እንደ አጀንዳ ይዘነው ብንወያይበት ይሻላል» አለ ይርጋ የሚሉት ጓድ:: ከመናገር ይልቅ ብዙ ማዳመጥ ይወዳል:: በይርጋ አሳሳቢነት ትሩፋት ያቀረበችው ሐሳብ ለድምጽ ቀረበ:: ከአምስቱ ሶስቱ ስለ ደገፉት ለውይይት ቀረበ:: የከተማ ግድያን በተመለከተ ውይይቱ ጦፈ::

«ጓዶች» አለ ዘመድኩን ያለችውን ሽንብራ ጸጉር በጁ እየገመደ። እንበሳሜ ጠንካራና ብስለት አላቸው ከሚባሉ ጓዶች አንዱ እሱ ነው:: የእድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ-- ዘማችም ነበር::

«የከተማው የውስጥ የትጥቅ ትግል ለምን እንደሚያስፈልግ ሁላችንም ጥርት ያለ እይታ ሲኖረንና ግልጽ አቋም ልንይዝበት ይገባል» ብሎ ጥቂት ጊዜ ዝም አለ:: «ትሩፋት እንደታያትና እንዳቀረበችው ትክክል ናት:: ብዙ ቆራጥ ታጋዮቻችንን እያጣን መሆኑ ግልጽ ነው። ፋሽስቱ ደርግ ይዞት በተነሳው ነጻ እርምጃ በሚለው ፋሽስታዊ የጥፋት ተልዕኮው በድርጅታችንና በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው እልቂት ከባድ ነው:: «ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል» በሚለው አቋሙ ጓዶቻችን ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ሕዝብ እየፈጀ መሆኑ ይታወቃል:: ነገር ግን ልንገነዘበውና ልብ ልንለው የሚገባን አብይ ጉዳይ አለ:: ኢሕአፓ አባሎቿን ስትመለምል የደርግን ፋሽስታዊ ቶርቸር መቋቋም የሚችሉና በዲሲፕሊን የታነጹ መንፈሰ ጽኑዎችን እየለየች ነው:: ከሁሉም በላይ ውድ ሕይወታቸውን መሰዋዕት ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ ቆራጥ የሕዝብ ልጆች አሏት:: ሞት ለነጻነት እስከሆነ ድረስ ያኮራል እንጂ አያስፈራም! ነጻነትን ለሕዝብ ያጎናጸፈ ሞት ዘልዓለም ሲዘከር የሚኖር ታሪክ ሰርቷልና ሕያው ነው! ጨቋኙንና አምባገነኑን መንግሥት እየገደልን ካልሞትን ታዲያ





ትግሉ ምኑን ትግል ሆነ?» ብሎ አሁንም ለጥቂት ጊዜ ትንፋሽ ወሰደ:: ሲናገር ከልቡ ነው:: ፊቱ ላይ ምንጊዜም ቆራጥነት ይነበባል:: ድምጹ ወፈር ያለ ለጆሮ የሚጥም ነው:: ዝግ ብሎ ሲወርድ አድማጭ ይሰባል:: ወኔን የሚያነሳሱት የተመረጡ የአብዮት ቃላቶቹ ተደማጭነት አላቸው:: ቀጠለ ዘመድኩን::

«ከፋሽስታዊ መንግስት-- ጭካኔ የተሞላበት ግርፋትና ሰቃይ እንጂ እንክብካቤ ከቶ ምንም ቢሆን አይጠበቅም:: ከፋሽስታዊ መንግሰት ባሩድ እንጂ የዘንባባ ዝንጣፊ በታሪክ ተገኝቶ አይታውቅም:: አፈጣጠሩንና የታሪክ አመጣጡን እንደ ተማርነው በየትኛውም ዓለም የተከሰተ ፋሽስታዊ መንግስት ጨካኝ ነው:: የሰውን ልጅ ነፃነት ከማፈንና ከመጨቆን አልፎ ተርፎ ለመንግሥቱና ለስልጣኑ ያሰጉኛል በሚላቸው ወገኖች ላይ ሁሉ አሰቃቂ ቶርቸሮችን ይፈጽማል:: ለሰው ልጅ ሕይወት ደንታ የለውም:: ይጨፈጭፋል:: ከእንዲህ ዓይነቱ ፋሽሽታዊ አፈናና ግድያ ነፃ ለመውጣት መስዋዕትነት ግድ ነው:: ከቶም ቢሆን ያለመስዋዕትነት ነፃነት ሊገኝ አይችልም» አለና ጓዶች ላይ ሲያፈራርቀው የነበሩትን ትንንሽ ዐይኖችን ጠበብ አድርጎ ወደ ሌላ ተመለከተ:: ሩቅ የሚያስብ ይመስላል ዘመድኩን::

«እጅ ከወርች ተተብትበን በታሰርንባት አገር ውስጥ መኖርን-- ከሞት ምን ይለየዋል!? እጅና እግርን አጣጥፎ ዝም ብሎ ዐይን እያየ ከመሞት ደግሞ ታሪክ ሰርቶ ስም ያለው ሞት መሞት ይሻላል:: አይሻለንም ትላላችሁ ጓዶች?» ሲል ጥያቄውን አቀረበ ዘመድኩን:: ሁሉም በአዎንታ ራሳቸውን ነቀነቁ::

«የነፃነታችን ቀን ለማቅረብ የከተማው ትጥቅ ትግል ተጠናክሮ ለሜዳው የትጥቅ ትግል ደጀን ሊሆነው ይገባል:: ያ ካልሆነ እስከ አፍጢሙ የታቀውን የደርግ ወታደራዊ ፋሽስት መንግሥት ከቶም ቢሆን ማንበርከክ አይቻልም። ሁለት መንታ መንገድ ላይ ቆመን ማወላወል ከማንችልበት ምዕራፍ ላይ ደርሰናል። ሐሳቤን ላጠቃለውና ወታደራዊው የደርግ ፋሽስታዊ መንግሥት በከተማው የትጥቅ ትግል ተደናግጧል:: ተፍረከርኳል። የነጻነት ጎሕ እስኪቀድና ሕይወታችን እስኪታልፍ ድረስ የከተማው የትጥቅ ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: የከተማ የትጥቅ ትግሉን በተመለከተ ለበላይ አካል ማስተላለፉ ገንቢነቱ አይታየኝም» አለና ተመቻችቶ ተቀመጠ:: ክርክሩ ጦፈ፤ ብዙ ተወያዩ:: በመጨረሻም የከተማ የትጥቅ ትግሉ መቀጠል አለበት በሚለው ተማመኑ። ሆኖም የትሩፋት ማሳሰቢያም ቢሆን ጉዳዩ ለበላይ አካል በሪፖርት መልክ እንዲተላለፍ አቋም ወሰዱ:: ሰዓቱ ገፍቶ ሌሊቱ እየተገባደደ መሆኑ እንኳ አልታወቃቸውም። አምስቱም አባላት በተቀመጡበት ትንሽ ትንሽ አሸለቡ። ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል ተነስተው ሹልክ---ሹልክ እያሉ በተለያየ አቅጣጫ ተበታተኑ::

******

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው እንበሳሜ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች እንደ ድሮው በየቦታው ተሰባስበው በጋራ ማውካካትና እንደ ልብ መጫወት እየቀነሱ መጡ:: በጅምላ የነበረው ጓደኝነት እየቀረ ቀስ በቀስ ድርጅታዊና ቡድናዊ መልክ እየያዘ መጣ:: በእንበሳሜ የገጠር ከተማ ውስጥ የመንግሥት ሰራተኞችና ወጣቶች በቁጥር አነስተኛ ቢሆኑም ግንኙነታቸውና ጓደኝነታቸው ሳይፈልጉትና ሳያውቁት እንደሚደግፉት የፖለቲካ ድርጅት እየሆነ ችግር ተፈጠረ:: የሰደድ፣ የመኢሶን የወዝሊግ... አባላት ናቸው ተብሎ ከሚጠረጥሩ ወጣቶች ጋር እንደ ልብ መጫወት እየቀረ ሆድና ጀርባ መሆን መጣ:: ይህ አዝማሚያ ደግሞ በሕቡዕ ለምንትቀሳቀሰው ኢሕአፓ የከፋ ችግር አመጣ:: ሁኔታው በከተማዋ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው በሚገኙ የገበሬ ማኅበራትም ጭምር የመንግሥት ደጋፊ በሆኑና ባልሆኑ መካከል ልዩነት እየታየ መሆኑን ይነበብ ሲጋቱን ገለፀ:: ቶሎ እርምት ካልተወሰደ በስተቀር እንድ ከስተት ቢፈጠር መጠቋቆምን ሊያስከትል ይችላል:: እያደር ነገሩ ሁሉ የከፋ ይሆኗል ሲል ሀሳቡን አሰተሳሰፈ:: አሁን አሁን እንደ መጀመርያው ጊዜ ከአገኙት ቤት ሰብሰብ ብሎ መወያየት አንኳ እያስፈራ መጣ:: ቀን በቀንማ የማይታሰብ ሆነ:: ብዙ ጊዜ ስብሰባዎች የሚካሄዱት ጨለማን ተገን ተደርጎ ሆነ:: ለዚያውም ሌሊት ሮንድ ከሚዞሩ የቀበሌ አብዮት ጥበቃዎች መጠንቀቅ ግድ ይላል:: አኩለ ሌሊት ላይ ኩራዝ በርቶ ካዩ ቤት እስከፍተው ድንገተኛ ፍተሻ ሊያካሂዱ ሁሉ ይችላሉ:: አንዳንድ ጊዜ ውይይቱ በጨለማ ውስጥ ተቀምጦ በዓይን ሳይተያዩ ዝቅ ባለ ድምጽ ይሆናል:: ጧት ላይ ሁሉም የገባውን ፍሬ ነገር ይጽፍና እንድ ሰው ተቀብሎ ለዶከመንትነቱ ያጠቃልለዋል ::

የዛሬው ስብሰባ ከትሩፋት ቤት ነው:: አዲሱ ቤቷ ከፖሊስ ጣቢያው አጠገብ በመሆኑ ብዙ ትኩረትና ጥርጣሬ እይደረግበትም ተብሎ ታስቧል:: አሁን የገባችበትን ቤት ቀበሌ እከራይቷት ነው:: በንጉሡ ጊዜ የአንድ መምህር ቤት ነበር:: ትርፍ ቤት በመሆኑ የደርግ መንግሥት ወርሶታል:: የመንግስት ሰራተኛ የሆነ ሁሉ እንደ እመጣጡና እመዘጋገቡ የሚከራይ የቀበሌ ቤት ያገኛል:: ምንጊዜም ቅድሚያው ግን ለባለሥልጣናቱ ነው:: ትሩፋት ቤቱን ይበልጥ የወደደችው ከሞላ ጎደል በሕቡዕ ለሚያካሂዱት ስብሰባ አመቺ መሆኑ ነበር:: ግቢው በለንሰልና በባህርዛፍ ግጥም ያለ ነው:: የአጋም ሽምጥ አጥር አለው:: በስተጓሮ በኩል በር ተሰርቶለታል:: ከጓሮው ውጭ ለጥ ያለ ሜዳ አለ:: ሜዳውን ሲወጡ ወደ ሀሙሲት ከተማ የሚያስገባው ጥርጊያ መንገድ ይገኛል:: ለዛሬ ስብሰባቸው ሁኔታዎችን አመቻችታለች:: ድልነሳና ራሔል እንዲሁም ሌሎች ታናናሽ እህቶቿ ሳሎን ብቅ እንዳይሉ ነግራቸዋለች:: ባትነግራቸውም በእንዲህ ዓይነት ጊዜ እነሱም ብቅ አይሉም::

ከሁሉም ቀድሞ የተገኘው ይነበብ ነበር:: የይነበብ ነገር ያስጨንቃታል:: እንግዳ ሆኖ በመንግሥት ሰራተኞች የውይይት መድረክ ላይ በአለተ እርብ ገና በሩ ላይ ብቅ ሲል ስታየው ነበር የደነገጠችው:: ያ ያኔ የተሰማት ሰሜት ዛሬም ድረስ ይፈታተናታል:: ልተውህ ብትለው እንኳ ሊተዋት አልቻለም:: ይረብሻታል:: እንዲህ እንደ አሁኑ





ብቻቸውን ሲሆኑ ደግሞ ከድርጅታዊ ግንኙነታቸው ባሻገር ሌላ ከአሁን በፊት ተሰምቷት የማያውቅ እንግዳ ስሜት ያስቸግራታል:: ለሰው ባትነግረውም ለራሷ ልትደብቀው አልቻለችም:: ቢቸግራት ለድርጅቷ ስነ-ስርዓት መገዛት እንዳለባት ደጋግማ ለራሷ ነግራለች:: ፍቅሩን መሳልሳ አለባዋለች:: ግን ይነበብ ጎልቶ ይመጣባታል:: በተለይ ከዚያ ከሀኪም ቤት ግንኙነታቸው ወዲህ ከሐሳቧ ልታወጣው አልቻለችም:: እንደውም ለራሷ ልትሸሽገው ያልቻለችው ነገር ይነበብ ላይ ብዙ የምትወዳቸው ነገሮች አግኝታበታለች:: እርጋታውን፣ አድማጭነቱን፣ ለሰው ያለውን አክብሮትና ቀና አመለካከቱን አድንቃ አታበቃም:: ኮራ ጀነን ያለውን ረጅም ቁመናውንም ቢሆን ትወድለታለች:: በተለይ— በተለይ ለድርጅቱ ያለው ፍቅርና የሥራ ትጋቱ ይገርማታል::

«እንደምን አመሸሽ ትሩፋት? ጓዶች አልመጡም እንዴ?» አላት:: ግቢው በር ላይ ቆማ መምጣታቸውን እየተጠባበቀች ነበር:: ወፈርና ሰሰለስ ብሎ የሚወርደው ድምጹ ሳይቀር ይረብሻት ጀምሯል::

«እግዚአብሔር ይመስገን:: እንደምን አመሽህ ይነበብ፤ ግባ ይመጣሉ::» አለች ወደ ጎን መንገድ እየለቀቀችለት ወደ ውስጥ ዘለቀ:: እሷ እዚያው በሩ ላይ ሆና የሌሎችን መምጣት ልትጠባበቅ ቆመች:: ዘመድኩን ተከተለ:: ቀስ ቀስ እያሉ አንድ ባንድ ቀሪዎቹ ይርጋና ብዙአየሁ መጡ:: ለብዙ ሰዓት ሲወያዩ ቆዩ:: ውይይታቸው ያተኮረው የደርግ መንግሥት ደጋፊ በሆኑትና በኢህአፓ አባሎች መካከል ቀሰ በቀስ እየታየ የመጣው ሆድና ጀርባ የመሆን አዝማሚያን በተመለከተ ነበር:: ምንም ቢሆን በእንበሳሜ ከተማና በአካባቢዋ የሚገኙ ጓዶች ሁሉ የተለየ አቋም ያላቸው ሰዎችን የማግለልና የጥላቻ ፊት ማሳየት እንደሌለባቸው ወሰኑ:: «ሙያ በልብ ነው» እንዲሉ ዋና ተልዕኳቸውንና ግባቸውን በሆዳቸው ይዘው ላይ ላዩን የነበረ የድሮ ጓደኝነታቸውን መቀጠሉ በሁለት መልኩ ጠቀሜታ እንዳለው ተነጋገሩ:: አንድም ድርጅታዊ ስራን እየሰሩ ለመቆየት፤ ሁለትም ከእነሱ አንዳንድ ጠቃሚ ኢንፎርሜሽኖችን ለማግኘት ሆደ ሰፊ መሆን እንደሚያስፈልግ ተማመኑ:: ግብታዊና ስሜታዊ መሆን በሕቡዕ ለምትንቀሳቀሰው ድርጅታቸው የከፋ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ በአስቸካይ በስራቸው የሚገኙ ሕዋሶች ሁሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉት ጥብቅ መልዕክት እንዲተላለፍ ወሰኑ::

ሁለተኛውና ብዙውን ሰዓት የወሰደባቸው ግን ከአባላት ከሚገኘው ወርሃዊ መዋጮ ሌላ በአካባቢው ለድርጅታቸው ማጠናከሪያ የሚሆን የገቢ ምንጭ እንዴት ማግኘት ይቻላል? የሚለው ነበር:: ከብዙ ውይይት በኋላ በእንበሳሜ ከተማ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ተብሎ የታሰበው የማታ ትምህርት መጀመር የሚለው ነበር:: በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ መማር ያልቻሉ ወገኖችን በመጠነኛ ከፍያ ማታ ማታ ማስተማር:: ይህን መርሀ ግብር ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደ ማለት ይሆናል:: ወገንን ከማይምነት አውጥቶ ለድርጅታቸውም ገቢን ማሰባሰብ:: የማታ ትምህርቱ ተፈቅዶ ከተከፈተ ጥቅሙ አላጠራጠራቸውም ለተፈጻሚነቱ ሀላፊነት የተጣለባት ደግሞ አስተማሪ በመሆኗ ትሩፋት

ነበረች፡፡ እነዚህን ሁለት ውሳኔዎችን አስተላልፈው ሲጨርሱ ጊዜው ገፍቶ አኩለ ሌሊት ሆኖ ነበር፡፡ የሰዓት እላፊ ገደብ የሚያበቃው ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ በመሆኑ በዚህ ሰዓት ማንም ወጥቶ የትም መሄድ አይችልም፡፡ ሁሉም በተቀመጡበት ጋደም ጋደም አሉ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ሌሊቱ በታውን ለቀጣዩ ቀን ለቀቀ፡፡ አንድ በአንድ ኢያሉ በተለያየ አቅጣጫ እየወጡ ሄዱ፡፡ ይነበብ በመጀመሪያ እንደ መምጣቱ መጀመርያ አልሄደም፡፡ ከሁሉም መጨረሻ ነበር የወጣው፡፡ ወጥቶ ሲሄድ ሲል

«ትሩፋት የተሰጠሽን ስራ ዛሬውኑ ጀምሪ፡፡ መጀመሪያ የትምህርት ቤታችሁን ዳይሬክተር ማሳመን ይኖርብሻል፡፡ የወዝሊግ አባል እንደ ሆነም እንዳትረሺ፡፡ ቃላቶችሽን መርጠሽ በጥንቃቄ ማናገር ይጠበቅብሻል፡፡ ከወረዳው አስተዳደር አካባቢ ያሉትን ሰዎች በማነጋገር በኩል እኔም ብሆን እረዳሻለሁ» ሲላት መስማማቷን የገለጸችለት በአንገት ንቅናቄ ብቻ ነበር፡፡ ረጅም ቁመናዉ ይበልጥ ገዝፎ እሷን ያሳጠራት መሰሏት አጠገቡ መሆኗ ምቾት ነሷት ነበር፡፡

ትምህርት ቤት በጠዋት ሄደች፡፡ ከርዕሰ መምህሩ ቢሮ ስትገባ ደሳለኝን አገኘችው፡፡ ግንኙነታቸው ባይገባትም አፍ ላፍ ገጥመው በተመሰጠ ሲያወሩ በመድረሷ ደነገጠች፡፡ ሰመመለስ ስትቃጣ

«ግቢ--ግቢ ትሩፋት-- ምነው ፈለግሽኝ? አላት ርዕሰ መምህሩ አቶ ጌትነት ከመቀመጫው እየተነሳ፡፡

«ይቅርታ! አቋረጥኳችሁ መሰል» አለች፡፡

«አይ ጨርሰናል፡፡ መግባት ትችያለሽ» ብሎ በሚስቅ ፊቱና ዐይኑ አስተውሎ አይቷት ወጥቶ ሄደ ደሳለኝ፡፡

«የሚሆን ከሆነ አንድ ነገር ላማከርህ ነበር ጓድ ጌትነት» አለች ትሩፋት፡፡ ለማያዊ ካኪ ለባሽን የሆነን ሁሉ «ጓድ» ብሎ መጥራት እንደ ግዴታ ነበር፡፡ እሷ ስለ እሱ አቋም ታውቃለች፡፡ እሱ ስለ እሷ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ እንዲሁ ግን ጥሩ አግባብ አላቸው፡፡ እንዴት መነገርና ማሳመን እንዳለባት በውስጧ አንሰላሰለች፡፡ «አይሆንም ባላለኝ» ስትል ተመኘች፡፡

«ምን ችግር አለ፡፡ ጉዳይሽን ልስማውና የሚሆን ከሆነ ይሆናል» አለ ጓድ ጌትነት፡፡

«እንደምታውቀው እዚህ አካባቢ መማር የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ ሁኔታው ስለ አልተመቻቸላቸው ግን በቀኑ የትምህርት ክፍለጊዜ ገብተው መማር አልቻሉም፡፡ በተለይ የቤት እመቤቶችንና የቤት ሰራተኞች፡፡ ማንበብና መጻፍ እንዲችሉ ብንረዳቸው ለአኛም ትልቅ የአገር ውለታ ይሆናል፡፡ እንዲሁም የመንግስትን የመሰረተ ትምህርት ፕሮግራም





ተግባራዊ ማድረግ ነው ብዬም አስባለሁ፡፡ ስለዚህ በትምህርት ቤታችን ውስጥ የማታ ትምህርት ፕሮግራም ቢከፈት ምን ይመስልሃል?» አለችው ለመልሱ እየጓጓች፡፡

«ትሩፋት ይሄ ጉዳይ እኮ አዲስ አይደለም፡፡ ከአሁን በፊት እኔ ራሴ ለወረዳው አስተዳደር የአዛኮ ኮሚቴ አንስቼው ነበር፡፡ እንደምታውቂው የማታ ትምህርት ለመስጠት መብራት ያስፈልጋል፡፡ መብራት ባለመኖሩ ምክንያት ነው የቀረው» አላት ውስጥ ድረስ ዘልቆ እየመረመራት፡፡

«እሱን አውቃለሁ፡፡ ሙከራህንም አደንቃለሁ፡፡ የምትቀበለው ከሆነ መፍትሄ ይሆናል ብዬ ያሰብኩትን ይዤ መጥቻለሁ፡፡ የቀኑን የትምህርት ክፍለ-ጊዜ ብናሸጋሽገው የፀሀይ ብርሀን ጠፍቶ ለዓይን ያዝ እስኪል ድረስ ለማስተማር ይረዳናል፡፡ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድን ብንጨምር ውጤቱ ቀላል ይሆንም» አለች አሁንም አለሳልሳ፡፡

«እንዳልሽው የሰዓት ሽግሽግ ብናደርግ ውጤታማ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ነገር ግን አሁንም አንድ ስጋት አለኝ፡፡ የትርፍ ጊዜ ሥራ ስለሆነ መምህራን ፈቃደኛ ይሆናሉ ለማለት ይከብደኛል» አላት የማመንታት ስሜት እየታየበት፡፡

«የማታ ተማሪዎቹ መጠነኛ ክፍያ እንዲከፍሉ ቢደረግና ለመምህራን ደግሞ መጠነኛ ጥቅም የሚያገኙ መሆኑ ቢነገራቸው ፈቃደኞች የሚሆኑ ይመስለኛል ጓድ ጌትነት፡፡»

«የቱን ያህል ክፍያ ማስከፈል እንችላለን ብለሽ ነው? የአካባቢውን ሰው አቅም የምታውቂው ነው» አለ ጓድ ጌትነት፡፡

«መቼውም ከባዶ ሳይሻል አይቀርም፡፡ ዋናው ጥቅም ደግሞ ወገን መማሩ ነው፡፡» አለች ትሩፋት ጨርሶ እንዳይዘጋባት እየሰጋች፡፡

«እንጃ! እንደሱም ሆኖ ፈቃደኛ መምህራን የምናገኝ አይመስለኝም፡፡»

«ፈቃደኛ መምህራንን ካላገኘን ደግሞ በከተማው ውስጥ የሚገኙት ወጣቶች እንዲተባበሩን መጠየቁ ሌላ አማራጭ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ በዚያ ላይ ወጣቶቹ ትንሽ ሳንቲም ካገኙ ፈቃደኞች ይሆናሉ የሚል እምነት አለኝ» አለች፡፡ የሚያቀርባቸውን የማፍረሻ ቀዳዳዎች ሁሉ እየደፈነች፡፡

«ትሩፋት ያቀረብሻቸው የመፍትሔ ሐሳቦች ሁሉ ጥሩ- በጣም ጥሩ ናቸው፡፡ እንደ ነገርኩሽ ከአሁን በፊት እኔም የበላይ አካሎችን አነጋግሬበት ነበር፡፡ የሚሆን ከሆነ ጉዳዩን እንደ ገና እቀሰቅሰዋለሁ፡፡ እንደምታውቂው ያለበላይ አካል ፈቃድ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር መልካም ምኞት ብቻ ምንም ነገር መስራት አይቻልም፡፡ ለወረዳው አስተዳደር ጉዳዩን አሳውቄ የሚሰጠኝን መልስ እነግርሻለሁ፡፡ የሥራ ተነሳሽነትሽና ሳይማር

ያስተማረንን ወገናችን ለማስተማር ያሳየሽውን በጎ ፈቃድ አደንቃለሁ:: አመሰግንሻለሁ» አላት::

አቶ ጌትነት የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ራሱ ሙገሳ ሊያገኝበት ስለፈለገ የበላይ አለቆችን ሁሉ አሳምኖ የማታ ትምህርቱ ተከፈተ:: ከፍያው አነስተኛ በመሆኑ በፍላጎት የሚያስተምሩት እነ ትሩፋት ብቻ ሆኑ:: ለተወሰነ ጊዜ ደህና ተከታታይ የማታ ተማሪ ተገኝቶ ነበር:: ገንዘቡም ተሰባስቦ ለድርጅታቸው ማጠናከሪያ እንዲውል አድርገዋል:: እያደር ግን ቀሪ እየበዛ የሚማረው ሰው ቁጥር እየተመናመነ ሄደ:: ያ ዓመት ባሉት ተማሪዎች እንደ ምንም አለቀ:: ለመጭው ዓመት ግን በዚህ አያያዝ የሚቀጥል አይመስልም::

*****

አንድ ቅዳሜ ቀን አርባተንሳ የሚኖረው የትሩፋት የአጎቷ ልጅ በጧት መጣ:: ወሰን ይባላል:: ገና አፍላ ጎረምሳ ቢሆንም ጠንካራ ገበሬ በመሆኑ በአካባቢው ኗሪ ሁሉ ይወደዳል-- ይከበራል:: ከአባቱና ከእያቱ ጎን ጎጆ ወጥቶ አንድ ልጅ ወልዷል:: የአርባተንሳ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ጸሐፊ ነው:: በእንበሳሜ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምሮ ነበር:: በለንቅ ተመላልሶ መማር ሲሰለቸው አቋርጦ ወደ ግብርናው ገባ::

ይነበብ በገበሬ አደራጅነቱ-— ወሰን በገበሬ ማህበር ጸሐፊነቱ ይተዋወቃሉ:: በኋላም በይነበብ አማካኝነት በሕዋስ ደረጃ ተመልምሎ ኢሕአፓን የተቀላቀለ ጠንካራ ጓድ ነው:: ታስሮ እሳር መከራውን ሲያይ እንኳን «ቃል-- ቃል ነው:: ቃል አይበላም:: ማተብ አይበጠስም» ብሎ በጽናት የቆመ የገበሬ ጓድ ነው:: እንደ እሱ በኢሕአፓ አባልነት የተጠረጠሩ ገበሬዎች እንበሳሜ ታስረው ብዙ ሳይቆዩ ተለቀዋል:: ወሰን ግን በከፍተኛ ደረጃ በመጠርጠሩ ከእንበሳሜ ፖሊስ ጣቢያ ደብረታቦር-- ከደብረታቦር ጎንደር ባታ ወይኒቤት ድረስ ተነድቷል:: አይሆኑ ሆኖ ተደብድቧል:: እሱ ግን «ምንም አላውቅም» በሚለው አቋሙ የጸና ኃይለኛ የገበሬ ታጋይ ነው:: በለስ ቀንቶት ነው ከዚያ ዘመን አልቂት የተረፈው:: መሬቱን ሁሉ ተነጥቆ በእገሩ ላይ እንደ ባይተዋር ቢሆንም እስከ ዛሬ በሕይወት አለ:: ሁሉንም እየታዘበ::

«ወሰን እንደምን አደርክ? ምነው በዚህ በጧት?» አለችው ትሩፋት:: ገጽታው ላይ የተመለከተችው ነገር አላማራትም ::

«ዛሬ እኮ የጌቶች ሙት ዓመት ነው:: 'ታባ ጸሀይ እንዳይበላቸው በጧት ይዘሃቸውና' ብላ ልካኝ ልወስዳችሁ ነው የመጣሁ» አላት ዐይኗን እየሸሸ:: «ጌቶች» ያላቸው የእሱንና የትትሩፋት የሴት እያት አባት ነው:: ፊታውራሪ አሊጋዝ ይመር ይባሉ ነበር:: ትሩፋት ስንት የሚያሳስብ ጉዳይ እያላት ከሞቱ ስንትና ስንት ዓመት ለሆናቸው «ጌቶች» ስትጨነቅ





ባልተገኘችም ነበር:: እያቷ በአካባቢው አጠራር እሚታዋ እሙሀይ እየለች ግን እንዲቀየሟት አትፈልግም::

«ሽማግሌና አሮጊት አዝኖ ወደ መቃብር መውረድ የለበትም:: ቢቻል ፈቃዳቸውን መሙላት ጥሩ ነው:: ያም ባይሆን ደስ እንዲላቸው የአቅምን መሞከር ነው» ትላለች ትሩፋት:: ከእያቷ መንደር መሄድ ደግሞ በብዙ ነገር ደስ ይላታል:: ዛሬ ወሰን ባይመጣ ኖሮ ግን የጌቶች ሙት ዓመት መሆኑን ብታውቅ እንኳ አትሄድም ነበር:: እሁድ የማይቀረው ስብሰባ አለባት::

እያቷ በአካባቢው የተከበሩ መነኩሴ ናቸው:: የእውቁ አርበኛ የፊታውራሪ አሊጋዝ ይመር ልጅ እሙሀይ እየለች አሊጋዝ:: ሳር ቤት ውስጥ ይኑሩ እንጂ ምርጉና የአበት ልቅልቁ የከተማን እልባሌ ቆርቆሮ ቤትና ቀለም ያሰንቃል :: በጉርጅ በጉርጅ ተከፍሎ መኝታ ቤትና ማጀት አለው:: የቤቱ ውጋግራዎች እንኳ ቀጥ ቀጥ ማለታቸው ተመርጠው እንደ ተዘጋጁ ያስታውቃሉ:: ዙሪያውን የተሰሩት መደቦች በነጭ አጎዛ አጊጠው ልዩ መስህብ አላቸው:: ሲገቡ በስተግራ በኩል የቤቱን አንድ ጥግ ይዞ በከብ ጭቃ የተሰራው ምድጃ አመዱ ወለሉ ላይ ለዐመል ብን ብሎ አይደርስም:: የትሩፋት እያት ቤት ሁሉም ነገር በመልክ በመልኩ የተቀመጠ ነው:: ሁሉም ነገር የድሮ ባህሉን እንደ ያዘ ይታያል:: ደስ ይላል:: ዛሬ ቀኑ ቅዳሜ ነው:: መደበኛ ስራዋ ዝግ ነው:: እንዳጋጣሚ ደግሞ ቀበሌም ስብሰባ አልጠራም:: እያቷ ቅር ከሚላቸው ዛሬ ብትሄድ ነገ ማታ ያለጥርጥር መመለስ ትችላለች:: ድልነሳ ከጓደኞቹ ጋር ሐሙሲት ትናንት እንደ ሄደ ነው:: እሷና ራሔል መሔድ ይችላሉ:: ሌሎቹ እህቶቿ ከሠራተኛዋ ጋር ይቆያሉ::

«ግባ እንጂ ታዲያ ወሰን ቁርስ በልተን እንሄዳለን» አለች ትሩፋት::

«ኧረገኝ ያንቺ ነገር! ከድግሰ ላይ መስሎኝ የመጣሁ:: የግዳስ ከግብርናው መስሪያ ቤት ደርሼ እስትመጣ እናንተ ተዘገጃጅታችሁ ጠብቁኝ::» ብሎ መልሷን ሳይጠብቅ ከፊቷ ሄደ:: እንዳለውም ግብርና ጽሕፈት ቤት ደርሶ ከይነበብ ጋር ተነጋግሮ ቶሎ ተመለሰ:: ትሩፋትና ራሔል እጥብቀው ቢለምኑትም አቤት አልገባም ብሎ በውጭ እንዳለ ለጉዞ ተነሱ:: መንገድ ላይ ወሰን እንደ ሁልጊዜው ብዙ አልተጫወተም:: እንደ ቆዘመ ዝም ብሎ ነበር የሚጓዘው::

«ታባ ግን ሳሉ ተሸሏታል ወሰን? ያ የላኩላት መድሃኒት ትንሽ አስታግሶላት ይሆን?» ጠየቀች ትሩፋት:: ሐኪም ፍስሃን አማክራ የላከችላቸው የሳል መድሀኒት ነበር::

«እንግዲህ ቢሻላት ይሆናል እንጂ የአባቷን ሙት ዓመት ልታወጣ የተነሳችው» አላት እንደ እቀረቀረ:: ዱላዉን ከሁለቱ ትከሻው ላይ እጋድሞ የያዘበት እጁ እንደ እሞራ ክንፍ ተዘርግቷል::

«ለእሚታቸው ሙት ዓመት ነው እንዴ ታትየና እየዋ መጥተው የሰነበቱት?» አለች ራሔል፡፡ እናታቸው ከሲፋጥራ የእናታቸው ታላቅ ወንድም ደግሞ ከገናበጋ ጊዮርጊስ ከመጡ ሳምንት ሆኗቸዋል፡፡ እናታቸው ሲመለሱ በትሩፋት በኩል እንደሚያልፉና እይተዋቸው እንደሚሄዱ መልዕክት ልከውባቸው ነበር፡፡

«በየዓመቱ ቀርተውም አያውቁ» አለ እሁንም እንደ ቆዘመ፡፡ ከእንበሳሜ አርባተንሳ ድረስ በእግር ጉዞ ሁለት ሰዓት ያህል ይወስዳል፡፡ ትሩፋትና ራሔል የሆነ ያልሆነውን እያነሱ ይጫወታሉ፡፡ ወሰን እንደ ሌላው ጊዜ ብዙ ባይጫወትም እልፎ እልፎ መነጋገሩን አልተወም፡፡ ትሩፋትና ራሔል ዝምታውና ቁዘማው የድካም ነበር የመሰላቸው፡፡

ከአያታቸው ቤት ሲደርሱ ተዳፋት መንገዱን ወጥተው ዳገቷ ላይ ብቅ ሲሉ ሰፈሩ ሁሉ በሰው ተጥለቅልቋል፡፡

«ኢታባ እናቴ! ኢታባ መግቢያዬ! ኢታባ እጉራሼ! ኢታባ እመቤቴ!» እያለ ወሰን ጩኸቱን ለቀቀው፡፡ ትሩፋትና ራሔል በወሰን ድንገተኛ ጩኸት ደንግጠው ሰፈር ሲደርሱ እናታቸው ያዙኝ ልቀቁኝ ይላሉ፡፡ የኖረ የወንድ የቅድመ አያታቸውን ሙት አመት ለመዘከር የሄዱት ትሩፋትና ራሔል ትኩስ ለቅሶ ላይ ደረሱ፡፡ ወሰን ሊወስዳቸው ሲመጣ ትንሽ እንኳ ጥርጣሬ አላደረባቸውም ነበር፡፡ እንግዲያው አያታቸው እሙሀይ እየለች ኃይለኛ ሳል ታመው መሰንበታቸውን ያውቃሉ፡፡ ለሞት ያበቃቸዋል ብለው ግን አልጠረጠሩም ነበር፡፡

ከዚያ ሁሉ ጋቢ ለባሽ ባላገር እንድ ከተመኛ ሰው--ከሰው ሁሉ ጋር እየተጋፋ መጥቶ ከጎኗ ሲቆም ትሩፋት «ይነበብ ይሆናል» ብላ እልገመተችም ነበር፡፡

«ይነበብ እዚህ ምን ትሰራለህ?» በመገርም ነበር ጠየቀችው፡፡

«ለመሰከ ሰራ መጥቼ ነበር፡፡ እዚህ ደግሞ እንዲህ ሆኗል፡፡ እግዜር ያጥናችሁ» አለ መንተፍረቱን፡፡

ወሰን እነ ትሩፋትን ሊወስድ የመጣ ጧት ተዘገጃጅተው እስኪ ጠብቁት ድረስ ቀጥታውን ወደ ግብርና መሰሪያ ቤት ይሄዳል፡፡ በዚያው እለት የቀበሌ ገበሬ ማኅበሩ ሰብሰባ ነበር፡፡ ሁልጊዜ በይፋ የሚካሄደው የገበሬዎቹ ሰብሰባ ካበቃ በኋላ ይነበብ ድርጅታዊ ስራውንም በዚያው ያከናውናል፡፡ ወሰንና ሌሎች እራት አባላትም ይህንን ያውቃሉ፡፡ ተራ ወሬ የሚያወሩ ይመስሉና ወደ ኋላ ይቀራሉ፡፡ ሁሉም ጥርግ ብሎ መሄዱን ሲያውቁ ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡ በዛሬው ቀን ግን የወሰን እያት እርፈዋል፡፡ ሁለቱም ሰብሰባዎች ሊካሄዱ አይችሉም፡፡ ይነበብ እርባተንሳ ድረስ ሄዶ በከንቱ መድከም የለበትም፡፡ ለዚህ ነበር ወሰን ሲገሰግስ ወደ ግብርና መሰሪያ ቤት የሄደው፡፡



ያልተቋጨ ጉዞ

«ጋሼ ይነበብ እንደምን አደርከ?» አለ ወሰን ከወገቡ ወረድ እያለና በእንድ እጁ ዱላውን መሬት ላይ እያጋደመ፡፡

«ደህና አደርከ ወሰን፡፡ ዛሬ ከእናንተ ገበሬ ማኅበር እባላት ጋር ሰብሰባ ነበረን እኮ ይህንን ሰነድ ይዤ መውጣቴ ነበር፡፡ ምነው በደህና ?» አለው ለሰላምታ የዘረጋውን እጁን ቀልጠፍ ብሎ እየጨበጠውና በቀይ ከላስር የያዘውን ዶሴ እያሳየው፡፡

«የእኔም እመጣጥ እጉል እንዳትደከም ከመውጣትህ በፊት ላግኝህ ብዬ ነው፡፡ እክል ኢጋጥምኛል» አለ ወሰን እንገቱን ደፍቶ፡፡

«የምን እከል? በገበሬ ማኅበሩ ውስጥ ችግር ተፈጠረ እንዴ?» አለ ይነበብ ደንገጥ ብሎ፡፡

«ኧረ በገበሬ ማህበሩ ውስጥ የተፈጠረ ችግር የለም ጋሼ! እሱ አያሳስብህ፡፡ በቤተሰብ የመጣ እክል ነው፡፡ ኢታባን ታውቃት የለ እሚታዬን እረፈች!» ሲለው ወሰን እንባው ኮለል ብሎ ወረደ፡፡ በጋቢው ጠረግ አደረው «እነ ትሩፋትን ልወስድ ነው በጧት ሰገሰግስ የመጣሁ፡፡ የእንድ እሚታ ልጆች እኮ ነን፡፡ ተዘገጃጅተው እስቲጨርሱ ድረስ እኔ ወዳንተ መጣሁ፡፡ እንኳም ሳትወጣ ደረሰኩብህ» አለ ወሰን ከመውጣቱ በፊት ሰለ እገኘው ደስ እያለው፡፡ እነ ትሩፋት ከመድረሳቸው በፊት ይነበብ ለቅሶው ላይ ነበር፡፡

«እንደምታየው ገበሬው ሁሉ እዚህ ነው ያለው፡፡ ሥራ መሥራት የምትችል አይመስለኝም፡፡ እንዳይመሽብህ በጊዜ ብትሄድ ይሻላል ይነበብ» አለች ትሩፋት፡፡

«ግድ የለም፡፡ ከመጣሁ አይቀር ቀብር ላይ ብገኝ ደስ ይለኛል» አላት ቀለል አድርጎ፡፡ ወሰን ጋር በገበሬ ቀበሌ ማኅበር ጸሐፊነቱ ባላቸው ግንኙነት ምክንያት እንደ መጣ ነበር ሌላው ሰው የተገነዘበው፡፡ ከቀብር በኋላም ይነበብ እዚያው ቆየ፡፡ ትሩፋት የሐኪም ቤቱ ሁኔታ ትውስ አላት፡፡ ያኔም እንዳይከተላት ያላደረገችው ጥረት እልነበረም፤ ግን ሳይቀበላት ቀረ፡፡ ይግረምሽ ብሎ እብሯት እቤቷ ድረስ መጣ፡፡ ድርቅ–ፍጥጥ ማለቱ እየገረማት ሊጫወት እምሽቶ ነበር የሄደው፡፡ የዛሬ ሁኔታው ደግሞ እልገባትም፡፡ «እድራለሁ እንዳይል ብቻ» አለች በልቧ፡፡ ሰታየው ደግሞ የሚሄድ አይመሰልም፡፡

«ይነበብ እየመሸ እኮ ነው፡፡ ከተማ ሰትገባ የሰዓት እላፊው ገደብ እንዳይዝህና እንዳትቸገር» አለችው ከቀብር መልስ፡፡ እነጋገሯ የማስታወስ ቢመስልም እንዲያድር እለመፈለጓንም ጭምር ይገልጻል፡፡

«እይ! ከአሁን በኋላማ እንዴት ይኬዳል ብለሽ ነው፡፡» ቁርጧን ነገራት፡፡ «መንገዱ ያን ያህል ሩቅ ባይሆንም ተዳፋት ሰለሚበዛበት ከመሸ በኋላ ከብድ ይላል፤ በተለይ ብቻን ሊሆኑ እንደ እየሽው የገብርኤል ሳር ደግሞ ከሰው ቁመት በላይ ሆኖ እድጓል፡፡ በምሽት ጢሻ ውስጥ ተደብቆ የሚጠብቀው አይታወቅም፡፡ የሚተናኮል እውሬም እይጠፋውም»

አላት ፍርጥም ብሎ:: ምንም አላለችም:: ምንም ብትል ለውጥ እንደማታመጣ ገብቷታል::

ትሩፋት፣ ራሔልና ይነበብ እንደ ከተመኛ ሰው ተቆጥረው እንክብካቤ አልጎደለባቸውም:: ከወሰን ቤት መኝታ ተዘጋጀላቸው:: ወለል ላይ ሳር ተጎዝጉዞ ሰፌ ላምነት ተነጠፈላቸው:: ጋቢና የወሰን ብርድልብስ ተሰጣቸው:: የዋሉበትን ልብስ ሳያወልቁ ተኙ:: ትሩፋትና ይነበብ አብረው ሲያድሩ ይህ የመጀመሪያ ጊዜያቸው አይደለም:: በቡድን ጥናታቸውና ውይይታቸው ጊዜ ወጥቶ ለመሄድ ካልተመቸ በዚያው ማደር ድርጅታዊ ልምድ ነው:: የዛሬውን አዳር ግን በዚያ መልኩ አላየችውም:: እዚህ ለቅሶ ላይ የመገኘቱ ነገር ለእሷ ወይስ ለወሰን ብሎ መሆኑ ሳይለይላት እንዲሁ ሲገርማት አደረ:: ራሔል ለወሰን ብሎ እንደ መጣ አሰበች:: ጧት ከቁርስ በኋላ ተሰናብቶ ሄደ:: ትሩፋትም የማይቀረው ስብሰባ ትንሽ ቆይታ መከተሏ አልቀረም::

******

ትሩፋት በጧት ተነስታ ወደ ስራዋ ስትሄድ ይነበብ ጋር መንገድ ላይ ተገናኙ:: ስታየው ሰውነቷን ርብሽ-- ድንግጥ የሚያደርጋት ነገር ብሶባታል:: ተናደደች:: በጣም ተናደደች:: ፍቅሩን አሰበችው:: ቃል ገብታለታለች:: ቃል አይታጠፍም:: ቃል የሕሊና ዕዳ ነው ያለው ማን ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ አጥብቆ ያዛል:: ልጅ እያለች ለአባባ መሳይ ሲታነብላቸው ሀቀኛና እውነተኛ መሆን በፈጣሪ ዘንድም የተወደደ መሆኑን አጥብቀው ነግረዋታል:: ድርጅቷ ኢሕአፓ ትልቁ መማሪያዋ የቃል ጽናት ነው:: ለዓላማ መሞት:: ጓዶች ሁሉ ለዓላማ ሲሉ የሚከፍሉት መስዋእትነት ከቃል ሌላ ምንም ማሰሪያ የለውም:: ጓዶችን ላለማጋለጥ--ድርጅታዊ ሚሥጢርን እንደ ጠበቁ ራስን እስከ ሞት አሳልፎ መስጠት የቃል እምነት እንጂ የሰነድ ውል የለውም:: ቃል ከቡር ነው:: ለፍቅሩ የገባችለትን ቃል:: የእናቷን የአደራ ቃል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የድርጅቷን የሥነ-ስርዓት ደንብ መጠበቅ ይኖርባታል:: በጓዶች መካከል ጾታዊ ግንኙነት አይፈቀድም:: ግን እንጃ! ከቁጥጥሯ ውጭ እየሆነ ተቸግራለች:: አንዳንድ ጊዜ አበራሽ የተናገረችው እውነት እንደ ሆነ ታስባለች::

«ፍቅር ከቁጥጥሬ ውጭ ሆኖ ጉድ ሊደርገኝ ይሆን?» ትልና «አይደረግም! በፍጹም መሆን የለበትም! ልብሴን ጥዬ ካላበድኩ በስተቀር ሦስት ቃል አልበላም!---ሦስት ቃል አላፈርስም! አደራ አልበላም!» ውስጧን ታስጠነቅቃለች:: አንዳንዴ ደግሞ ራሷን ትመረምራለች---ሀቁ ፊት ለፊት ይጋፈጣታል::

«ግን እኮ ይህን ልጅ መጀመርያ ያየሁት ቀን ነው የደነገጥኩት:: ምን ነክቶኝ ይሆን? እውነት ግን ፍቅር ሊይዘኝ ይሆን?» ትላለች ደጋግማ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለፍቅሩ ያላትን





ስሜትና ለይነበብ ያላትን ስሜት ለማወዳደር ትሞክራለች:: ለይነበብ ያላት ስሜት የተለየ ነው:: ከልቧ ፈንቅሏት ሲወጣ ይሰማታል::

«እንደምን አደርሽ ትሩፌ» አላት ለሰላምታ እጁን እየዘረጋ ስሟን በቁልምጫ ሲጠራት የባሰውን ተረበሸች:: ለሰላምታ የዘረጋውን እጁን መጨበጥ ነበረባት:: እጇ ከረጃጅም እጣቶቹ መሀል ዋለ:: በዚህ ሙቀት በሌለበት ማለዳ እንዳያልባት ሰጋች:: ይባስ ብሎ ቆም ብሎ ወሬ መጀመሩ::

«የማስተማር ሥራ እንዴት ይዞሻል?» አላት:: በዚህ ሰዓት መጠየቅ የሌለበት ጥያቄ በመሆኑ አናደዳት::

«ጥሩ ነው፤ ምንም አይልም» አለችው በግዴለሽነት::

«ላናግርሽ የምፈልገው ጉዳይ አለኝ» አላት ቀጥሎ:: አነጋገሩ ፍርጥም ያለ ነበር::

«አልችልም:: ሰዓት ደርሷል:: መጀመርያው ክፍለ ጊዜ ላይ ክፍል አለኝ» አለችው እሷም ፍርጥም ብላ::

«አሁን ባይሆንም:: መነጋገር ግን ይኖርብናል:: ማታ እቤትሽ እመጣለሁ» ብሏት መልሷን ሳይጠብቅ በችኮላ ሄደ::

ትሩፋት ስታስተምር ሁሉ ይነበብን ከሐሳቧ ልታወጣው አልቻለችም:: የፈለጋት ለድርጅታዊ ሥራ እንዳልሆነ ገብቷታል:: ስታየው ዐይነ ውሃው አላማራትም:: የራሷን ስሜትም ፈርታዋለች:: ባሰበችው ቁጥር ልቧ እየዋለለ ቁርጥ ያለ አቋም ሳትይዝ ነው የዋለችው:: የማስተማር ሥራ አልቆ ወደ ቤቷ ለመሄድ ስትነሳ መንገድ ላይ ብታገኘው በወደደች:: እቤቷ እንዲመጣ በፍጹም አትፈልግም:: እሷ ራሷ ከቤት ላለመግባት ፈልጋ ነበር:: ምን ዋጋ አለው? ልጁ እንዲህ በዋዛ የሚለቃት አይደለም:: ዝም ብላ ቀጥታውን ወደ ቤቷ ሄደች::

«የራሱ ጉዳይ ይምጣና የሚለውን ብሎ ይሂድ» አለች ለራሷ «እኔ ግን መጠንከር ይኖርብኛል:: ምንም ቢሆን ፊት መስጠት አይኖርብኝም» ስትል ራሷን አስጠነቀቀች:: ልቧ ግን ከውስጥ እየከዳቻት ነበር::

ይነበብ አልቀረም:: መሽትሽት ሲል መጣ:: የትሩፋት ቤት ሳሎኑ ጠበብ ቢልም አንድ የገመድ ሶፋ፣ አንድ የእንግዳ አልጋና አራት ወንበሮች ያሉት አነስተኛ የምግብ ጠረጴዛ ይዟል:: የገመድ ሶፋዉ የቤቱ ባለቤት ንብረት ነበር:: የሚገባው ሰው ሁሉ የጥጥ ትራሱንና ጨርቁን እየቀየረ ይጠቀምበታል:: ትሩፋትም ፈካ ያለ ቢጫ አበባ የበዛበት ጨርቅ ገዝታ አልብሳዋለች::

የግቢውን ቆርቆሮ በር የከፈተችለት ራሷ ነበረች:: በዚያ ሰዓት ሌላ ሰው እንደማይመጣ እርግጠኛ ነበረች::

«እንደምን አመሸሽ» ሲላት መልሱን የሰጠችው ተኮሳትራ ነበር:: እቤት ገብተው ሁለቱም በትይዩ ተቀመጡ:: ፈላጊው እሱ በመሆኑ ጉዳዩን መጀመር ያለበት ራሱ ነው:: ዝም ብላ ጠበቀችው::

«ጠነከራችሁ:: እናትሽ በረቱ» አላት ለቅሶውን አስታውሶ::

«ስንት ወጣት በሚያልቅበት በዚህ ዘመን ታሞና አድሜ ጠግቦ መሞት ጌጥ ነው አባከህ!» ለማጽናናት ያሰውን ነገር አጣጣለችበት::

«እናትሽ ግን በጣም አዝነው ነበር::»

«ለእሷማ እናቷ አይደለች:: ከዘመኑ ጋር ሳሰባት ነው እንጂ እኔም እኮ አላሳዝነችኝም ማለት አይደለም:: ሌላው ቢቀር ከአራት እያት አሁን ሁለት ብቻ ይቀሩናል:: ይኸ እንኳን በራሱ ጎዶሎ ነገር መኖሩን ያመለክታል::» ድምጿ ሰሰለሰ ማለት ጀመረ::

«ምንም የሌለን ምን እንበል?» አላት::

«ከሞት የሚቀር የለም:: ሁሉም ግን የየራሱ ትዝታ አለው:: በተለይ ለሴት እያቶቼ ብዙ ትዝታ አለኝ» አለች ተከዝ ብላ::

«እስኪ የእኚህዋን ሴት እያትሽን ትዝታ ንገሪኝ:: አገር የመሰከረላቸው ቆንጆ ናቸው:: ቁንጅናቸውን እንኳ እኔም እመሰከራለሁ:: እድሜ ያላጎበጠው ቀጭን መለሎ ቁመናቸው በስፖርት የማይገኝ ነበር:: አሳቸውም በቁንጅናቸው ሳይኮሩ አይቀሩም ብዬ እገምታለሁ:: ከባሎቻቸው ጋር እረግተው የማይቀመጡት በዚሁ በቁንጅናቸው እየኮሩ ነው ይባላል:: የእናትሽን እባት ሳይቀር የፈቷቸው አጭር በመሆናቸው ንቀዋቸው መሆኑን የአርባተንሳ ሰው ሳይደብቅ ያወራል» አላት::

«ምን የቀረህ ታሪክ አለ? ከኔ ይበልጥ አንተ እውቀኸዋል:: እኔ እምለው ግን ይህን ሁሉ የሰው ታሪክ ስታጠና ሥራ አትሰራም ማለት ነው? መንግሥት አምኖ ቢያሰቀምጥህ እንዲህ ቀልደህበታል ለካ! ገበሬውን ሁሉ በማኅበር አደራጅተህ ያምራቾች የኅብረት ሰራ ማኅበር እንድታቋቁምለት መስሎኝ የቀጠረህ? እንደምሰማህ ከሆነ ግን ሥራ እየሠራህ አይደልም:: የሰው ታሪክ ስታጠና የምትውል ነው የሚመሰለው:: ይህንን አሻጥርህን ለመንግሥት ጠቆሜ ባላሰይዝህ እኔ አይደለሁም» አለች ፈገግ እያለች::





«የደራ ወረዳንና የፎገራ ወረዳ ገበሬዎች ሁሉ ለመንግሥት መመሪያና ደንብ ሰጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ እየጣርኩ ነው:: ጉማራ ላይ የትኑሯን የመሰለ የተጠናከረ የገበሬዎች የአምራቾች ሥራ ማኅበር መስርቼለታለሁ:: ለመንግሥት ታማኝ አገልጋይ እንዲሆኑ በደንብ አደራጅቼለታለሁ:: ለዚህም ከአንቺ በላይ ምስክር አልጠራም» አላትና ተሳሳቁ::

ዝም ብለው የሆነ ያልሆነውን እያወሩ ቆዩ:: እድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ስለ አሳለፈው ሕይወቱ አወራላት:: በአዋሳ ከተማ የማኅበራዊ ኑሮ እድገት ተቋም የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለ እንደ ዘመተ-- ምድብ ጣቢያውም በዚያው አዋሳ ዙርያ እንደ ነበር--- በተፈጠረው የፖለቲካ ልዩነት ተጠርጥሮ መንግሥት አስሮት እንደ ነበር -- አስር ቤት እያለ ሰለ ደረሰበት ስቃይና መከራ ተረከላት:: ከእስር ከተፈታ በኋላ ዘመቻውን ጥሎ አዲስ አበባ ወደ ቤተሰቦቹ መመለሱን-- በኋላም በመንግሥት ፈቃድ ሁሉም ተማሪ ወደየተቋሙ ገብቶ እንዲማር ሲደረግ እሱም ተመልሶ ትምህርቱን ማጠናቀቁንና እዚህ የመጣውም ለከፍተኛ ድርጅታዊ ተልእኮ መሆኑን ብዙ ብዙ ተረከላት:: በጽሞና አዳመጠችው::

ትሩፋት ጊዜው እየመሸ የሰዓት እላፊው ገደብ እየደረሰ መሆኑን ለማሳወቅ አስር ጊዜ ሰዓቷን ብትመለከትም ይነበብ ተረጋግቶ ነበር የሚጫወተው::

«ዛሬ ወደ አንቺ ያስመጣኝ ይህንን ያለፈ ታሪክ ልተርከልሽ እንዳልሆነ መቼም ይገባሻል» አለና ትኩር ብሎ ተመለከታት::

«እንዴት ሊገባኝ ይችላል? ጠንቋይ ትቀልባለች እሉህ?»

«ከልብ የበለጠ ምን ጠንቋይ አለ ትሩፋ? ልቦቻችን ከተጠናቀሱ ቆይተዋል» አላት ፈገግ ብሎ::

«የምን መጠናቆል አመጣህብኝ ደግሞ!? የሚገባኝ ሀቅ ቢኖር በዚህ ሰዓት ያለምክንያት ከድርጅታችን ደንብና ስርዓት ውጭ መገናኘታችን ትክክል ያለመሆኑ ብቻ ነው:: አደጋም ያስከትላል ይነበብ::»

«እውቃለሁ ትሩፋ! ይህንን ለእኔ መንገር አይጠበቅብሽም::» አላት አሁንም ዐይኑን አላዩዋ ላይ ሳይነቅል:: ስሟን በቁልምጫ በጠራት ቁጥር ደግሞ ልቧ ከውስጥ እየከዳቻት ታስቸግራት ጀመር::

«ካወቅኸው ታድያ ለድርጅታችን ስነ-ስርዓት ተገዢ አለመሆንህ ነው?»

«አልቻልኩም ትሩፋት-- አልቻልኩም፡፡ እንዲህ በቀላሉ እረታለሁ ብዬ አንድም ቀን አስቤ አላውቅም ነበር፡፡ አሁን ግን አልቻልኩም፡፡ ምንም ማድረግ አልችልም? ከአቅሜ በላይ ሆኗል» አሳት ዐይን ዐይኗን እያየ፡፡

«ለምን እንደምታወራ አልገባኝም ይነበብ?»

«ገብቶሻል ትሩፋት፤ ገብቶሻል፡፡ እንዴውም ከገባሽ ቆይቷል፡፡»

«እንዴ! ምኑ ነው ከገባኝ የቆየው?»

«ጊዜው አልፏል፡፡ ብንደባበቅና ብንወሻሽ ምንም ጥቅም የለውም፡፡ ሁለታችንም ካልፈለግነው ፈተና ውስጥ ወድቀናል፡፡»

«የምን ፈተና ነው የምታወራው ይነበብ?»

«ፍቅር አልያዘኝም ለማለት ከሆነ እኔን ይዞኛል በቃ!! አሸንፎኛል፡፡ ፍቅር ጉድ አድርጎኛል ትሩፋት!»

«ሊሆን አይችልም ይነበብ፡፡ የድርጅታችንን ዲሲፕሊን ሊገዛህ ይገባል፡፡ አይሆንም! መሆን የለበትም!» ጮኸች! መኝታ ቤት ያሉት እነ ራሔል ሳይሰሟት አይቀሩም፡፡

«ሆኗል ትሩፋት! ሆኗል! ለብዙ ቀን-- ለብዙ ሌሊት ስሜቴን አልሰማህም አሳዳምጥህም ብዬ ሰሸሸው ቆየሁ፡፡ እዚህ እንበሳሜ ድረስ የመጣሁበትን ዓላማና ድርጅቴን እንደ ከዳሁ እንደሚቆጠር ለራሴ እየነገርኩ ላሳምነው ሞከርኩ፡፡ ግን አልቻልኩም፡፡ በዚህ በተፋፋመ የትግል ወቅት በፍቅር መውደቅ ራስን እጅግ መውደድ መሆኑ ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም፡፡ ግን ምን ላድርግ? ከቁጥጥሬ ውጭ በሆነ አንድ ባልገባኝ ምትሀታዊ ኃይል ሰር ውያለሁ!» አሳት ፍርጥም ብሎ፡፡

«ይነበብ አንድ ያላወቅኸው ነገር አለ» አለች ትሩፋት አቅሟ ሁሉ ድክም እያለ፡፡

«ላውቀው አልፈልግም ትሩፌ፡፡ ከእንግዲህ ይህንን ከሰተት ሊያስለውጥ የሚችል ነገር ይፈጠር አይመስለኝም፡፡ አትድከሚ ትሩፋት፡፡ እኔ በጣ---ም ብዙ ደክሜያለሁ! እዚህ ደረጃ ላለመድረስ የቻልኩትን ሁሉ ጥሬያለሁ፡፡»

«ይነበብ እኔ እኮ ቃል የገባሁለት ሰው አለኝ፡፡ ከኢሕአፓ የድል ማግስት በኋላ ቃል ከገባሁለት ሰው ጋር እንጋባለን» ስትለው ድምጿ ሙትት ብሎ ነበር፡፡ እሱ ቆርጦለት--- እንዲቆርጥላት አንጂ በተናገረችው እርግጠኛ ሆና አልነበረም፡፡





«እኔና እንቺ ግን በድል ዋዜማ እንጋባለን፡፡ እመኝኝ ትሩፌ ድሉን የምንቀበለው ከአዲሱ ልጃችን ጋር ይሆናል፡፡ የድሉን ብስራት ከአዲሱ ትውልድ ጋር ስናከብረው ይታየኛል! ድርብ ድል ይሉሻል ይሄ ነው፡፡ ደስ አይልም!» ብሏት የሰዓት እላፊ ገደብ ማለፉን እንኳ ልብ ሳይል ወጥቶ ሄደ፡፡ ይነበብ ከሄደ በኋላ የተናገረውን በሙሉ አንደገና አሰበችው፡፡ መረር ያለ ነበር፡፡ የራሷን አቋም ለማወቅ ውስጧን መረመረች፡፡ ቁርጥ--ጥርት ያለ አቋም አልነበራትም፡፡ የዋለለችው ልቧ ፍራት--- ፍራት አሳት፡፡

******

ትሩፋት አባቷ አቶ ማንያዘዋል በጠና የመታመማቸውን ወሬ ይዞላት የመጣው ራሱ ይነበብ ነበር፡፡ ጅግና ኪዳነምህረት ቀበሌ ገበሬ ማኅበር የትኑራ የእምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበርን ለማጠናከር በሄደ ጊዜ ጌታሁንን ያገኘዋል፡፡ ጌታሁን የትሩፋት አባት ቅርብ ዘመድ ነው፡፡ በየትኑራ የእምራቾ ገበሬዎች ማኅበር ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ያለው አባል ነው፡፡ ከይነበብ ጋር ይበልጥ የሚያግባባቸው ደግሞ ድብቁ ድርጅታዊ ሥራ ነው--- ልክ አንደ ወሰን፡፡

«ደህና ሰነበትከ ጋሼ ይነበብ» አለ ጌታሁን ከእምራች ገበሬዎች ሰብሰባ በኋላ፡፡

«እንደምን አለህ ጌታሁን? ቤተሰብ ሁሉ ደህና ?» አለ ይነበብ አጸፋውን፡፡

«እግዜር ይመስገን ሁላችንም ደህና ነን፡፡ የእኛ ሰዎች እስቲመጡ ና እዚች ላይ እረፍ በል» አለው የሆነች የግንድ ጉማጅ ነገር እያመቻቸለት፡፡ ሌሎች አባሶች እስኪሰባሰቡ ሁለቱ ተቀምጠው ጨዋታ ጀመሩ፡፡

«እንበሳሜ አንዲት ዘመድ ነበረችኝ ትተዋወቁ ይሆን ጋሼ ይነበብ? አሰተማሪ ናት» ጠየቀ ጌታሁን፡፡

«ሦስት ሴት መምህራን አሉ፡፡ ዘመድህ የትኛዋ ትሆን?» አለው ይነበብ ሦስቱንም ሴቶች በዐይነ-ሕሊናው እያመጣቸው፡፡ ከሁለቱ ሴቶች በላይ ትሩፋት ገዝፋ---ጎልታ ታየችው፡፡

«ትሩፋት ነው ስሟ ካወቅሃት፡፡»

«አውቃታለሁ» አለ ቀልጠፍ ብሎ፡፡

«ዘድያ ጋሼ ይነበብ ያባቷን በጠና መታመም ያልሰማች ሆና ነው መጥታ ያልጠየቀችው? እኔም እንዳጋጣሚ አዲስ ዘመን ለጉዳይ ሄጄ አምላክ ፈቅዶ ዐይኑን አይቼው መጣሁ» አለ ጌታሁን፡፡

«ትሰማ አትሰማ ያወቅሁት ነገር የለም:: ስገምት ግን የለማች አይመስለኝም:: የመንግሥት ሠራተኛ በመሆኗ ብትለማም በፈለገችው ጊዜ ብድግ ብላ መምጣት አትችልም አኮ ጌታሁን:: እንደምታውቀው የይለፍ ደብዳቤ ካልያዙ ካንዱ ቦታ ወደ ሌላው መንቀሳቀስ አይቻልም:: የሥራ ጊዜ በመሆኑ ደግሞ ፈቃድ እንዲህ በቀላሉ ማግኘት ይቸግራል::»

«አይ ጋሼ ይነበብ እንኳን እናንተን ከተምኞችንና የተማራችሁትን ዛሬ ዛሬስ እኛንም አላላውስ አላንቀሳቅስ ብለውናል ኧረ! ያለ ይለፍ ወረቀት አዲስ ዘመንና ሐሙሲት እንኳ ገበያ ውለን መምጣት አልቻልንም» አለ ጌታሁን እየተማረረ::

«ይኸውልህ ጌታሁን በገዛ አገራችን እንደ ልብ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንኳ አልተፈቀደልንም:: በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ላይ ደርሰናል» አለ ይነበብ በቁጭት::

«አይ ጋሼ ይነበብ! የእግዜር እርዳታ ታክሎልን ይሄ አውሬ መንግሥት ቶሎ ካልነቀልነው ገና ብዙ ችግር ይገጥመናል:: ትሩፋት ግን ከቻለች የይለፍ ወረቀቱን አጥፋም ቢሆን ዐይኑን ብታየው ጥሩ ነበር» አለ ጌታሁን ተከዝ ብሎ::

«መልዕክቱን እንዳደርስላት ትፈልጋለህ ጌታሁን?»

«እንተን መላኩ ድፍረት እንዳይሆንብኝ እንጂ ተሆነማ ጥሩ ነበር:: ኋላ አንድ ነገር ቢሆን ጠጠቱ ከሆደ አይወጣላትም:: በሕይወት እያለ ዐይኑን ብታየው ይሻላታል» አለ ጌታሁን ስጋት የገባው መሆኑ ከአነጋገሩ እየታወቀ::

«ግድ የለም እንደ ሄድኩ እነግራታለሁ::»

«እንግዲያማ ኢደራህን ጋሼ ይነበብ ልድፈርህና ሳትውል ሳታድር ዐይኑን ትየው ንገራት» አለ ጌታሁን ጠበቅ አድርጎ::

አንበሳሜ እንደ ተመለሰ ከቤቱ እንኳ አልገባም:: በቀጥታ ወደ ትሩፋት ቤት ነበር ያመራው:: የውጬን በር ሲያንኳኳ በፈረሰው የኢጋም ሽምጥ አጥር ወደ ውስጥ ተመለከተ:: ራሔልን ለትመጣ እያት:: ከሰላምታ በኋላ ትሩፋት እቤት አለመኖሯን ነገረችው:: እቤት ገብቶ እንዲጠብቃት ብትለምነውም አልገባም:: ትሩፋት በዚህ ሰዓት የት ልትሄድ እንደምትችል እያንሰላሰለ ወደ ቤቱ ተመለሰ:: ሠራተኛው የገላ ውሃ እንድታሞቅለት ነግሮ አልጋው ላይ ጋደም አለ አንበሳሜ የመጣበትን አብይ ዓላማ እያሰበ:: ከመጣ ጀምሮ የሰራቸውን ሥራዎች አንድ ባንድ ፈተሻቸው:: ያን ያህል አጥጋቢ ሆነው አላገኛቸውም:: በጣም መንቀሳቀስ እንዳለበት እያውጠነጠነ እያለ ትሩፋት ድንገት መጥታ በሐሳቡ ስንቅር አለበችበት::





«ራሴን ልዋሸው አልችልም:: አፍቅሬያታለሁ:: ከማውቃቸው ብዙ ሴቶች ሁሉ እሷ በምኗ እንደምትለይ ባይገባኝም ትሩፋት ልዩ ናት:: ግን ምኗ ይሆን ልዩ የሆነብኝ?» ሲል ሁለተኛ ደረጃ፣ አዋላ ማኅበራዊ ኑሮ እድገት ማስልጠኛ ተቋም፣ የእድገት በኅብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ላይ የሚያውቃቸውንና ያወጣቸውን ሴቶች ሁሉ በዐይነ ሕሊናው ተመለከታቸው:: በጣም ብዙ ቆንጆ ቆንጆ ሴት ልጆችን ያውቃል:: እንደ ትሩፋት ግን አላብከነከኑትም::

«እዚች ትንሽ የገጠር ከተማ ሌላ ብዙ ሴቶች ማየት ባለመቻሌ ይሆን? አማራጭ በማጣቴ ይሆን?» ራሱን ጠየቀ «አይደለም! በፍጹም አይደለም!» ሆነ መልሱ:: «ትሩፋት ልዩ ናት! ምኗ ላይ ይሆን የምትለየው ግን?» በጀርባዉ እንደ ተኛ ብዙ አሰበ:: ስለ ትሩፋት ብዙ አወጣ አወረደ:: መጨረሻ ላይ «አዎ ዐይኗ ላይ! ሌሎች ሴቶች ላይ የሌለ ዐይኗ ውስጥ አንድ የሚታየኝ የተለየ ነገር አለ» ብሎ ደመደመ:: እንደገና ደግሞ ከአዲስ አበባ አንበሳሜ ድረስ የመጣበትን ዋና ጉዳይና ተልዕኮውን አውጠነጠነ:: በአሁኑ ሰዓት--በዚች ቅጽበት በደርግ ፋሽስታዊ የአፈና መረብ ውስጥ ገብተው ስንት ጓዶች እንደሚሰቃዩና እንደሚሰው አሰበ:: ራሱን እንደ ከሀዲ ቆጠረ:: ጨነቀው:: ኢሕአፓ ለተፈጥሮ ልጓም ሳታበጅ በደፈናው መፋቀርን መከልከሏ ትክክል ነው ብሎ መቀበል ከበደው:: ሐሳቡና ምኞቱ ተዘበራርቀውበት እንዴ ራሱን ሲወቅስ ሌላ ጊዜ ለድክመቱ ማመኻኛ ምክንያት---መሸሸጊያ ጥግ ሲፈልግ

«ጋሼ ውሃው ሙቆሎዎታል:: ይኸው ጥሽቱንም አዘጋጅቸልዎታለሁ» የሚለው የሰራተኛው ድምጽ ከገባበት የሐሳብ አዘቅት ገላገለው:: የሞቀ ውሀ በባልዲና የልብስ ማጠቢያ ሳፋ ወለሉ መሀል ላይ አስቀምጣለት በሩን ከኋላዋ ዘግታ ወጣች:: ይነበብ ገላውን እየታጠበ ሁሉ የሚያስበው ስለ ትሩፋትና ስለ ድርጅቱ ነበር::

«ለሁለተኛ ጊዜ መምጣቴ ነው» አላት ይነበብ ሲገናኙ::

«ራሔል ነገረችኝ:: ምነው ይህን ያህል በእግር በፈረስ የፈለከኝ?» አለችው ወደ ቤት እየገቡ::

«እሱን አንቺም ታውቂያለሽ:: ያውም የምፈልግሽ አንድ እምሳል አንድ አካል እስከ መሆን ድረስ ነው» ሲላት ቀልድ ብሎ ነገር ከፊቱ ላይ አይነበብም:: ድምጹም ከረር ያለ ነበር::

«አንተ ነገር ያልሰለቸህ ሰው ነህ ወንድሜ! ይልቅ ለምን ጉዳይ እንደ ፈለከኝ ልትነግረኝ ትችላለህ?»

«ጅግና ኪዳነምህረት የሚኖር ጌታሁን የሚባል ዘመዳችሁ አንድ መልዕክት እንዳደርስልሽ ልኮኝ ነበር:: በዚህ ጸባይሽ ግን የምነግርሽ አይመስለኝም» አላት ፊት ለፊት እየተመለከታት::

«ይሄኔ አንድ ዘመዳችን ሞቶ 'ልቅሶ ድረሺ' ሲለኝ እንዳይሆን? እሱ ምን አለበት? የይለፍ ደብዳቤ አይፈለግበት፤ ፈቃድ አይጠይቅ:: ባሻው ጊዜ ብድግ ብሎ ከፈለገው ቦታ ደርሶ ይመለሳል::»

«እንዴ ትሩፌ! በአሁኑ ጊዜ እርሶ አደር ቢሆንም ያለይለፍ ደብዳቤ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ አይችልም:: አላጋጠመሽ ይሆናል እንጂ በተለይ ፈታሹ ሰይጣናሙ ወታደር ከሆነ ባላገር ነው ብሎ አይምረውም:: ሰንቱን ምስኪን እርሶ አደር ባፍጢሙ እያዳፋ ሲወስደው አይቻለሁ መሰለሽ» አለ ይነበብ::

«ከስንት አንድ ነው እባክህ! እሺ ለቅሶ እንድደርስ ካልሆነ መልዕክቱ ምን ነበር? ከአንዴም ሁለቴ የፈለከኝ» አለች ትሩፋት::

«መፈለግሽን አውቀሽ አይደል አንቺም እንዲህ የምትከሪውና የምትጠፊው::»

«በእናትህ ይነበብ አሁን የሚቀለድበት ጊዜ ላይ ነው ያለነው ግን?»

«ከምሬ ነው ትሩፋት እየቀለድኩ አይደለም:: ቀልድ መስሎሽ ከሆነ ተሳስተሻል::»

«ተቀድመሃል ወዳጄ::»

«መጽሐፍ ቅዱስ ሉቃስ-- ምዕራፍ አስራ ሦስት፤ ቁጥር ሰላሳ ላይ ምን ይላል መሰለሽ ‹የኋለኞቹ ፊተኞች ይሆናሉ፤ ፊተኞቹም ኋለኞች ይሆናሉ› ይላል:: ዘመን ተቀይሮ ኮሚኒስት ሆንኩ እንጂ የቄስ ልጅ ነበርኩ» አላት::

«ፉከራህ ለጠለፋ የተዘጋጀህ ያስመስልብሀል:: ባታስበው ይሻልሃል:: ስንት ሳተና ሳተና ዘመዶች እንዳሉኝ እይተሃል:: እነ ወሰንን የመሳሰሉ:: ገልዳን አያሻግሩህም::

«ምርጫ ካጣሁ እሱንም መሞከሬ አይቀርም:: እርግጠኛ ነኝ ግን ፍቅር ያሸንፋል!!»

«እሺ በቃ! የጌታሁንን መልዕክት ንገረኝ» አለች ስልቾት ብሏት::

«እንደ-ሱ ነው:: 'እሺ' ስትይ ሲያዩሽ እንዴት ደስ እንደምትይ!» አላት ፈገግ ብሎ:: ፈገግ ሲል ትናናሽ እንቁ መሳይ ጥርሶቹ ያምራሉ:: ይበልጥ ያሳመራቸው ደግሞ ከላይና ከታች በቀጭኑ እኩል ተስተካክለው የወረዱት ፍንጭቶቹ ናቸው::

«አባትሽን ትንሽ አሟቸዋል አሉ እንድታያቸው ይፈልጋሉ» ሲላት ከመደንገጧ የተነሳ ብድግ አለች:: በፈርጣማ ክንዱ ጎትቶ ቁጭ እንድትል አደረጋት::





«ትሩፋት! እነራሔልን ደንግጠሽ ማስደንገጥ ያለብሽ አይመስለኝም:: ተረጋግተሽ ማረጋጋት ይጠበቅብሻል:: ታላቅ እህት መሆንሽን አትርሺ:: ታመሙ እንጂ ሞቱ አልተባልሽም:: ምን እንዲህ ያደርግሻል?» ሲላት በመጠኑም ቢሆን ተረጋጋች::

«ፈቃድ እንዴት ይሆን ማግኘት የምችለው? የይለፍ ደብዳቤውንስ ይጽፉልኝ ይሆን? ደግሞ የፈተና ወቅት መሆኑ:: ምን አለበት አሁን በዚህ ጊዜ ባይታመም» አለች ጭንቅ እያላት::

«የፈተና ወቅት መሆኑ እንደውም ጥሩ ነው:: ፈተናሽን አውጥተሽ ሲፈትኑልሽ ለሚችሉ ፈቃደኛ መምህራን መስጠት ትችያለሽ:: እነሱ ፈትነው የፈተና ወረቀቱን ከሰበሰቡልሽ አባትሽን ጠይቀሽ ስትመለሽ እኛ ደግሞ ተረዳድተን እናርመዋለን» አላት ይነበብ:: ጉዳዩዋን ልክ እንደ ራሱ ጉዳይ በመቁጠር::

«መፈተኑን እንኳ አማዋይሽም ብትሆን ትፈትንልኝ ነበር:: ፈቃድና የይለፍ ደብዳቤውን ማግኘቱ ነው ችግሩ» አለች ባመጣው ሐሳብ እየተስማማች::

«ምነው ከአቶ ጌትነት ጋር ትግባቡ የለም እንዴ? ቀስ ብለሽ የደረሰብሽን ችግር ንገሪው:: ፈተናሽን የሚፈትንልሽና የፈተና ወረቀቱን የሚሰበስብልሽ ፈቃደኛ መምህር እንዳገኘሽ ግለጭለት:: የሥራ ክፍተት እንደማይፈጠር አሳምኚው:: የይለፍ ደብዳቤውን የምታገኚበትን መንገድ እኔ እፈልጋለሁ» ሲላት በመጠኑ እፎይታ ተሰማት:: ይነበብ ችግሯን አብሮ በመላፈሉ ከልብ አመሰገነችው:: ሌላው ሰጋቷ ደግሞ ራሔልና ድልነሳ «አብረን እንሄዳለን» ማለታቸው አይቀርም:: እንዴት አሳምናቸው እንደሚቀሩ ማሰብ ጀመረች:: ሌሎቹ እንኳ ከእሷ ፈቃድ ውጭ አይሆኑም::

ትሩፋት የሦስት ቀን ፈቃድ አገኘች:: ቅዳሜና እሁድን አንተርሳ አምስት ቀን እንዲሆንላት ፈቃዷን የሞላችው ከረቡዕ ጀምራ ነበር:: የይለፍ ደብዳቤው በይነበብ በኩል መጣላት:: ራሔልና ድልነሳ እሷ ስትመለስ ሲሄዱ ተስማሙላት::

ረብዕ በጠዋት ተነስታ በእግሯ መንገድ ልትጀምር ስትል ለስራ ጉዳይ የመጣች አንድ የግብርና መኪና ገበያው መሀል ቆማ አየቻት:: የጉዞ አቅጣጫዋ ወዴት እንደ ሆነ ባለማወቋ በመጠየቅና ባለመጠየቅ መካከል ላይ እንዳለች ይነበብ ወደ እሷ ሲመጣ አየችው:: ሲታየው ውስጧ መረበሹን አላቆመም:: እሷም በሁኔታዋ መናደዷ አልቀረም::

«እንደምን አደርሽ ትሩፋት? እድለኛ ነሽ ለሥራ ጉዳይ ወደ ወረታ እየሄድን ነው:: አብረሽን መሄድ ትችያለሽ:: ከዚያ በኋላ ያለው ትራንስፖርት ችግር አይሆንብሽም» ሲላት «አመሰግናለሁ ይነበብ» ከማለት ውጪ ሌላ ቃል አልነበራትም ::

አንድ የግብርና ባለሙያ ከሾፌሩ ጎን ፊት ተቀመጠ፡፡ ከኋላ የተቀመጡት ትሩፋትና ይነበብ ብቻ ነበሩ፡፡ ድንጋይና ጠጠር ያልፈሰሰበት ዝም ብሎ በሰው ጉልበት ብቻ የተጠረገው መንገድ በክረምቱ ጎርፍ በየቦታው ጉድጓድ-ጉድጓድ ሰርቷል፡፡ በመንገዱ ምክንያት መኪናዋ ወደ ሰማይ ጉና ወደ ምድር ትወርዳለች፡፡ ውስጧ ያሉ ሰዎች አብረዋት ይንገላታሉ፡፡ ይነበብ የትሩፋትን እንግልት ለመቀነስ አስቦ ይመስላል መኪናዋ ወደ ላይና ወደ ታች ስትዘልና ባፍጢሟ ልትተከል በሞከረች ቁጥር እቅፍ እያደረገ ወደ ጉያው ይሸጉጣታል፡፡ እሷ ደግሞ ሰዎቹ እንዳያዩዋት ተሳቃ ልትሞት ደረሰች፡፡ እንዲህ ከምሳቀቅ የይነበብ እርዳታ ቀርቶብኝ የመኪናዋ እንግልት ይሻለኝ ነበር አለች በውስጧ፡፡ እንዲህ እየሆኑ ሀሙሲት ደረሱ፡፡

«አብሬሽ ብሄድ ቅር ይልሻል?» አላት ይነበብ ወረታ እንደ ደረሱ፡፡

«አይ! ኧረ አያስፈልግም! እስከ አሁን ያደረግህልኝ ውለታ ከበቂ በላይ ነው፡፡»

«የእኔም ጉዳይ እንደ ሆነ አድርገሽ ውሰጅው» ብሎ ትክ ብሎ አያት፡፡ ዐይኑን ሸሸች፡፡ መኪና እግኝታ ተሳፍራ እስክትሄድ ድረስ ይነበብ አብሯት ነበር፡፡

አዲስ ዘመን ደረሰች፡፡ ወደ አባቷ ቤት ስትሄድ ድሮ የምታውቀው ቅርብ የነበረው መንገድ አሁን ሩ—ቅ የሆነ መሰላት፡፡ ያንኑ አንድ የጠጠር የመኪና መንገድ ተብዬ ተከትላ ስትሄድ ሁሉ ስጋት ውስጥ ነበረች፡፡ ጥቂት እንደ ሄደች ከሰልክ ቤቱ ከፍ ብላ በስተግራ በኩል በምትገኘው ጠባብ መንገድ የአርጉዲፋን ቦይ ተሻግራ ወደ መንደሩ ውስጥ ገባች፡፡ ሰፈሩ ጭልል ብሏል፡፡ የአባቷን ግቢ አሻግራ ተመለከተች፡፡ ድንኳን አልተጣለም፡፡ ቢያንስ ሞት እንደ ሌለ አወቀች፡፡ እቤት ስትገባ አባቷ አልጋቸው ላይ ተኝተዋል፡፡ መሃኗን ሚስታቸውን ከፈቱ በኋላ የአገቧት ሚስታቸው የምትጠባ ልጇን ይዛ አጠገባቸው አለች፡፡ ሁለት አባቷን ጠያቂ ጎረቤቶች መደብ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ ትሩፋት ስትገባ ሁሉም ቆመው ተቀበሏት፡፡ ጉንጯን እያገላበጡ ሳሟት፡፡ ወደ አባቷ ስትጠጋ ድክም ብለዋል እንጂ ወዛቸው ደህና ነው፡፡ ከአንገታቸው ቀና ብለው

«እንዴት ሰነበትሽ ትሩፋት» ሲሏት ድምጻቸው ስልል ያለ መሰላት፡፡ እንባዋ መጣ፡፡ በእንጀራ እናት እንዲያድጉ በማድረጋቸውና ጠጪ በመሆናቸው ብታዝንባቸውም አትጠላቸውም፡፡ «እናታችን ባይፈታ ኖሮ....» የሚለው ወቀሳዋ እንዳለ ሆኖ ለእሷ ያላቸውን ልዩ ፍቅርም ታውቃለች፡፡ በተለይ ለመምህራን ኮርስ አልፋ አስመራ ድረስ ይዘዋት የሄዱትን ምንጊዜም ልዩ ቦታ የምትሰጠው ነው፡፡ በዚሁ የአስመራ ጉዞ ከመሃኗ እንጀራ እናቷ ጋር ስንት ጭቅጭቅ ፈጥረው እንደ ነበር ዛሬም ትዝ ይላታል፡፡ ቢያስሯቸው ከቤት መቀመጥ የማይወዱት ሰውዬ እንዲህ ከአልጋ ላይ ውለው ስታያቸው ከልቧ አዘነችላቸው፡፡





ጤና ጣቢያ ወስዳ በምታውቃቸው ሀኪም ጓደኞቿ አማካኝነት እንዲታዩ አደረገች፡፡ በእርግጥም የተሻላቸው መሰሉ፡፡ ያለቻትን የፈቃድ ጊዜ ሁሉ ቀና እያሉ ሲያጫዉቷት ሰነበቱ፡፡ ወደ ስራ ቦታዋ መመለሻ ቀኗ ሲደርስ አባቷ ጠሯት፡፡

«እቤት ባብዬ ፈለከኝ?» አለች ከአጠገባቸው ሄዳ እየተቀመጠች፡፡

«አዎ ፈለኩሽ ልጄ፤ ለብርቱ ጉዳይ ፈለኩሽ» አሏት፡፡ ለወትሮው ትክ ብለው ማየት የማይወዱት ሰውዬ ትኩር ብለው እየተመለከቷት፡፡

«ምነው ባብዬ በደህና?»

«በደህና ነው ትሩፋቴ፡፡ በደህና ነው» ብለው ዝም አሉ፤ እሷም ዝም ብላ ጠበቀቻቸው፡፡

«እነ ድልነሳ ምነው አብረውሽ ያልመጡ?» አሉ፡፡ ሊያናግሯት የፈለጉት ጉዳይ ግን ይህ እንዳልሆነ ገብቷታል፡፡

«ጊዜውን ታውቀው የለ ባብዬ፡፡ ተንጋግተን ስንመጣ ለተመልካች ጥሩ አይሆንም ብዬ ነው፡፡ እኔ እንደ ተመለስኩ እነሱ ይመጣሉ፡፡ ትንሽ ቀንም አብረውህ ይቆያሉ» አለቻቸው፡፡

«ደግ ትሩፋቴ ጥሩ አለባችኋል፡፡ ሞት ቀጠሮ አይሰጥም ልጄ፡፡ በቀደምለት ሞቼ ነበር፡፡ ከፈን ከቀደድኩ ነው የተመለስኩ፡፡ ቀኔ ገና ያልተቆረጠች ሆና» ብለው ትክዝ አሉ፡፡

«ተመስገን ነው ባብዬ፡፡ አትመመኝማ አይባልም፡፡ አሁን ተሽሎሃል፤ እያደር ደግሞ ታገግማለህ፡፡»

«ጌታዬን የማስቸግረው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ እሱን ሳያሳየኝ አይግደለኝ እንጂ ሞት አልፈራም ልጄ፡፡ ከእንግዲህ እኔ ሞት ፈርቼ የት ልደርስ ነው?»

«ምነው ባብዬ ገና እኮ ነህ፡፡ ከአንተ የሸመገሉት ሁሉ እያሉ ሞትን እንዴት ታስበዋለህ? እኛ እንድትቆይልኝ እንፈልጋለን፡፡ አባት መኩሪያ ነው፡፡ አባት ቅርስ ነው» አለቻቸው፡፡

«ከሞት የሚቀር የለም ትሩፋቴ፡፡ ይልቅስ እኔን አባትሽን ከልብሽ የምትወጅኝ ከሆነ ደስ ብሎኝ ወደ መቃብሬ በሰላም እንድወርድ አድርጊ ልጄ!» አሉ፡፡ ንግግራቸው የማባበል ነበር፡፡

«አልገባኝም ባብዬ፡፡ ምን ባደግልህ ነው ደስ የሚልህ?»

«ሳልሞት ዓለምሽን አሳይኝ ልጄ! ዛሬ ዘመን እስኳላ ትምህርት የሚሉት ጣጣ መጥቶ ነው እንጂ ሴት ልጅ አሰራ አምስት ዓመት ካለፋት በኋላ ካላገባች እንደ ቁሞ ቀር ነበር የምትቆጠር፡፡ አንቺ ደሞ ሰራ ይዞሻል፡፡ ከእንግዲህ ምን ይጠበቃል? መቃብር ሳልወርድ ባይሆን የአንቺን ዓለም አይቼ የልጅ ልጅ ስሜ ልሙት፡፡ በጓደኞቼ እንደ ቀናሁ አልቅር ልጄ!» አሏት፡፡ ልመናም ልምምጥም በተሞላበት አንደበት፡፡ ትሩፋት ድንግጥ አለች፡፡

«ባብዬ አንዴው እንዲህ በድንገት ባሉስ ከየት ይመጣል?» አለች አፏ ላይ እንደ መጣ፡፡

«አንቺ ፈቃድሽ ከሆነ ልጅህን አባከህ እጇን ስጠነ እያለ የሚሰምነኝ ስንቱ መኳንንት-- ስንቱ የመንግሥት ሠራተኛ መሰለሽ» አሏት፡፡ እሷ ከፈለገች የሚመርጡላትን ባል ማን - ከማን እንደሚሻል በልባቸው እያወዳደሩ፡፡

«ባይሆን ምርጫው እንኳ ለእኔ ይሰጠኝ፡፡» አለች ትሩፋት ሰበብ እንዳጣች ሲገባት፡፡

«እሱን እንደ ወደድሽ፡፡ ግድ በእኔ ምርጫ ይሁን አልልም፡፡ ዘመን ሽሮታል፡፡ የማሰቸግርሽ የሞት ቀጠሮ የለውም፡፡ ነገ ዛሬ ሳትይ እንድትወስኚ ነው፡፡ ያለዚያ እንዲህ እየለመንኩሽ ብሞት መቃብር ውስጥ ሆኜም አጽሜ ያዝንብሻል ልጄ!» አሏት፡፡ አቶ ማንያዘዋል ካለ ነገራቸው እንደ እሳቸው ዘመን አባቶች ልጆቻቸውን

«በየት ወጥታችሁ-- በየት ገብታችሁ-- ከማን ጋር ቆማችሁ-- ከማን ጋር አየኋችሁ-- ከማን ጋር ወጣችሁ-- ከማን ወረዳችሁ» እያሉ አያሰጨንቁም ነበር፡፡ በልጆቻቸው ላይ እምነት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ አቶ ማንያዘዋል በዘመናቸው ከነበሩት ሰዎች የተሻለ ነጻነት ለልጆቻቸው የሰጡ ሰው ነበሩ፡፡ አሁንም ቢሆን «እኔ የመርጥኩልሽን ካላገባሽ» ብለው ድርቅ አላሉም፡፡ እንደውም በአዲስ ዘመን ሰው እንደ ታሪክ የሚነገርላቸው አንድ ኢጋጣሚ አላቸው፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ትሩፋትን ለሚስትነት ያሰባል፡፡ አዲስ ዘመን ከተማ እሉ የተባሉ ሽማግሌዎችን አፈላልጎ ይልካል፡፡ አቶ ማንያዝዋል ሽማግሌዎችን ተቀብለው ሲያነጋግሩ የመጀመርያ ጥያቄያቸው የነበረው

«ለመሆኑ ባለጉዳዩዋን ጠይቆ ፈቃድ አግኝቷል ወይ?» የሚል ነበር፡፡ ሽማግሌዎች መጀመርያ የእሳቸውን ፈቃድ ለማግኘት እንደ መጡ እንጂ ሰውየው ትሩፋትን ገና አለመነጋገሩን ሲነግሯቸው

«መጀመሪያ ከባለጉዳይዋ ጋር በጨረሰ ነበር እንጂ--- እኔ እሺ ብለው እኔን ኢያገባኝ፡፡» ብለው ሽማግሌዎችን አሰቀው ሸኙተዋቸዋል ይባላል፡፡ የአዲስ ዘመን ሰው እስካሁን «እኔን አያገባኝ» አለ ማንያዘዋል እያለ እንደ ተረት ይዞላቸዋል፡፡

«ትሩፋቴ መፍጠን አለብሽ፡፡ ብዙ እድሜ እንደሌለኝ ከአያያዜ አውቀዋለሁ፡፡ እንደ አዘንኩ መቃብር አልውረድብሽ ልጄ!»





«እሺ ባብዬ አስብበታለሁ» አለቻቸው ደስ እንዲላቸው፡፡

ለስንብት ስትሰማቸው ሁሉ «አደራ! እንግዲህ ጊዜ እንዳትፈጅ ልጄ አደራ!» እያሏት ነበር፡፡ ሁኔታቸው ሁሉ ስጋት ለቀቀባት፡፡ አባቷ እንደዚያን ቀን አሳዝነዋት አያውቁም፡፡ ምን ማድረግ እንዳለባት ግራ እስኪገባት ድረስ አስጨነቋት፡፡

በትራንስፖርት መኪና ተሳፍራ ስትሄድ መንገዱን ሁሉ የምታስበው ስለ አባቷ ነበር፡፡ «እውነት ሊሞት ይሆን እንዴ እንዲህ ያጣደፈኝ፡፡ ምን ታይቶት ይሆን?» የሚለው ሐሳብ እንደ ወዘወዛት ሀሙሲት ደረሰች፡፡ ወደ እንበላሜ የሚሄድ ሰው ስታፈላልግ ይነበብ እዚያው ሀሙሲት ነበር፡፡ ስታየው

«እየጠበቀኝ ነበር እንዴ? ምን ዓይነቱ ቸኮ ልጅ ገጠመኝ አባካችሁ!?» አለች፡፡ ፍቅሩ በሐሳቧ ብቅ ጥልቅ ማለቱም አልቀረላትም፡፡

«ፍቅሩ ግን ምን ሆኖ ይሆን የጠፋው? በሕይወት መኖሩንና አለመኖሩን ሳላዉቅ ስንት ዓመት መጠበቅ ይኖርብኝ ይሆን? አለሁ ወይም የለሁም ሳይለኝ ይኸው ሦስት ዓመት ሊያልፍ ነው» ብላ ራሷን ወደ ውስጥ መረመረች፡፡ ጥፋተኝነት አልተሰማትም፡፡ የድርጅቷ ጉዳይ ግን እንዲህ በዋዛ የሚታይ አይደለም፡፡ ያውም በዚህ ወሳኝ ወቅት፡፡ «አይሆንም! አይደረግም!» አለች፡፡ የአባቷ ጉዳይ ደግሞ መጣ፡፡ ጭንቀታቸው ታያት፡፡ ልመናቸው አሳዘናት፡፡ የጠየቋትን ሳትፈጽም ቢሞቱ ፀፀቱ እስከ ወድያኛው የሚለቃት አይመስላትም፡፡ ግራ ግብት አላት፡፡ ተጨነቀች፡፡

«ትሩፋት እንዴት ሰነበትሽ? አባትሽ እንዴት ናቸው?» አላት ይነበብ፡፡ የእጅ ሰላምታ ብቻ ሰጥታ ልታሰቆመው ስትል ጎተት አድርጎ ጉንጯን ሳመ፡፡ ፍቅሩ መጀመሪያ ቀን ከባህርዳር መጥቶ እንደ ሳማት አይነት ስሜት አልነበረም፡፡ ያን ጊዜ የተሰማት ትኩስ የልጅነት ሙቀት ነበር፡፡ ያኔ የሸተታት ትኩስ ወተት-ወተት የሚል የልጅነት ትንፋሽ ነበር፡፡ የይነበብ ግን ልዩ ነው፡፡ ውስጥ ድረስ ዘልቆ የልቧን ምት ነው የጨመረው፡፡ አጥንቷ ድረስ የዘለቀ ንዝረት ነው ያስከተለው፡፡ ኢጋጣሚውን ትውደደው ወይ ደግሞ ትጥላው ለይታ ያወቀችው ነገር አልነበረም፡፡ ድንግጥ ማለቷ ብቻ ነበር የታወቃት፡፡ መልስ የሰጠችው ዘግይታ ነበር፡፡

«ደህና ነው፡፡ የተሻለው ቢመስልም ጨርሶ አልዳነም» አለች እንዳይታዘባት ራሷን ለመግዛት እየታገለች፡፡

«አይዞሽ ቀስ በቀስ ይሻላቸዋል፡፡»

«ተስፋ አደርጋለሁ» አለች አሻግራ እየተመለከተች፡፡ የምታየው ነገር ግን አልነበረም፡፡

«ተስፋ ጥሩ ነው፡፡ የሰው ልጅ ነገን በተስፋ ባይጠብቅ ኖሮ ዛሬ ሞቶ ያልቅ ነበር» አላት፡፡

«ወደ እንበሳሜ የሚሄድ ሰው እገኝ ይሆን? ለነገ ሥራ ዛሬ ገብቼ ማደር ይኖርብኛል» አለች የወሬውን አቅጣጫ ቀይራ፡፡

«እንዴት የግብርና መኪና ትመጣለች ተብሎ እኔም እሷን እየጠበኩ ነው፡፡ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ካልመጣች አብረን እንሄዳለን፡፡ ካልሆነም አድረን ነገ በጣም በጧት እንጓዛለን» አላት፡፡

«ማደር አልችልም፡፡ ነገ ደከሞኝ ሥራ መግባት አልፈልግም፡፡ እርግጠኛ መኪናዋ የማትመጣ ከሆነ አብሮኝ የሚሄድ ሰው ማፈላለግ ይኖርብኛል» አለች ዐይኗ ሰው እየፈለገ፡፡

«ኧረ እባክሽ ረጋ በይ! ምን ያስቸኩልሻል? መጀመሪያ መኪናዋን እንያት፡፡ ማደር ካልፈለግሽ አንቺ በርቺ እንጂ በጨረቃም ቢሆን አብረን እንጓዛለን፡፡ እንደውም በጨረቃ ብርሀን መጓዝ ፍቅር ያደረጃል ይባላል እንደ ሮሚዮና ጁሊዬት፡፡

'ሮሚዮ ሮሚዮ የልቤ ወለላ፣

እባክህ ቀይረው ስምህን በሌላ፡፡.....' እያለች የፍቅር ወለላ ማር ያዘነበችለት ፍንትው ብላ በወጣት ሙሉ ጨረቃ ነበር፡፡ በመኝታ ቤቷ መስኮት ብቅ ብላ ሮሚዮን ስታየው እማላዩ የጨረቃዋ ብርሃን እላዩ ላይ ፈሶ ነበር፡፡ በጨረቃ ብርሀን እንጓዝ ካልሽ ደስታውን አልችለውም፡፡ ብዙ የፍቅር ቃላት የሚወለዱት ከጨረቃዋ ጋር ነው አሉ» አላት፡፡ በሙሉ ፈገግታ እተየመለከታት፡፡

«ደግሜ ላስጠነቅቅህ እወዳለሁ ይነበብ! እንደ እለመታደል ሆኖ የኛ ትውልድ ለፍቅር ጨዋታ የተፈጠረ አይደለም፡፡ ለትግል ነው» አለችው ትሩፋት ኮስተር ብላ፡፡

«አቤት! ኮስተር ስትይ ደግሞ እንዴት እንደምታምሪ! በይ ነይ መኪናዋ እስክትመጣ ድረስ ገረመው ቡና ቤት ሻይ ቡና እያልን እንጠብቃት» አላት፡፡ እጇን ያዝ አድርጎ ወደዚያው ጎተት እያደረጋት፡፡ መሄድ አልፈለገችም----- ግን አልቀረችም፡፡

ይኑበበ እንዳለው የግብርናዋ መኪና ዘጠኝ ሰዓት ላይ አልመጣችም፡፡ ሁለት ሰዓት ያህል ቆይታ አስራ አንድ ሰዓት ገደማ መጣች፡፡ ትሩፋት ያታለላት መሰሏት ውስጥ ውስጧን በጣም በሽቃ ነበር፡፡ የመኪናዋን መምጣት ስታይ ግን ደስ አላት፡፡ የማታ ማታም ቢሆን እንበሳሜ ገብታ ማደሯ አይቀርም፡፡





ጧት ትምህርት ቤት ግቢ ስትደርስ ደሳለኝን ቀድሟት አገኘችው፡፡ ከመምህራን ማረፊያ ክፍል ሆኖ የፈተና ወረቀት ያርማል፡፡ ሰላምታ ስትሰጠው የመለሰላት በቀዘቀዘ ስሜት ነበር፡፡

«እንደምን አደርሽ ትሩፋት በሰላም ነው ጠፍተሽ የሰነበትሽው?» አላት እርማቱ ላይ እንዳተኮረ፡፡

«ምነው ፈልገኸኝ ነበር?» ስትል ጥያቄውን በጥያቄ መለሰች፡፡

«እኔ ብፈልግሽ ምን ዋጋ አለው? ያንቺ ቀልብ ያረፈው ሌላ ላይ፡፡»

«ከማን ላይ አረፈ ልትል ይሆን?»

«አገር አውርቶ የጨረሰውን፡፡ ያኔ እኔ ስጠይቅሽ ግን ወንድ የተባለ ፍጡር ለዘለዓለም ጥግሽ የምታስደርሺ አትመስይም ነበር» አላት የሚያርመውን የፈተና ወረቀት ትቶ ቀይ እስክርቢቶውን ጠረጴዛው ላይ ወርወር አድርጎ ትኩር ብሎ እየተመለከታት፡፡

«ምን ታደርገዋለህ? መታገል ሳይሆን መታደል ይሉታል እንግዲህ ይህንን ነው» አለችው፡፡ እጉል ላያምናት መከራከሩ እንደማይጠቅም ገብቷት፡፡

«ግን ትሩፌ ከኔ በምኑ በልጦ አገኘሽው? በሞቴ ይህንን ብቻ ንገሪኝ ማወቅ እፈልጋለሁ» አለ ደሳለኝ አይታውን እላይዋ ላይ ሳይነቅል፡፡

«ነገርኩህ እኮ ደሳለኝ፡፡ የማነስና የመብለጥ ጉዳይ አይደለም፡፡ እድል ነው፡፡ ጧቱኑ የመመረጥ እድል፡፡»

«እኔ ግን አይመስለኝም፡፡ ለመሆኑ ተያይዛችሁ የት ጠፍታችሁ ሰነበታችሁ?» አላትና ወደ ማረም ሥራው ተመለሰ፡፡

«ዓለም ሰፊ ናት፡፡ ከተፈለገ መሄጃ ይጠፋል ብለህ ነው ደሳለኝ» እያለችው እማዋይሽን ስትመጣ እየቻት፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የፈተና ወረቀቷን ሰባስባ ሰጠቻት፡፡

«አመሰግናለሁ እማዋይሽ! የጓደኛ እውራ ያድርግልኝ» አለቻት ትሩፋት ስትቀበላት፡፡

«ምንጊዜም ከጎንሽ ነኝ» አለች እማዋይሽ፡፡ የመጨረሻው ደወል ተደውሎ ወደ ቤቷ እስክትሄድ ድረስ የደሳለኝ አባባልና ግምት የብዙው የእንበሳሜ ኗሪ አስተያየት እንደ ሆነ እያሰበች ነበር፡፡ እንደ ሁልጊዜው ግን አላስጨነቃትም፡፡

«ስለ እኔና ይነበብ የሰው ሁሉ ግምት እንደ ደሳለኝ ከሆነ እንደውም ጥሩ ነው። ለድርጅታዊ ሥራችን ያመቻናል» ስትል ቀለል አድርጋ ወሰደችው።

******

አቶ ማንያዘዋል ሕመሙ ባይገላቸውም አስደንግጧቸዋል። ከዚያ ሕመም በኋላ ጧት ማታ የሚያስቡት ብዙ ስለመኖር አይደለም። እንደ ጓደኞቻቸው የመጀመሪያ ልጃቸውን ዓለም ማየት ሆኗል የቀን ሐሳባቸው--- የሌሊት ህልማቸው። የልጅ ልጅ ስም መሞት ሆኗል ጉጉታቸው። ገና መጥቶ ሄደ። ጥምቀት ተከተለ። በተስፋ ጠብቀውት የነበረው የትሩፋት ቃል ወሬውም የለ። ድምጿን አጥፍታለች። ፋሲካም ቀረበ። ትሩፋት ሆዬ በዝምታዋ እንደ ጸናች ናት። «እሺ» እንደ አባባሏ ወድያው የምታገባላቸው መስሏቸው ድል ያለ ሰርግ ሲሰርጉ እየታያቸው ደስ ብላቸው ነበር።

ትሩፋት ታናናሽ እህቶቿን እዚያው አንበሳሜ እያስተማረች ነው። ራሔልና ድልነሳ ደግሞ ከድል በኋላ ሕዝባዊ መንግሥት ሲቋቋም ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ። መቼም ሁሉም ነገር እንዲህ እንደ ሆነ አይቀጥም። አንድ ቀን መስመር ይይዛል። ለድርጅቷ የምታበረክተው እያንዳንዷ እንቅስቃሴዋ ወደ ድል እያቀረባት መሆኑን ስታስብ ኩራት ይሰማታል። የድሉን ቀን ለማቅረብ ከዚህ የበለጠ መስራት ብትችል ደግሞ ደስታዋ እጥፍ ድርብ ይሆን ነበር።

መቼም ዓለም አስር አትሞላም። አልፎ አልፎ አዕምሮዋን የሚያስጨንቅ ሐሳብ አላጣችም። የፍቅሩ ደብዛ መጥፋት የጎን ውጋት ሆኖባታል። ቃሏን ማጠፍ የተራራ ያህል ከብዷታል። እስከ መቼ ልትጠብቀው እንደምትችል ደግሞ አታውቅም። በሕይወት ለመኖሩም እርግጠኛ አይደለችም። ለዚህም ራሷን ጥፋተኛ ታደርጋለች። እሷን ብሎ እሷን ተከትሎ ነውና አሰመራ ሄዶ ምጽዋ ላይ ቀልጦ የቀረው። ይነበብ የሚሉት ሰው ደግሞ እንዲህ በዋዛ የሚታይ አልሆነም። ጧት ማታ እየተከታተለ ፈተናዋን አብዝቶታል። ልቧን ለፍቅር ገርበብ ያደረገ ጀግና ነው። በሩን ጭራሽ በርግዶ እንዳይገባ ያገደው የድርጅታቸው ዲሲፕሊንና ለፍቅሩ የገባችለት ቃል እየያዛት ሳይሆን አይቀርም። ፍቅሩም ቢሆን በቃለ-በላነት ሊፈርድባት አይችልም። ከሶስት ዓመታት በላይ ለስንት ጊዜ ልትጠብቀው ትችላለች? የአባቷን ጉዳይ ግን በዋዛ የምታልፈው አልሆነም ነጋ ጠባ መልዕክት እየላኩ ውጥር አድርገው ይዘዋታል። ጊዜ ሊሰጧት አልቻሉም። ለመጣ ለሄደው «ምነው ዝም አልሽሳ? ጉዳዩን ከምን አደረሽው?» እያሉ ሳይልኩባት የቀሩበት ቀን የለም። ደብዳቤ እየጻፉ መወትወታቸው ሰቀቀን ለቆባታል። «ሳልሞት ዓለምሽን አሳይኝ» የሚለውን አባባል እንደ ደርግ መንግሥት «ኢትዮጵያ ትቅደም» የዘወትር መፈክራቸው አድርገው ይዘውታል። ውስጧን ስትፈትሸው እሷም ብትሆን ፍቅር የሚሉት ጣጣ ሳይጀማምራት የቀረ አልመሰላትም።





«ባብዬ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ቢታገሱኝ አሁን ምን አለበት? እሱን ደስ ካለው በድል ማግስት አገባለት አልነበር።» ከአባቷ መልዕክት በደረሳት ቁጥር የምትለው ነው። የድሉ ቀን የተቆረጠለት-- በእጇ የጨበጠችው ይመስል። ለኢሕአፓ አካላት ፍቅር የተነሳ እውነታውን አምኖ መቀበል ተስኗት ነው እንጂ መሽቶ በነጋ ቁጥር የድሉ ቀን ከመቅረብ ይልቅ እንደ ሰማይ እየራቀ---እየራቀ እየሄደ ነው። እያደር ጉም እንደ መዝገን ያህል ባዶ እየሆነ።

«ምን ዓይነት አበሳ ነው? ሰንቱ ነገር ነው የሚያስጨንቀኝ ግን? የመንግሥት መፈናፈኛ ማሳጣት!-- በጉጉት የምንጠብቀው የድሉ ቀን መራቅ!-- የአግቢ ባዩ ውትወታ! --የአግቢኝ ባዩ መውጫ መግቢያ መንሳት! አሁንስ ሰለቸኝ። መቼ ይሆን የምፈልገውን ነገር በራሴ ጊዜ መወሰን የምችለው?» ተማረረች ትሩፋት። የሚገርመው ግን የአባቷ ውትወታ ይሁን የራሷ ፍላጎት እንደ ሌላው ጊዜ የጋብቻን ነገር ጨርሾ አይነሳብኝ አትልም። የሕይወት አንድ ምዕራፍ መሆኑን አምና ተቀብላ መለሳለስ ጀምራለች። ትዳርን ባሰበች ቁጥር ደግሞ ቶሎ በአዕምሮዋ የሚመጣው ይነበብ መሆኑ ያስደነግጣታል። ሆኖም ፍቅሩም ሊረሳት አልቻለም። የሐሳቧ አንድ ዘርፍ ሆኖ ይኸው ይወዘውዛታል።

«ብቻሽን ነሽ እንዴ» ይነበብ ነበር። ደነገጠች። ድምጹን እስከትሰማ ድረስ ኮቴ አልሰማችም ነበር።

«ሰራተኛሽ ስትወጣ እኔ ስገባ አንድ ሆነ። ልጆቹ የሉም እንዴ? ብቸኝነት እንዳይሰማሽ ይኸው እኔን ፈጠረልሽ» ብሎ ወደ ውሰጥ ተመለከተ። ሳታስበው በስሱ ከንፈሯ ላይ ሰሟት ሄዶ ፊት ለፊቷ ተቀመጠ። አቤት! እንደ ድሮው ቢሆን ኖሮ ይህን ጊዜ ቁጣዋ ሰማይ ጥግ በደረሰ ነበር። አንድ ጊዜ ደብረታቦር ስትማር የትምህርት ቤት ጓደኛዋ ከሆነ ልጅ ጋር ከንፈር በመሳም የተነሳ እስከ መደባደብ የደረሰችበትን ጊዜ መቼም አትረሳውም።

በወቅቱ የአስረኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። የዓመቱ ትምህርት ተጠናቆ ለክረምቱ እረፍት ትምህርት ቤት ሊዘጋ ሽር ጉድ በሚባልበት፣ እንደሁልጊዜው የወላጆች ቀን ከተከበረ በኋላ ነው። ተማሪው ሁሉ ለበዓሉ ዝግጅት ነፍሱን እያውቀውም። የተለያዩ የከበብ እንቅሲቃሴዎች ይታያሉ። በልጃገረድና በውድ ወርኪንግ ከበብ የተሰሩ የእጅ ሥራ ውጤቶች ለትምህርት ቤቱ ልዩ ገቢ ለሽያጭ ይቀርባሉ። ሹራቦች፣ የሰፋ ልብሶች፣ የአልጋ ልብሶች፣ በርሳዎች፣ ወንበሮች፣ ኩርሲዎች... ወላጆች በደስታ ይገዟቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የስፖርት ትዕይንቶች ይታያሉ። በድራማና ስነ-ጽሑፍ ከበብ ግጥሞች ይቀርባሉ። በተማሪዎች የተዘጋጁ ትያትሮች ይታያሉ። ልጅና ወላጅ የዓመቱን ጠቅላላ ውጤት የሚሰበሰቡበት ስለሆነ በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል። ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላ ደግሞ ተማሪዎች በየከፍሎቻቸው የመሰነባበቻ ግብዣ ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ ከተለመደው ሰዓት በላይ ቢያመሹም ወላጆቻቸው ጨክነው እንደማይጣሏቸው ያውቃሉ ።

ሰኔ በመሆኑ ይዘንባል። ጥሎበት ደብረታቦርን ደግሞ ዝናብ ይወደዋል። ለዐይን ያዝ በማድረጉ ፀሐይ ከትሩፋት ጋር ለማደር ተስማማችላትና ወደ አራዳ ገበያ መንገድ ጀመሩ። ተሻገርና ሙላት የሚሏቸው የክፍል ጓደኞቻቸው ደግሞ «አንሸኛችሁ» ብለው ተከተሏቸው። ዝናቡ ደግሞ ከፋኛ ያወርደዋል። ጨለማውንም አባብሶታል። አንድ ነጠላ ለሁለት ለብሰው ፊትና ኋላ ሆነው መጓዝ ጀመሩ። ፀሐይና ሙላት ወደ ፊት ገሰገሱ። የነትሩፋት ድምጽ መጥፋት ገርሟቸው ዘወር ሲሉ-- ሁለቱ ለካ ድብድብ ላይ ነበሩ። ተመልሰው ሄደው ካገላገሏቸው በኋላ የጠቡ መነሻ ምን እንደ ሆነ ጠየቋቸው። ተሻገር ከንፈር ለመሳም ያደረገው ሙከራ መሆኑን ትሩፋት ለትናገር በንዴት እየተንቀጠቀጠች ነበር። ተሻገር የሀፍረት ብልኮውን ተከናንቦ አንገቱን ደፍቶ ዝም ብሎ ቆሟል። ጎርፍ ላይ የወደቀውን ነጠላ አንስተው ሁለቱ እንደ ተኳረፉ ሸኝተዋቸው ተመለሱ። ብቻቸውን ሲሆኑ ፀሐይ

«ወይ ትሩፋት! ምን ሰይጣን የተጠናወተሽ ነሽ በእናትሽ! ልሳምሽ ያለሽን ሰው እንዲህ ጎርፍ ውስጥ ገብተሽ ድብድብ የገጠምሽው ቢነክለሽ ምን ልታደርጊው ነበር?» እየተገረመች ነበር የጠየቀቻት።

«የታባቱ! ድፍረቱስ አያናድድም!» ነበር መልሷ። ዛሬ ለይነበብ ተሻገር ላይ እንደ ሆነችው ቦከለ አልገጠመችም። ድርጊቱ ዛሬም ለእሷ ከብረ-ነክ ቢሆንም ብዙ እልተቆጣችም፤ ብቻ ደንገጥ አለች። ፍቅሩ በሐሳቧ ውልብ ብሎ አለፈ።

«እንዴ አንተ ልጅ! ምን እያደረክ ነው? በጣም አልተዳፈርከም። ብዙ መዘዝ እንዳይከተልህ። ስነ-ስርዓት ያዝ» ብላ ቆጣ አለች።

«ምን አደረኩ? ያፈቀርኳትን ልጅ ከንፈር ብስም ምንድነው ኃጢያቱ? አውቃለሁ--- የድርጅታችንን ሥነ-ሥርዓት እየጣስኩ እንደሆነ። ግን ምን ልሁን? ሥጋ ለባሽ ሰው ነኝ ተሸንፍኩ። የፍቅር አማልዕክት ከንፋቸውን ዘርግተው አንድ ተዓምር ካልፈጠሩ በስተቀር መውጫ ቀዳዳ የለኝም» አለ እንገቱን ወደ አንድ በኩል ዘንበል አድርጎና በትካዜ ወደ ውጭ እየተመለከተ።

«በአናትህ ይነበብ አትፈታተነኝ! ሌላው ቢቀር የተነሳንለትን ዓላማ አስበው። የዚህ የጭቁን ሕዝብ ነጻነት ሊቀድም ይገባል። በዚያ ላይ እኔ ቃል የገባሁለት ሰው መኖሩን ደጋግሜ ነግሬሃለሁ። አባክህ አማይሆን ነገር ውስጥ እኔንም አትክተተኝ።»

«አበድኩ ትሩፋት--አበድኩ። ለእብደቴ ማርከሻ መድሀኒቱ ደግሞ አንቺ ሆነሽ ተገኘሽ በቃ!»

«አይሆንም ይነበብ! አይደረግም! እሺ ለድርጅታችን የገባነው ቃልስ?» አለች ትሩፋት ጭንቅ እያላት።





«አላውቅም! ትሩፋት እኔ አላውቅም!» አላት ጭንቅላቱን እየነቀነቀ።

«አደጋ አለው እኮ ይነበብ ምን እየሆንክ ነው?»

«አውቃለሁ። ግን ምን ላድርግ ትሩፌ? ፊልጌ የሆንኩትን አልሆንኩም። ምርጫ የሌለው ሁለት ነገር ቀስፎ የያዘው ሰው ገጥሞሽ ያውቃል? በቃ! እኔ እንደዚያ ነው የሆንኩት። ከሁለታችሁም መነጠል አልችልም። ከአንቺም ከድርጅቴም። አንድ ነገር ግን እርግጠኛ ሆኜ ልንገርሽ። በፍቅር ምክንያት ለድርጅቴ መክፈል የሚገባኝን መስዋዕትነት ከመክፈል ቅንጣት ታክል አላፈገፍግም። እስከሞት ድረስ!» አላት ከረር አድርጎ።

«የድርጅታችንን ዲሲፕሊን መጠበቅ የመጀመሪያው መስዋዕትነት ነው። ራሱን ለዲሲፕሊን ያላስገዛ አባል ሌላ የሕይወት መስዋዕትነት ከቶ ሊከፍል አይችልም። ለዓላማው ቆርጦ አይታገልም ይነበብ ይግባህ!» ይህንን ትበል እንጂ የእሷም ልብ እየተሸረሸረች መሄዱ ተሰምቷታል።

«ለዘለዓለም ሴት ሳላፈቅር እንዲሁ ብቀር ምርጫዬ ነበር» አላት ትክዝ ብሎ። ለጥቂት ጊዜ በየራሳቸው ሲተክዙ ቆዩ።

«ያለምክንያት እቤት መምጣትህ ራሱ ተገቢ አይደለም» አለች ከቆይታ በኋላ።

«ያለምክንያት እንኳ አልመጣሁም። ሲጀምር አንቺ ራስሽ ዋናዋ ምክንያቴ ሆነሻል። ሁለተኛ ነገ አስቸኳይ ስብሰባ እንዳለን ልነግርሽ ነው። በታውም እዚሁ አንቺ ቤት እንዲሆን ተስማምተናል። ተዘገጃጂ። ልጆቹን በጊዜ ቦታ ቦታ አስይዢ» አላት።

ነገሮች ሁሉ እንዳሉ እንደ ነበሩ ናቸው። ደርግ የበላይነቱን እንደ ያዘ---ማሰር መጨፍጨፉንም እንደ ገፋበት። የጓዶች ሥጋት እንደ ቀጠለ----የተቀየረ ነገር የለም። ይመሻል ይነጋል። ሳምንት ይሄዳል ወር ይከተላል። ገና መጣ --ጥምቀት ተከተለ። ፋሲካም በጊዜዉ መጥቶ ሄደ። ከደርግ መንግሥት ጋር ግብግብ በመግጠም ስንት መስዋዕትነት የተከፈለለት የድል ቀን ላይመጣ እንደ ለማይ እየራቀ---እየራቀ---- ጊዜው ነጎደ። እነ ትሩፋት የጓጉለት ድል ሳይገኝ ልባቸው እንደ ተንጠለጠለች ቅድስ ዮሀንስ ባተ መስቀል ተተኮሰ። መስከረም መጣ--- መስከረም ሄደ። ዓመት አልፎ ዓመት ተተካ.....

## ድርብ ታጋይ

ፈረስ የሚያስጋልብ ባይሆንም የመንደሯን ሰዎች ከትት አድርጎ የሚይዝ ዳስ ተጥሏል። አብሮ አደግ ጓደኞቿ «ለዛሬ ያልሆነ ጓደኝነት....» በሚል ይመስላል ሽብ--ረብ ይላሉ ። የሙሽራው መቀመጫ ድንጋይ ተከቦ በሳር ድልዳል ከፍ ብሎ መድረከ ተዘጋጅቶለታል። አበባ ምንጣፍ ለብሶ የሳር ከምር መሆኑንን ማንም ሲያውቅ ቀርቶ ሲጠረጥር አይችልም። ለሙሽሮቹ መቀመጫ የሚሆን ሶፋ በአማረ ልብሰ አጊጦ መድረኩ ላይ ጉብ ብሏል። ከሙሽራው መቀመጫ ጀርባ ያለው ግድግዳ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ለብሶ ለዳሱ ልዩ ሞገሰ አጎናጽፎታል። የዳሱ ዙሪያ በአልጋ ልብሰና አበባ ምንጣፍ አሸብርቋል። የሰፈሩ አልጋ ልብሰ አንድ የቀረ አይመሰልም። የተንዘንዘው ጉዝጓዝ መጠጥ ብሎ ሲደርቅ የተቃረበ ቢሆንም የባህር ዛፉ፣ የአርቲው፣ የከሴውና የጠጅሳሩ ሽታ አውድ ሲያደርግ ሳያሰቡት አየር ደጋግሞ ወደ ውሰጥ ያሰባል።

አቶ ማንያዘዋል እንደ ተመኙት ግቢያቸው በሰርግ ዘፈን ድብልቅልቁ ወጥቷል:: ዛሬ የመጀመሪያ ልጃቸው ሰርግ ነው :: ህልማቸው አውን ሆኗል:: አሳቸው ግን በዚህ የደስታ ቀን የጎደለ ነገር ያለ ይመሰል ደርሶ ቅር ቅር እያላቸው ተቸግረዋል:: ሐሳባቸውን ማሰብሰብ አቅቷቸዋል:: እንዲህ እየዋለሉ ባሉበት ሰዓት ሦስት መኪኖች ተከታትለው መጥተው ዳሱ አጠገብ ቆሙ።

በአዲስ ዘመን ከተማ-- ጭቃ መንደር ውሰጥ በሦስት መኪና ሰትዳር ትሩፋት የመጀመርያዋ ናት። ሙሽራው ከመኪና ሲወርድ ሆሆታው ቀለጠ:: የአዲስ ዘመን ወጣት አንድ የቀረ አይመሰልም:: ጭቃ መንደር የሰው ጎርፍ ውጧታል:: ትሩፋትን በእጁ ያስገባው ጀግና ማን እንደሆነ ለማየት ሰው በሰው ላይ ይንባበራል:: ሙሽራው በሚዜዎቹ ታጅቦ ሴቷ ሙሽራ ወዳለችበት ቤት አመራ:: የሴት ሚዜ «አናስገባም» ብለው በር ዘግተው አገርግረው ቆመዋል:: እንገባለን--- አናስገባም በሚል የወንድና የሴት ሚዜዎች ግርግር ፈጠሩ:: የወንድ ሚዜ በአሸናፊነት ወጣ::

ሙሽራው ሙሽሪትን ከጎኑ ሻጥ አድርጎ ይዞ ሲወጣ ከበሮው እጅ አለኪ-ቃጠል ተመታ---- ጥሩንባው ተነፋ-ሆታው እስገመገመ--- እልልታው ቀለጠ:: የገደል ማሚቶ እልልታውን ተቀብላ ከተራራ ተራራ አስተጋባች። ዋኘታ ያደገችባት ሽኒ ወንዝ ፏፏቴዋን ከመልካ መልካ እያላጋች ከሰርገኛው ጋር አብራ አጨበጨበች። ጭቃ መንደር በወጣቶች ጭፈራ አቧራዋ ጤሰ። ሞሽሮቹ በጭፈራው እንደ ታጀቡ ቀሰሰ እያሉ ሄደው ዳሱ ውሰጥ በተዘጋጀላቸው የከብር መቀመጫ ላይ ተቀመጡ።

ይህ ሁሉ ሲሆን አቶ ማንያዘዋል እንዲያ የጓጓለት የትሩፋት ሰርግ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ የደስታው ተካፋይ አልሆኑም:: ቅር--ቅር የሚላቸው ነገር ጨርሶ አልተዋቸውም:: ምክንያቱን አሰቦ ለማግኘት ደግሞ በቂ ጊዜ አልነበራቸውም:: «እንዲህ ይሁን--እንዲያ





ይደረግ- እዚህ ይምጡ--እዚያ ይሂዱ---» እያለ በየቦታው የሚጎትታቸው እጅ በዝቶባቸዋል:: ሕሊናቸውን ሰብሰብ አድርገው ይህን አጉል ሰሜት መመርመር አልቻሉም:: ያሳደጓት ጎረቤቶቿ፣ አብሮ አደግ ጓደኞቿና የአዲስ ዘመን ኗሪ በሙሉ ግን ያለዛሬ ሰርግ የለም የተባለ ይመሰል ሁሉም የደሰታው ተካፋይ ሆነዋል::

«በእናትሽ ትሩፋትን እበኪ ተመልከቻት» አለች:: ልከየለሽ የምትባል የሰፈር ልጅ:: የትሩፋት አብሮ አደግ ናት::

«በጣም አምሮባታል! የለበሰችው የሙሽራ ልብሰ ነጭ ጽጌረዳ አሰመስሏታል» አለች በላይነሽ የምትባለዋ ሌላዋ አብሮ አደግ::

«እሱን መቼ አጣሁት:: ደስ ትላለች:: በ--ጣም ደስ ትላለች:: ግን ሆዷን ተመልከቺው እስቲ!»

«ምነው ምን ሆነ? ለእኔ ምንም አይታየኝም::» አለች በላይነሽ የትሩፋትን ሆድ እያሰተዋለች::

«ኧረ በእናትሽ በላይነሽ ተይ! ትሩፋትን አታውቂያትምና ነው:: ወገቧ ጭብጥ የማይሞላ-ሆዷ አህል በልቶ ያደረ የማይመሰል እልም ሙትት ያለ እኮ ነበር:: አሁን ግን እንጃ! ሞላ ያለ መሰለኝ» አለች ልከየለሽ የትሩፋትን ሆድ አትኩራ እየተመለከተች::

«ወይ አንቺ ልጅ! ለሰው ሁሉ ያልተገለጠ ምሥጢር ላንቺ ብቻ ይከሰትልሻል-- እ!? የለበሰችው የሙሽራ ልብሽ እኮ ነው:: ቡፍ ማለቱ ይቀራል:: ምን ልትይ እንደሆነ ገብቶኛል አርግዛለች ለማለት ነው አይደል? ምን ይሻልሻል በፈጠረሽ?» አለች በላይነሽ በትዝብት እያሰተዋለቻት::

«ኧረ እኔ አልወጣኝም! ሸንቧ ሞላ ያለ ሰለመሰለኝና.....» ብላ ዝም አለች ልከየለሽ::

«እና ምን?» ጠየቀች በላይነሽ::

«ሰርግ የሚሰረገው ኅኖን፣ ጥምቀትን እለዚያም ፋሲካን ጠብቆ ነው:: የትሩፋት ሰርግ ግን መስከረም ላይ መሆኑ ገርሞኛል::»

«መሰከረም ወር ለምን እንደማይሰረግ ታውቂያለሽ? ያለፈው ዓመት ምርት ያለቀበት--- መጭው አዲስ ምርት ደግሞ ገና ያልደረሰበት በመሆኑ ብቻ ነው:: ሰርግ ሁሉ ጥር ወይ ፋሲካ ላይ የሚሆነው አዲስ ምርት የሚገባበት ሰለሆነ እህልና ገንዘብ አይቸግርም:: በቃ! ሌላ የተለየ ምክንያት ኖሮት አይደለም» አለች በላይነሽ::

«እሱን አላውቅም ነበር» አለች ልከየለሽ::

«አንችስ ብትሆኚ እስቲ አሰቢው ከመስከረም የበለጠ ምን የሚያምር ወር አለ? ሜዳና ተራራው፣ ሸለቆውና ሸንተረሩ ሁሉ አበባ የሚለብሰበት! ጨለማ ተገፎ ብርሃን የሚበራበት:: ካልሸሰ እህሉ ሁሉ የሚደርስ ቢሆን ኖሮ እንደ መስከረም ለሰርግ ተመራጭ ወር ባልኖረም ነበር» አለች በላይነሽ የልከየለሽ የነገር አካሄድ እየገረማት::

«በበኩሌ የሚያስቸኩል ነገር ካላጋጠመ በስተቀር መስከረም ወር ላይ የሚሰረግ ሰርግ አይቼ አላውቅም::»

«ስሚ ልከየለሽ አትጨነቂ! እርግዝና ከሆነ ወሩን ጠብቆ ይወለዳል:: ደግሞስ ብታረግዥም እኮ አገባች በቃ! እንደ አንዳንዶቹ አባት የሌለው ልጅ አትታቀፍም» ብላ በነገር ጠቅ አደረገቻት:: ሌላ ወሬ ከመቀጠላቸው በፊት አንድ ቄስ መስቀላቸውን አስቀድመው ብድግ አሉ:: ዙሪያውን በቀይ ግምጃ የተዘመዘመ ዘርፋፋ ጥቁር ካባ ከኩታቸው በላይ ደርበዋል፡፡ የለበሱት ልብሰ-ተክህኖ ከስዕብናቸው በላይ አግዝፏቸዋል።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፋስ ቅዱስ ...» እራቱን ማዕዘን እየተሿሿሩ በብር መስቀላቸው አማተቡ፡፡ ድብልቅልቅ ሲል የነበረው የወጣቶች ዘፈንና ጭፈራ ጸጥ--- ረጭ አለ። ሁሉም ሰው አንገቱን በአከብሮት ደፋ ደፋ አድርጎ የቄሱን ቡራኬ ማዳመጥ ያዘ::

«የወልደ ጌዎርጊስንና የወለተ ተክለሃይምኖትን ጋብቻ የአብርሃምንና የሳራን ጋብቻ የባረከ ልዑል እግዚአብሄር ይባከልን» ሲሉ እድምተኛው በሙሉ በአንድ ድምጽ «አሜን» አለ። ድምጹ ቀትር ላይ ከቀፎው እንደ ወጣ ንብ ተመመ። ቄሱ ጎልቶ በማይሰማ ድምጽ በግዕዝ ማነብነባቸውንና ቡራኬ መስጠታቸውን ቀጠሉ። ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ሁለት ዲያቆናች ከቄሱ ኋላ ቆመዋል። አንደኛው በአሰላ የተንቆጠቆጥች ትንሽ ሙዳይ ይዟል። ሙሽሮቹ ወደ ቄሱ እንዲቀርቡ ታዘዙ። ሙዳዩዋን የያዘው ዲያቆን ዞሮ ከቄሱ ፊት ከሙሽሮቹ ጋር አብሮ ቀረበ፡፡ ቄሱ ሙሽሮቹን በያዙት መስቀል ባረኩ:: ሙሽሮቹ በአከብሮት ከወገባቸው ዝቅ እያሉ መስቀሉን ተሳለሙ። ዲያቆኑ ሙዳዩዋን ከፈተና ወደ ቄሱ አቀረበ፡፡ ቄሱ ጸሎታቸውን ሳያቋርጡ የተከፈተችዋን ሙዳይ አሁንም በመስቀላቸው ሦስት ጊዜ ባረኩ::

ዲያቆኑ አንደኛዋን ቀለበት አውጥቶ ለቄሱ አቀበላቸው:: ቄሱ ጸሎታቸውን በለሆሳስ እየደገሙ ቀለበቷን ለወንዱ ሙሽራ ሰጡት:: በሴቷ ሙሽራ ጣት ላይ አጠለቀ። አልሌታውና ጭብጨባው ዳሱን አነቃነቀው። አሁንም ሌላኛውን ቀለበት ዲያቆኑ አቀበላቸው:: ቄሱ ጸሎታቸውን አላቋረጡም:: ቀለበቱን ለሴቷ ሙሽራ አቀብላለሁ ሲሉ እጃቸው ላይ አምልጦ ወደቀ:: ከተጎዘጎዘዉ ሳር ውስጥ ገብቶ ሰመጠ። ቄሱ መስቀላቸውን እንደ ያዙ የጨው አምድ መስለው እንደ ቆሙ ቀሩ። ሰርገኛ ሁሉ «እኔ አገኙ- እኔ አገኙ» ተተረማማሰ:: ጉዝጓዙ የባሰ ተረጋገጠ። በፍለጋ ብዙ ቢደከምም ቀለበቱ





ደብዛው ጠፋ። ለጊዜው የተውሶ ቀለበት መጥቶ ትሩፋት ወንዱ ሙሽራ ጣት ላይ አጠለቀች:: የቀለበቱ መጥፋት ከባድ ድንጋጤ ቢፈጥርም የሰርጉ ስነ ሰርዓት ቀጠለ። ቄሱ እንደ ደነገጡ ደመነፍሳቸውን በአቡነዘበሰማያት አሳርገው ከተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ ሄደው ሲቀመጡ የመውደቅ ያህል ዘፍ ብለው ነበር። ወጣቶች ጭፈራውን ወዲያው ቀጠሉ:: ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ሰርጉን ሲያደምቁት አፍታም አልወሰዱ::

አሞራው ሲያይሽ ዋለ--ሲያይሽ ዋለ፣

የይነበብ ነሽ እያለ-- የይነበብ ነሽ እያለ::

አሞራው ሲያይህ ዋለ --ሲያይህ ዋለ፣

የትሩፋት ነህ እያለ---- የትሩፋት ነህ እያለ::

በትሩፋት ሰርግ የጭቃ መንደር ወጣት እንገት እንደ ትሩፋት ሰርግ ከቶም አልታየ ተባለ። ሁሉም ነብሱን የሳተ እስኪመስል ድረስ ጨፈረ ዓለም ቀለጠች!--- ።

አሞራው ሲያይሽ ዋለ---- ሲያይህ ዋለ፣

ተነሽ ለትግሉ እያለ----- ተነስ ለትግሉ እያለ::

አሞራው ሲያየን ዋለ---- ሲያየን ዋለ፣

የትግሉ ናችሁ እያለ-- የትግሉ ነን እያለ::

አሞራው ሲያየን ዋለ--ሲያየን ዋለ፣

የሕዝብ ልጆች እያለ--የሕዝብ ነን እያለ::

ትግሉስ የነበር ነው -- ትግሉስ የነበር ነው፣

ቆራጥንቱ የራሷ ነው--- ቆራጥነቱ የራሱ ነው፣

ቆራጥነቱ የእኛ እኮ ነው—የእኛ እኮ ነው::

በምን ቅጽበት የሰርጉ ዘፈን ይዘት ወደ አብዮታዊ ቅስቀሳ እንደ ተለወጠ ከወጣቶቹ በስተቀር የሚያውቅ የለም:: ማንን ተው! ብሎ ማስቆም ይቻላል? ሁሉም ወጣት--- በወጣትነት ትኩስ ስሜት ያበደበት የፖለቲካ መድረክ እስኪመስል ድረስ ግጥሞች መፈክሮች ሁሉ ተኽጎደጎዱ:: ወጣትነት ድፍረት--- ወጣትነት ጀግንነት--- ወጣትነት

አይበገሬነት ነው፡፡ ፖሊሶች ደግሞ ከመቼው ወሬው ደርሷቸው—ከመቼው ከተፍ እንዳሉ ፍጥነታቸው ከንፋስ ቀድሟል! አካባቢውን በቁጥጥር ስር አዋሉት፡፡ ዘፈኑ ወዲያው ቆመ፡፡ ወጣትና ፖሊስ ፊት ለፊት ተፋጠጡ፡፡ ቀደም ሲል ቀለበት ጠፍቶ ያ ሁሉ ትርምስ ተፈጠረ፡፡ አሁን ደግሞ ደም ሊያፋስስ የሚችል ሌላ ችግር-- ሌላ ድንጋጤ ተከሰተ!

አቶ ማንያዘዋል «ዛሬ የመጨረሻ ዓለሜ ነው---- የመጨረሻ ደስታዬ ነው፡፡» ባሉት የመጀመሪያ ልጃቸው ሰርግ ላይ-- በደስታቸው መሀል ይኸ አስደንጋጭ ክስተት እንደሚፈጠር ውቃቢያቸው ነግሯቸዋል፡፡ ያለ ነገር ዕቃ እንደ ጠፋው ሰው ቅር ቅር ሲላቸው አልዋለም፡፡ ባልጠበቁት ሁኔታ ጉዳያቸው የነበር ወግና ባህሉን አጥቶ ሊበላሽባቸው ሆነ፡፡ በጣም ደንግጠው የሚይዙትን የሚጨብጡትን አጡ፡፡

«እባካችሁ እነዚህን ፖሊሶች ገላግሉኝ!» አሉ የአገር ሽማግሌዎችን አስነስተው፡፡ «ተከብሬ በኖርኩበት አገር ከእንዲህ ያለ ፈተና ላይ ሰወድቅ ዝም ብላችሁ አትዩኝ፡፡ አንድ ነገር ብላችሁ ከጉድ አውጡኝ! የዛሬን ቅበሩኝ!» አሉ አቶ ማንያዘዋል። የአገር ሽማግሌዎች ተነስተው ፖሊሶችን መማጸን ያዙ፡፡ የወጣቶችን ጥፋት ሳይሆን የአቶ ማንያዘዋልን ጉዳይ አይተው የዛሬን ምህረት እንዲያወርዱ ለመኑ፡፡ ፖሊሶች ግን «በአብዮቱና በእናት አገር ቀልድ የለም!» በሚል ዓይነት አሻፈረን አሉ፡፡ ሰርጉ ላይ ያለውን ወጣት በሙሉ አፍሰው ለመውሰድ አሰፈሰፉ፡፡ የአበራሽ መኖር ግን ሁኔታውን ቀየረው፡፡

«እዚህ ያሉት ወጣቶች በሙሉ ፀረ-አብዮተኞች ናቸው ማለት አይቻልም» አለች አበራሽ ፖሊሶችን ለብቻቸው ወደ አንድ ጥግ ወስዳ፡፡ «ከመካከላቸው ይህን ተንኮል የፈጸመው አንድ ወይ ሁለት ወጣት ቢሆኑ ነው፡፡ በሰርግ ላይ የደርግ ወታደሮች በጠበጡ፤ የሰርግ ስነስርዓት አበላሹ ተብሎ ወሬ እንዲነዛና የአብዮታችንን መልካም ገጽታ ጥላሸት ለመቀባት ሆን ተብሎ የተሸረበ ሴራ ነው፡፡ አብዮታችን በሕዝብ ዘንድ ያለውን ተቀባይነትና ድጋፍ ለማሳጣት በፀረ-አብዮተኞች የተቀነባበረ ተንኮልና ደባ መሆኑን መጠርጠር ተገቢ ነው» ብላ ንግግሯን ቆም አድርጋ ተመለከተቻቸው፡፡ ወታደሮቹ ቁጣቸው እየበረደላቸው መምጣቱን አስተዋለች፡፡

«እያችሁ ጓዶች! በዚህ አስቸጋሪ የአብዮት ወቅት ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡ ዛሬ በተከሰተው ሁኔታ እነዚህን ወጣቶች በሙሉ አፍሳችሁ ብታስሩ ትርፉ በሕዝብ ዘንድ መጠላትና የአብዮት ኪሳራ ማድረስ ነው፡፡ ጉዳዩን በይደር ያዙት፡፡ ከነገ ጀምሮ ግን ያላሰለሰ ክትትል አድርጉ፡፡ ይዋል ይደር እንጂ ፀረ-አብዮተኛውን ወጣት ማወቃችሁ አይቀርም፡፡ ዛሬ ግን የሰርጉ ስነስርዓት ይቀጥል፡፡ ለማንም ተብሎ ሳይሆን ለአብዮታችን መልካም ስም ሲባል» አለች አበራሽ፡፡

በስልጣን ደረጃዋ ከእነሱ ይልቅ እሷ ከፍ ትላለች፡፡ የክፍለ ሀገሩ የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ናት፡፡ በጉዳዩ እሷ ትጠየቅበት ብለው ፖሊሶቹ ሀላፊነታቸውን አወረዱ፡፡ የተፈጠረው





ውጥረት ረገበ፡፡ ወታደሮቹ ዳሱ ውስጥ ገብተው የሰርጉ ተካፋይ ሆኑ። ከግብዣው በኋላ ወጥተው ሊሄዱ ግን ወጣቶችን በንዴት በቀሉ ዐይኖቻቸዉ እየገላመጧቸው ነበር። ወጣቶቹ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ ወደ ቀድሞ የሰርግ ጭፈራቸው ገብተዋል። ምንም ያህል አልቆዩም መልሰው አካባቢውን በዘፈን ሲያደምቁት-- አካባቢው መልሶ የሰርግ ድባቡን ተላበሰ።

አቶ ማንያዘዋል ከመጀመርያው ነገሩ ሁሉ አላማራቸውም። ሙሽራው ዘግይቶ ነበር የደረሰው። አማቻቸው ልክ የሰርጉ ቀን አጣዳፊ ድርጅታዊ ሥራ ነበረው። ጅግና ኪዳነምህረት ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ለኢሕአፓ ምልምል ገበሬዎች ትጥቅ የሚሰጥበት ቀን ነበር። በአፋኙ የደርግ መንግሥት እጅ እንዳይወድቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡ ከእሱ ውጭ ይህንን ኃላፊነት ሊወስድ የሚችል ሌላ ጓድ አልነበረም። የዚያ አካባቢ የገበሬ አደራጅ ሆኖ ስመንግስት እንዲቀጠርና ሽፋን እንዲሆነው የተደረገበት ዋናው ተልዕኮው ይኸው ነው፡፡ በመንግሥትና በድርጅታዊ ሥራ ነፍሱ በወስፈንጠር እንደ ተያዘች ወፍ በምትቃትትበት በዚህ ወቅት ለካ እሱ ሙሽራ ኖሯል። ይባስ ብሎ አስቸኳይ የበላይ ትዕዛዝ የደረሰው ደግሞ በዚሁ በሰርጉ እለት ነበር። አቶ ማንያዘዋል አማቻቸው ገበሬ ሲያነቃ፣ ሲያደራጅና ሲያስታጥቅ ሰዓቱ የሄደበት መሆኑን አላወቁም የንቀት መሰሏቸው ተናደዱ፡፡ ስንት መኳንንት «ልጅህን ስልጃችን» እያለ ለምኗቸው ነበር፡፡ እጉል ሰልጥነው የባል ምርጫውን ለእሷ በመስጠታቸው ተቆጩ፡፡ አሁን ባለቀ ሰዓት «አይሆንም ልጄን እንዲህ ላለ አማች አልሰጥም» አይሉ ነገር ወዳጅ ዘመድ ጠርተው ዳሱ ከእፉ እስከ ገደፉ በሰው ጢም ብሏል። ንዴታቸው ተጎልጉለው ሊወጡ በደረሱ ትላልቅ ድፍርስ ዐይኖቻቸው ይንበለበላል። እሳት ጎርሰው እሳት ይተፉሉ። ቁጣቸውን ጣሪያ ያደረሰው ደግሞ አማቻቸው ብቻ አልነበረም። የገዛ ልጃቸው ትሩፋትም ጭምር ነበረች። እንደ ሴት ሙሽራነቷ መለንበቻውን ከወላጆቿ ቤት መከተት ነበረባት። ይባስ ብላ እሷም ቢሆን ከወንዱ ሙሽራ ጋር የተቀዳደመችው የአንድ ሰዓት ልዩነት ቢሆን ነው።

«ቀረች! ኧረ--ቀረች! ኧረ ጉድ ነው! በዚህ በሰርጓ ቀን ምን ነካት? ምን ጉድጓድ ዋጣት» እያሉ አብሮ አደግ ጓደኞቿና ያሳደጓት ጎረቤቶች ሁሉ በጭንቀት ተውጠው ሲንቆራጠጡ የመምጣቷ ወሬ ተሰማ፡፡ ሁሉም ከምጥ የተገላገለ ያህል ነበር የቆጠረው፡፡ «ተመስገን ፈጣሪ ከጉድ አወጣኸን!» ያላለ ወዳጅ ዘመድ አልነበረም።

ትሩፋት ራሷ ልክ የሰርጓ እለት ከድርጅቷ ሥራ ተሰጥቷት ነበር። የሚነበቡ የዲሞክራሲያ ልሳኖች የሚደርሳቸው ጓዶች ይጠብቋታል። ስነገ ይደር የማትለው ሁሉም ነገር ከፍተኛ ሚሥጢርና ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሥራ ነበር፡፡ ትንሽ እንኳ የጊዜ ዝንፈት ቢያጋጥም የሕይወት መስዋዕትነት ሊያስከፍል ሁሉ ይችላል፡፡ የመርፌ ቀዳዳን ያክል የጠበበ አስጨናቂ ጊዜ ላይ ነበረች።

በጠዋት ነበር የወጣችው። የመሞሸሪያ ጊዜው ደግሞ ለከፋቱ ቶሎ ቶሎ ሰዓቱ መድረሱ እየታያት ነው። ግዴታዋን ተወጥታ በሩጫ እያለከለከች ሀሙሲት ደረሰች። አንድ ከባህርዳር ከመጣ አውቶብሰ ውሰጥ ከሰንት ሰው ጋር ተጋፍታ በመከራ ገባች። የተሳፈረችበት አሮጌ አውቶብስ ደግሞ ወረታ ሲደርስ ጥቂት ሲቀረው ተበላሸና ተንገጫግጮ ቆመ። ትሩፋት ተጨነቀች፡፡ ትንፋሿ ቀጥ ሊል ምንም ያህል አልቀረውም፡፡ ሌላ መኪና ይመጣል ብላ መንገድ መንገዱን ብታይ ያን ቀን ደግሞ ለከፋቱ ብቅ ያለ መኪና አልነበረም። እንደ እሞራ አትብር ነገር ገራ ገባት። የአባቷን ሁኔታ ማሰብ አትፈልግም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ያሉበትን ንዴት ባሰበችው ቁጥር ራሷን አዞሮ ሊያሳብዳት ይደርሳል፡፡ አሰር አስር ጊዜ ሰዓቷን እያየች ከወዲያ ወዲህ ስትንቆራጠጥ በረዳቱና በሹፌሩ ተንራጉሮ እንደ ምንም ተነሳና ጉዞውን ጀመረ ያው ጥርሰ ምላሱን የፈጀው አሮጌ መኪና።

ሙሽራዋ በሌለችበት ዘፈኑ ቀልጧል፡፡ ከርቀት ነበር የሰማችው፡፡ የአባቷን ቤት ግድግዳ ተንተርሶ የተንጣለለውን ዳስ አየችው፡፡ እየቀረበች ስትመጣ ያች ያደገችባት እንደ ነፍሷ የምትወዳት ጭቃ መንደር የጦር ሰፈር መሰላ ታየቻት፡፡ ፈራች-- በጣም ፈራች፡፡ እንደ ሰረቀ ሰው ሹልከ--- ሹከከ ብላ እማማ ታገኝ ቤት ገባች። ከሰርጉ ቀድተው ገና መግባታቸው ነበር፡፡ ሲያዩዋት አይናቸውን አላመኑም፡፡ እማማ ታገኝ ከሰማይ የወረደች ነበር የመሰላቸው ።

«ትሩፋቴ እውን አንቺነሽ ልጄ!?» አሉ ከተቀመጡባት ትንሽ ዱካ ላይ ብድግ እያሉ፡፡ «እርግ ተመስገን! እመቤቴ ማርያም ምስጋና ይግባሽ!» ብለው ጉንጭና ጉንጪን አገላብጠው ሳሚት፡፡ ጥቂት ሳይቆዩ ግን ቁጣቸው ገነፈለባቸው፡፡

«ምነው? ምነው ልጄ!? እንዲህ ታሰጨንቂነ፤ የምንኸድበት-- የምንገባበት ቀዳዳ ጠፍቶነ ሰንጓለል እኮ ነው ያረፈድነ! ሰማይ ምድሩ ተደፍቶብነ ሰርጉም ሰርግ አልመሰለነ! ምኑ አውሬ ዋጠሽ ብለን የምንጠይቀው ወፍ አጥተን ከትናንት ጀምሮ ግራ ግብ--ት ብሎን እኮ ነው ያለነ፡፡ ያባትሽ ነገርማ ምኑ ተነሰቶ! እሳቸው ሰራሳቸው ውትሮም ጥቂት ነው የሚበቃቸው፡፡ እረ ዛሬስ በአሳቸውም ፍርድ የለ ይገባቸዋል!»

«ፈቃድ አጥቼ እኮ ነው እማማ እታገኝ። የመንግሥት ሥራ ዝም ብሎ ጥሎ ብድግ ተብሎ አይምጣ ነገር» አለች፡፡ የአባቷ ንዴት ከወዲሁ አሰፈርቷት ዐይናቸውን ማየት አያስጨነቃት።

«ኢዩ ወዲያ ዝም በይ! ቀጣፊ! ከመቼ ወዲህ ነው ደሞ እንዲህ ያል ቅጥፈት የተሰተማርሽው!? ቅዳሜና እሁድ መስሪያ ቤቱ ሁሉ ዝግ መሆኑ ጠፍቶኝ! የሰርግሽን ቀን ጠብቆ ከፍት የሚሆን መሰሪያ ቤት ዛሬ ሰአንቺ ሲሆን ተገኘልሽ! የመላሽ አሰማማር! በይ ይኸንን እጉል መላሽን እንደ እኔ ሌላ ሰው ሰምቶት እንዳይታዘብሽ!» አሉ እማማ እታገኝ፡፡





ስለዋሸቻቸው ይበልጥ እየተቆጡ፡፡ ትሩፋት መልስ አልነበራትም፡፡ እንገቷን ደፍታ ዝም አለች፡፡-

«ሲሆን ሲሆን የወርና የሁለት ወር ፈቃድ ወሰደሽ ካባትሽ ቤት ቀድመሽ መከተት ነበረብሽ፡፡ አላወቅሽውም እንጂ ከብሩ ላንችው ነበር፡፡ እንዴው ወጉ እንኳ እንዳይቀር ሳምንት! ሳምንት! ካባት ቤት መሞሽር እንዴት ይቅር!? አላየንም ሙሽራ!! እረ እንዴት ካለው ጊዜ ላይ ደረሰነ! እረ ምን የተረገመ ጊዜ መጣብነ!!» እየተማረሩ ጮሁባት፡፡ እማማ ታገኝ እንዲህ የሆኑ-- አባቷ የሚሆኑትንማ ጭራሽ ማሰብ ከበዳት፡፡

«በኛ ጊዜማ ሙሽራ ከወላጆቿ ቤት አስቀድማ ነው የምትከተት። ቅቤዋን እየተቀባች-- እየታጠበች-- እንሶስላዋን እየሞቀች ባደሱ፣ በጠጆሳሩ፣ በአሪቲው እየታጠነች ወዟ እንደ ቅቤ ቅል እየተንጨፈጨፈ በዜት ባየናት ታሰኛለች፡፡ የሚያውቃት ሰው ሁሉ ሲያያት ይጓጓል። አንች ካናካቴው በሰቱለትም ጠፍተሽ ምጥ አሰገብተሽነ አረፈድሽ፡፡ ጉድ! የጉድ ዘመን!! »

«እሺ አሁን አይቆጡ....»

«እረ ወድያ ዝም በይ! ደሞ አፉለኝ ብለሽ ስትሞጣሞጭ አታፍሪም!? አላየነም ሙሽራ እያ! እንዴው የአሁን ዘመን ልጆች ስትባሉ ነገራችሁም ከሰው አይገጥም፡፡ ከኔያችሁም አይገባኝ! ግራ ገብቷችሁ ግራ የምታጋቡ ጉዶች!» ወቀሳቸውን ደረደሩ። የድርጅቷ ተልዕኮ ሆኖባት--- የዓላማ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ከወግ ከባሕሉ አንጻር ስትመለከተው እሷም ቢሆን ጥፋተኝነት ተሰምቷታል፡፡

«ሕባክዎ ልጅ ይላኩና አበራሽን ያሰጠሩልኝ፡፡» አለች ቁጣቸው በረድ ማለቱን አይታ፡፡

«ይች ጠይሟን አይደል?» አሉ እማማ ታገኝ፡፡ በመጠኑም ቢሆን ቀዝቀዝ ማለት ጀምረዋል፡፡ «ሕሷም ቀረሽ ብላ በር--በሩን ሰታይና ስትጨነቅ ነው ያረፈደች፡፡ እንዴው ነፍስሽ ይገኛል ያለ ሰው አለ መሰለሽ ልጄ! ጉድ እኮ ነው የሰራሽነ ጉድ!» ካሉ በኋላ «ጠይሟን ይቺ ዐይኗ ጎላ ጎላ ያለውን አይደል ትጠራልኝ የምትይው?» ሲሉ ደግመው ጠየቋት፡፡

«አዎ እሷን ነው የሚላክ ልጅ...» ብላ ዝም አለች፡፡

«እረ እኔ ኸጄ እጠራታለሁ፡፡ አሁን በጅ ብሎ የሚላክ ኩታራም አይገኝ፡፡ ልጁ ሁሉ ዳሱ ውስጥ በዘፈኑ እያበደ ነፍሱንም አያውቀው። እኔው ራሴ አኸዳለሁ፤ በዚያውም የምሰራቹን ላባትሽ ልንገር» ብለው እየተጣደፉ ወጥተው ሄዱ፡፡

ጓደኞቿ ተከታትለው ገቡ። እነሱም እንደ ማማ እታገኝ ከሰማይ የወረደች ነበር የመሰላቸው። በጭንቀት መንገድ መንገዱን ሲያዩ ነበር ያረፈዱት። አበራሽ ትናንት ነው ከጎንደር የመጣች። ዋናዋን ሙሽራ በሰርጓ እለት እንኳ እንዳትገኝ ያደረጋት ከፍተኛ የፖለቲካ ተልዕኮ ሊሆን እንደሚችል ገምቷለች:: ድርጊቱ ከንክኗታል:: ሆኖም ግን ለጊዜው ምንም ማንሳት አልፈለገችም:: ለውይይት የሚሆን ጊዜም አልነበራቸውም:: እቅላቸው ሁሉ ሰርጉ ላይ ነበር::

«ቀረሽ ብዬ እንደ ፈረደብኝ እኔው ራሴ ልሞሽር ነበር::እግዜር እወጣኝ!» አለች አበራሽ:: ሁሉም እያቀፉ ከሳሟት በኋላ::

«ዘገየሽ አበራሽ! እስከ አሁንስ ለምን አልተሞሸርሽም ነበር? አንደኛ ሚዜ ማለት እኮ ዋናዋ ሙሽራ ባልተገኘችበት ቦታ ሁሉ ተከቶ ጎደሎውን እየሞሉ መገኘት ነበር:: ዝም ብሎ የክብር ቦታውን መያዝ ብቻ አልነበረም::» አለች ትሩፋት አበራሽን በፈገግታ እየተመለከተች::

«ዋ---! የሌሊቱንም እኔው እሞላውና ጉድ እንዳላደርግሽ ትሩፌ! ብትጠነቀቂ ይሻልሻል!»

«አሁንማ ዋናዋ ሙሽራ ተገኝቻለሁ:: ቅድሙኑ ቀረብሽ» አለች ትሩፋት እየሳቀች::

«ከአሁን አሁን ትመጫለሽ እየተባለ ነዋ! እኔማ መቼም አልቀረልኝ ብዬ ተዘጋጅቼ ነበር። ታዲያ ጓደኛ ለመቼ ነው? ኢታይም አሳሳች ሙሽራ መሰያለሁ እኮ!» አለች አበራሽ ሽከርከር ብላ ሁለመናዋን እያሳየች:: እውነትም ሙሽራ መስላለች:: ትላልቅ ዐይኖቿ ከኩሉ ጋር እንደ ፈርጥ ይቦገቦጋሉ። እጭር ጸጉሯ ተተኩሶ ግንባሯ ላይ ደፋ በማለቱ ረዘም ያለው ፊቷን በመጠኑም ቢሆን ከብብ ያለ አስመስሎታል። የለበሰችው ሮዝ ማክሲ ቀሚስ ጥይም ፊቷን ፈካ አድርጎታል:: የፈከች ጽጌረዳ መስላለች:: እውነትም ብትሞሽር ያምርባት ነበር።

«ይልቅስ የሚዜ ፈዛዛ የለውም ለዚ እንዳትባሉ:: የወንድ ሚዜ ሳይመጣባችሁ ቶሎ-ቶሎ ብታሰማምሩኝ ይሻላችኋል። ቆማችሁ ወሬ ከምትሰልቁ:: ለዛሬ ንግስታችሁ እኔ ነኝ:: በአሰቸኳይ ትዕዛዜን ተቀበሉ» አለች ትሩፋት። የሚያጠፉት ጊዜ አልነበራቸውም። ቶሎ ቶሎ ገላዋን አጠቡ---ጸጉሯን ፈቱ---በየቦርሳቸው የያዙትን ማስዋቢያ ሁሉ ተጠቅመው አሰማመሯት። የሙሽራ ልብሏን ሲያለብሷት ለዘመኑ «እዩኝ--እዩኝ» የምትል ውብ ሙሽራ ሆነች። እሷ ግን ጧት ስትባዝን ያረፈደችበት ሳይሆን አይቀርም ተሞሽራ ቁጭ ስትል ጊዜ ድካም ለቀቀባት:: ሰውነቷ ሁሉ ቁርጥርጥ ያለ መሰላት::

እቶ ማንያዘዋል የትሩፋት መምጣት ሲነገራቸው በውስጣቸው «እፎይ» ቢሉም ቁጣቸው አልበረደላቸውም ነበር:: እንደ ልጅነቷ ጊዜ እጇን ይዘው ባለንጋ ሸጥ--ሸጥ ማድረግ ቢችሉ ኖሮ እንዴት በወደዱ!!





ሙሽሮቹ ግርማ ሞገስ ተላብሰው ከፍ ብሎ ከተዘጋጀላቸው መድረክ ላይ ጉብ ብለዋል:: በሥራ ገጠር ለገጠር ሲባከኑ የዋሉ አይመስሉም:: ከሁሉም ይበልጥ ወጣትነት ያረበበት ገጽታቸው እንዳች መስህብ ነበረው። የሚያውቃቸውም--- ያማያውቃቸውም ሊያያቸው ይንጠራራል። ሰው በሰው ላይ እየተደራረበ ይጋፋል::

ሙሽራው ተመርቆ ትሩፋት ያደገችባትን ሰፈር ጭቃ መንደርንና የእባቷን ቤት ለቃ ስትወጣ ፀሐይ ወደ ማደሪያዋ እየገሰገሰች ነበር። የጭቃ መንደር እብሮ እደግ ጓደኞቿ ያለዚያች ቀን ጭፈራ የለም የተባሉ ይመስል አቧራዉ እስኪጤስ ሆሆታውን እስነኩት---እንገት በሮ ሊሄድ እስኪመስል ድረስ እስክስታውን አወረዱት---- እናቶች እልልታውን እቀለጡት--- እዛውንቶች ምርቃትን እኽጎደጎዱት---- ጭቃ መንደር ልጇን መርቃ ሰጠች::

የትሩፋት ማንያዘዋልና የይነበብ መዝገቡ ትልቁ ትዳር ተመሰረተ.....

******

«ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት አሁኑኑ!!» የሚለው የኢሕአፓ መፈክር የብዙውን ወጣት ቀልብ ገዝቷል:: ከደርግ መንግሥት ጋር ጉሩቦ ለጉሩቦ እያስተናነቀው ይገኛል:: በኢትዮጵያ ምድር ጫፍ እስከጫፍ በእብዛኛው ሕዝብ በተለይ ወጣቱ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሰረት ዘንድ ሕይወቱን አሳልፎ እየሰጠ ነው:: የወታደራዊው የደርግ መንግሥት ደግሞ ሰልጣን ጥምታል:: ወንበሩን አደላድሎ የሙጥኝ ብሏል:: በዚህ ትንቅንቅ ዳግም የማትገኝን እንድያ ነፍስ እንዱ ለጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምሰረታ ሌላው የያዘውን ሰልጣን ላለማጣት እንደ ቅጠል እየቀጠፉት ይገኛል። ኢሕአፓ አባሎቿን የደርግ መንግሥት ከፉኛ በሚጨፈጭፍበት በዚህ ወላኝ የትግል ወቅት ዖታዊ ግንኙነት እጥብቆ የተከለከለ መሆኑን አስታውቃለች:: ደጋግማ አስጠንቅቃለች። ትሩፋትና ይነበብ ግን የፍቅር ዛር ሰፍሮባቸው የድርጅታቸውን ደንብ ጣሱ:: የፍቅር ዛሩ ማርከሻ ደግሞ ትዳር ሆነ። ፍቅር ከሁሉም በላይ ኃያል መሆኗን አስመሰከረች:: ምድራዊ ሕግና ደንብን ጣሰች። በትግል መድረክ ላይ ድንኳኗን እብራ ተከለች::

ትሩፋት ከተለመደው የሰብሰባ ሰዓት ውጭ እሸቸኳይ የሰብሰባ ጥሪ ደረሳት:: በተባለው ቦታና ሰዓት ስትደርስ አራቱ ቀድመዋታል:: ይነበብ ከሥራ እንደ ወጣ ወደተባለው የሰብሰባ ሰፍራ ነበር ያመራው:: እንደ ሌላው ጊዜ የኢንፎርሜሽን ልውውጥ እንኳ አልተካሄደም:: ቀጥታ ወደ መልዕከቱ ነበር የገባው ዘመድሁን::

«ጓዶች የዛሬው አሰቸኳይ ሰብሰባ ያስፈለገው ከድርጅታችን ሥነ-ሥርዓትና ደንብ ውጭ የተፈጸመ ጉዳይ በመኖሩ ነው:: የምንወያይበት አጀንዳ የለንም:: መልዕከትና ውሳኔ ማላወቅ ብቻ ነው» አለ ዘመድሁን:: ቁጥ--ር ከሰከሰ ያለው ገጽታው ያስፈራል::

«ወይ ጉዳችን! ምን ይወሰንብን ይሆን?» አለች ትሩፋት ለራሷ:: ዘመድሁን የሥነ ሥርዓት ጉድለት መሆኑን ሲናገር እነሱን የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን አላጣችውም:: ይነበብ የመጣውን ለመቀበል የተዘጋጀ በሚመስል ቆራትነት ኮስተር ብሎ ያዳምጣል:: ትሩፋት ዐይኗን ጣል አድርጋበት ቶሎ መለሰ አደረገች::

«ጊዜው የትግል ነው፤ ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ላይ የደረስንበት:: እያሌ ጓዶቻችን በደርግ የአፈና መረብ ውስጥ የወደቁበት---በየእስር ቤቱ የሰው ልጅ ይችለዋል ተብሎ ሊታሰብ የማይቻል ስቃይ እየተቀበሉ ያሉበት---ጥፍሮቻቸው በፈላ ዘይት እየተነከሩ በጉጠት እየተነቀሉ የሚገኙበት----በወንዶች ብልት ላይ ውሃ የያዘ ጠርሙስ እየተንጠለጠለ ፋሽስታዊ ደርጊት የሚፈጸምበት አስቃቂ ጊዜ:: ሴት ጓዶቻችንን አስገድዶ እስከ መድፈር-እንሰቶ ብዙ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ አፀያፊ ግፍ እየተቀበሉ ያሉበት---- ጓዶቻቸውን ላለማጋለጥ ለድርጅታቸው ዲሲፕሊን በመገዛት ሰቃይና መከራ እየተቀበሉ በየስር ቤቱ እየማቀቁ የሚገኙበት።» ዘመድሁን በጓዶች ላይ የሚደርሰውን ስቆቃ፣ ግፍና መከራ ሲናገር አንዳንዴ እንባው እየተናነቀው ድምጹ ሰርቅርቅ ይልና ንግግሩን ቆም ያደርጋል:: ትሩፋት ለድርጅቷ ስነ-ስርዓትና ደንብ ባለመገዛቷ ጥፋተኝነት ተሰምቷታል:: ውስጥ ውስጧን ፀፀት እያንገበገባት ነው:: ራሷን ኮነነች:: ዘመድሁን ደግሞ በዚች ሰዓትና ጊዜ ጓዶች እየከፈሉ ያለውን መስዋዕትነት እያነሳ በፀፀት የቆሰለች ልቧን ይበልጥ ያደማት ጀመር::

«በደርግ መንግስት ፋሽስታዊ ጭካኔ በድብደባ ብዛት የነደለው አካላቸዉ-- የፈሰሰዉ ደማቸዉ ሲጠራን--- ጩኸቱና ዋይታው ሊሰማን ይገባል:: በቀይ ሽብር በፋሽስቱ ጥይት ተመትተው ከቡሩ የሰው ልጅ ከውሻ አሰከሬን አንኳ አንሶ በየጎዳናው ተጥሏል:: በየዋሻው ወድቋል:: በየሜዳው ተዘርግቷል:: ይህን የመሰለ ዘግናኝ ግፍ የተቀበሉ ጓዶቻችንን ሬሳ በዐይናችን የተመለከትነው ሀቅ ነው:: ከኛስ ምን ይጠበቃል? ለግል ኑሮ መሽቀዳደም? ወይስ ለነፃነት የምንከፍለውን ዋጋ ከፍ ማድረግ? በጅምላ ተጨፍጭፈው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ በዓሪደር አፈር የተመለሰባቸው ጓዶቻችን ድምጽ ከመቃብር ይጮሃል!!» ጥርሱን ነከሰ ዘመድኩን፤ እልህ የተናነቀው ይመስላል:: እሱ እንዲህ በተናገረ ቁጥር ትሩፋት ደግሞ በደለኝነቷ እንደ ቋጥኝ እየተቆለለ ከምትሸከመው በላይ ሆኖ ከበዳት::ይነበብ ምንም ነገር ፊቱ ላይ አይታይም:: ኮስተር እንዳለ ነው::

«በየበረሃው ከደርግ ፋሽሽታዊ ወታደር ጋር ጎሮሮ ለጎሮሮ ተናንቀው የወደቁ ጓዶቻችን አፅም እየወጋ ለድል የምናደርገውን ጉዞ እናቅርበው ዘንድ ሊያነሳሳን ይገባል። ይህ የጭቁን ሕዝብ አደራ---የትውልድ አደራ-- ብሎም የደርጅታችን ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድ ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለብን ትውልዶች ነን:: ለግል ስሜታችን ተቸንፈን ለፍቅር ድሪያ የምናውለው ጊዜና ጉልበት ሊኖር ፈጽሞ አይገባም:: ትዳር መስርተን በፍቅር የምንምነሸነሽበት ጊዜ ላይ ነን እንዴ ጓዶች?» ብሎ ትሩፋትንና ይነበብን ተመለከታቸው:: ሲናገር በሰሜት ነው:: የጓዶችን ስቃይ በተናገረ ቁጥር ፊንጣጣ ወጋ ወጋ ባደረገው ፊቱ ላይ ሀዘንና ጭንቀት ይነበባል። አንዳንዴም ጠበብ ባለችው ዐይኑ እንባው ግጥም ይላል።





ድምጹ ስልቱን ያጣል:: ግራ እጁ ሰላላ ነው። ውጊያ ላይ ተመትቶ እንደሆን ሁሉም ጓድ ያውቃል። እሱ ግን ትንፍሽ ብሎ አያወጣትም። በቅሎ ላይ ወድቆ እንደ ተሰበረ ያስወራል። ወደ ከተማ የውስጥ ትግል የተመለሰውም በዚሁ በእጁ ምክንያት እንደሆነ ውስጥ ውስጡን ይወራል። ሲስቅ ትናንሽ ዐይኖቹ እብረው ይስቃሉ:: እንዲህ እንዳሁኑ ሀዘን ሲገባው ደግሞ ከጉድጓዳቸው ገብተው ይደበቃሉ:: የትሩፋትና የይነበብ ጋብቻ በአንበሳሜ ከተማ የኢሕአፓ ንዑስ ኮሚቴ ቀርቦ እየታየ ነው። ከአባልነትም ሊያሰርዛቸው ይችላል። ቡተለይ ዘመድሁንን በጣም ያሳዘነውና ያበሳጨው ይመስላል።

«ድርጅታችን ከተማ ውስጥ በደርግና በመኢሶን መንታ ጦር እየተወጋች ነው። ትግራይ ውስጥ አሲንባ ላይ የተመሰረተው ቤዛችን በጠባቦችና በጎጠኞች ህወሀትና ሻብያ በደረሰብን መሰሪ የከህደት ሴራ እንድናጣው ተደርጓል:: የአሲንባ የጦር ቤዛችንን ላለመልቀቅ በተደረገው እውደ ውጊያ ላይ የወደቁት ጓዶቻችን ቁጥር የትየለሌ ነው:: ወደፊት ታሪክ የሚዘከረው ይሆናል። በሁለቱ ጠባብ ጎጠኛ ቡድኖች ከህደትና ሸፍጥ ማጣት የሌለብንን ጓዱቻችንን አጥተናል። ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ አንድነት ጠላቶቻችን ብዙ ናቸው:: በማይረባ የዓለም ሕይወትና የሥጋ ፍላጎት መዘናጋት የዚህ ትውልድ እጣ ፈንታ አይደለም:: ለድል መፍጠን ይኖርብናል። ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ እውነተኛ ነፃነት ቀን ከሌት መሮጥ ይጠበቅብናል» ብሎ ለእፍታ ተክዝ ብሎ ቆዬ::

«ለመሆኑ የታጋይ ድምጽ ይጮሃል--- ይጮሃል ከመቃብር፤

ትግሉን እፋፍም ይላል----ተከቶን ታጋይ እልፏል፤

ትግላችን ይቀጥላል!!..... የሚለውን መዝሙር እንዲሁ ለይስሙላ ነበር እንዴ ስንዘምር የነበረው? ሲል ዐይኑን ትሩፋት ላይ ተከለ:: ትሩፋት አንገቷን ደፋች::

«የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ለዚህ የትግል ታሪክ የተጠራን ትውልዶች ነን። ሰማችን፣ ንብረታችንና በአጠቃላይ እኛነታችን የምናወርሰው ለወለድነው ልጅ ሳይሆን ለተጠራንበት የታሪክ ጥሪ ነው። ለምንመሰርተው ነፃ ትውልድ!!- ልንገነባት ላሰብናት ነፃነት-- ፍትህ-- እኩልነት ለሰፈነባት ኢትዮጵያ!! ይህ የታሪክ ጥሪ የዚህ ትውልድ ዕጣ ፈንታ ነው:: ይህ ደግሞ ተራ የውስጥ ስሜትን አይደለም የሕይወት መሰዋዕትነት የሚያስከፍል መሆኑን ጓድ ይነበብና ጓድ ትሩፋት ታጡታላችሁ ብዬ አልገምትም። ለሕይወት መሰዋዕትነት ዝግጁ የሆነ ቆራጥ ታጋይ ደግሞ ለስጋ ፍላጎት አይቸነፍም። እናንተ ግን የድርጅታችን ዲሰፕሊን ጥሳችኋል:: ለግል ስሜታችሁ ተገዥ ሆናችኋል:: ትዳር ከትግል ሜዳ በጅጉ ያዘናጋል፤ ምክንያቱም ትዳር ከፍ ያለ ኃላፊነት ይጠይቃልና። ስለሆነም የበላይ አካል ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ በድርጅቱ ውስጥ የምታደርጉት እንቅስቃሴ ከዛሬ ጀምሮ ለጊዜው ይቆማል» አለ ዘመድኩን:: ስብሰባው በዘመድሁን የንዴትና የቁጭት ንግግር ብቻ ተደመደመ:: ማንም አባል አስተያየት፣ ተጨማሪ፣ ተቃውሞ፣ ጥያቄ፣ ማስተካከያ፣

ሚስኮት፣ ሚስ እንደርስታንድ፣ ሰሞሽን ይቅረብ...... አያለ ሐሳብ የሰጠ አልነበረም:: ከዘመድሁን ረኘም የወቅቱ ገለጻ በኋላ የትሩፋትንና የይነበብን ላልታወቀና ላልተወሰነ ጊዜ ከድርጅቱ መገለልን አርድቶ ስብሰባው በዚሁ ተጠናቀቀ::

ትሩፋትና ይነበብ ከሁለት ወር ቆይታ በኋላ በፊት የነበራቸው የድርጅት ፍቅርና የተግባር እንቅስቃሴ ታይቶላቸው በጠንካራ ሂስና የገንዘብ ቅጣት ታለፉ:: እንደተለመደው የቀድሞ ሥራቸውን ቀጠሉ። ሕይወት ዳግም ነፍስ ዘራች:: ከደስታ ጋር መኖር ተጀመረ::

******

ሀሎ---!ሀሎ---! በአንበሳሜ ከተማ ለምትገኙ ወጣቶች በሙሉ:: ለአስቸኳይ ስብሰባ ስለምትፈለጉ በቀበሌው ጽ/ቤት ግቢ ልክ ከጧቱ ሶስት ሰዓት ላይ እንድትገኙ በጥብቅ እናሳስባለን! በማይገኙ ወጣቶች ላይ ሕጋዊ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን ከወዲሁ በጥብቅ እናስታውቃለን! የወረዳው— አስተዳደር!

«ዛሬ ደሞ ምን ተገኝቶ ይሆን» አሉ እዛውንቱ ሸበቶ ጸጉራቸውን እከክ እከክ እያደረጉ። ቡና ለሚጠጡት ተርቲመኞች።

«ለዚያው የዘመቻ ምልመላ ይሆናላ!» አሉ ቡና ያፈሉት እማ አዛለች:: የዛሬው ጧት ቡና ተራ የሳቸው ነው:: ጎረቤቱ ሁሉ ተሰባስቧል። የቡና ቁርስ ገብስና ሽንብራ ቆሎ ተቀላቅሎ በእለላ በተንቆጠቆጠች ቆለምሽሽ ከእዛዉንቱ ፊት ቀርቧል:: አንድ አራት ስኒዎች በአንዲት እንስተኛ ጣውላ ተደርድረው ይታያሉ:: ጣውላዋ ከስኒው ተርፎ አሳይዋ ላይ የሚፈሰውን ቡና እየጠጣች ሳይሆን አይቀርም ቡናውን መለላ ጠቁራለች:: የቤቱ ባለቤት ምድጃው ላይ እሳት በገል ጭረው ያጤሱትን ጡንጅት በሩ ስር አስቀመጡት:: የጡንጅቱ ጢስ ያደረውን የቤት ጠረን በጥሩ መዓዛው ሰወጠው::

ከሁሉም በአድማ ገፋ ያሉት አባ አበጀ ከፊታቸው በትንሽ ቆለምሽሽ የቀረበውን የገብስና የሽንብራ ቆሎ እየዛገኑ ሰቡና ተርቲመኛው ሁሉ እንድታድል ከፊታቸው ለቆመችው ልጅ ይሰጧታል:: በግምት አስራ ሁለት ዓመት ይሆናታል። ቆሎውን ከእጃቸው እየተቀበለች ሰቡና ታዳሚው ሁሉ ታድላለች:: እማ እዛለች ቡናውን እምድጃው ላይ አውርደው ለመቅዳት ሲዘጋጁ ሁሉ ልጅቱ እንደቆመች ነበር:: ቡናውንም ለማቀበል:: ጀበናውን ቀስ አድርገው እንስተው ጨረር አድርገው ቀዱ:: የፈረስ ጭራ የመሰለ የሰከነ ቡናቸው ገና ሲኒው ላይ ሲያዩት ያስጎመጃል። እንደ አድማ ተዋረዱ በተራ ይታደላል:: የቡና ስኒው የማይዳረስ ከሆነ በእድሜ እንስተኛው ይቆያል። ሰኒው በውሃ እየተለቀለቀ ላልደረሰው ይዳረሳል::

«እንዴው ለመሆኑ የትኛው ጥሊያን—የትኛው ድርቡሽ መጥቶ ይሆን ዘመቻ--- ዘመቻ የሚባለው? ገና ሰማይና ምድር በወጉ ሳይላቀቅ ይኸ ሁሉ ለፈፋ ምን የሚሉት እብደት





ነው? አስታራቂ ሁነኛ ያገር ሽማግሌ ጠፍቶ እንዲህ ወንድማማች እርስ በርሱ ተላልቆ ይሙት! ኧረ እንዴት ታለው ክፉ ጊዜ ላይ ደረስነ! በመልክና በሐይማኖት የማይመስለን ጠላት አልመጣብን! የውጭ ጠላት ተመጣማ ማን ይቀራል? በዛስ ጉልበታችን እኛስ ቢሆን መዝመታችን ይቀር ነበር» አሉ አባ አበጀ::

«ያች አባ የሚሏት ሰይጣን አንዱን ወደል ባለስልጣን ገልብጣው ኸዳ ይሆናላ! እሷ እንደ ሆነች በሰንት ጦር ተከበ ቢጠበቅም አያመልጣት:: እንዲህ በጧት እንደ ቆሰለ አውሬ የሚያስጓራቸው የጤናቸው አይደለም» አለ:: ሌላው፣ የጠጣበትን ስኒ ከተቀመጠበት ተንጠራርቶ ለቡና ቀጅዋ እያቀበለ።

«ልጅቱ የቆመችው እኮ ፍንጃል ለማቀበል ነው:: ለምን ትንጠራራለህ? አንቺ ምን እፍዞ አቆመሽ!? ቶሎ ብለሽ አትቀበይውም ኑሯል? ለዚሁ ሙያ መስሎኝ የቆምሽው! የዘመኑ ልጆች ሲባሉ ወሬ ሲወራ አፍ አፍ ሲያዩ ሥራ መች ልብ ብለው ይሰራሉ» አሉ እማ እዛች:: ስኒውን ከሰውየው እጅ እየተቀበሉ::

«አልተንጠራራሁም ኧረ! እጄ ረጅም ነው ይደርሳል:: የሚያሳስበውስ የዚህ የጥሩንባ ለፈፋ ነገር:: አባ ጉድ ሳታደርጋቸው አልቀረችም:: እንግዲህ እንደ ፈረደብነ እኛው እንሰብሰብና እኛው ስንሰደብና ስንወቀስ ውለን እንምጣ:: አባን እንደሆነ የትም አያገኟትም:: ሰማይ ቢወጡ ምድር ቢቧጥጡ» አለ ደግሞ::

«ያች አባ የሚሏት ጉድማ የማትሰራው ምን ታምር አለ? በለንት ጦር የሚጠበቅ ባንክ በጠራራ ጣሀይ ዘርፋ ጥርግ ስትል በር ላይ የቆመው ዘበኛ በዜት ገብታ በዜት እንደ ወጣች እንኳ ጨርሶ አያያትም አሉ:: ምኑን ያፍዝ ያደንግዝ እንደምትረጭንባቸው እግዜር ይወቅ» አለ ሌላው ጎልማሳ እየሳቀ:: እማ በለጡ የሚሏቸው ጎረቤት ደግሞ

«አባ የሚሏት ደሞ የዜት አገር ሰው ናት?» ሲሉ ጠየቁ ወደ እማ እዛች አንገታቸውን ዘንበል አድርገው በሹክሹክታ::

«ኧረ እኔ ወት አባቴ አውቄያት:: አገሯ ወደ ዜቱ እንደ ሆነም አልሰማሁ:: ተዚሁ ቡኑ ላይ ነው ውቂው ደብልቂው ሲሉ የምሰማቸው:: አባ የሚሏት ፍጥረት ዛር ትሁን ቆሌ ነገሯም አይገባኝ» አሉ እማ እዛች:: እሳቸውም በሹክሹክታ::

ኢሕአፓ የሰራችውም ያልሰራችውም ገድል ተጋኖ ይወራል፣ ቡና ተርቲም ላይ---ገበያ ውስጥ--ግብርና ደቦ ላይ-- በየመሸታ ቤቱ --- በየእድሩ --- በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ሁሉ ሳይቀር የትም ---የትም በሹክሹክታ የሚወራው ወሬ ሁሉ ስለ ኢሕአፓ ገድል ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ አገሌ የተባለው ባለስልጣን ከዳ--- አገሌ ሸፈተ---ታሰረ---እጁን ሰጠ---ተረሸነ---የወታደር ምልመላ ሊካሄድ ነው ---ስንቅ ዝግጅት ታዘዘ --- ቀበሌ ስብሰባ ጠራ ---በተሄደበት ቦታ ሁሉ የሚሰማው ይኸው ብቻ ነው። የሽብር ወሬ--- ዘመነ ሽብር...

የወረዳው አስተዳደር ይህን አስቸኳይ ጥሪ ያስተላለፈው ለወረዳው አስተዳደር ተላላኪና ለወረዳው ፖሊስ አዛዥ አድራሻ የሌለው ፖስታ ከደረሳቸው በኋላ ነበር። ሁለቱ ሰዎች አገር ሰላም ብለው በቢሯት ሲነሱ በራቸው ስር አድራሻ የሌለው ፖስታ ያገኛሉ። ከው! ብለው ደንግጠው እየተርበተበቱ ፖሊስ ጣቢያ ይደርሳሉ። ሁለቱም ያልተከፈተ ፖስታ በእጃቸው ይዘዋል፡፡ «ለእኔ ብቻ አይደለም» በሚል ሁለቱም ጓዳዊ በሆነ ስሜት ተያዩ። «ሊይዞን» ተባብለው ለእለቱ ተረኛ ፖሊስ ያስረከባሉ፡፡ ስለሁኔታው ቃላቸውን ይሰጣሉ። የወረዳው ፖሊስ አዛዥ አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ አስተዳደሩን ያሳስባል፡፡ የወረዳው አዘአኮ ኮሚቴ ለአስቸኳይ ስብሰባ ተቀመጠ፡፡ በስብሰባው ፊት ያለ አድራሻ በበር ስር የተሳኩት ሁለቱ ፖስታዎች ተከፈቱ፡፡ የተፈራው አልቀረም የወረዳው ፖሊስ አዛዥና የአስተዳዳሩ ተላላኪ ሰውን ያለ ወንጀሉ ከማንገላታት ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ያስጠነቅቃል፡፡ በእነሱ የሀሰት ጥቆማ ብዙ ሰው መታሰሩን፣ መንገላታቱንና የቀይ ሽብር ሰላባ የሆነ መኖሩን በምሬት ያትታል ደብዳቤው፡፡ ከእንግዲህ ከዚህ ድርጊታቸው ካልተገቱና በተሰይ ገበሬው ላይ የሚያደርሱትን ግፍና በደል ካላቆሙ ሕይወታቸው አደጋ ላይ መሆኑን እንዲያውቁት በአጽንኦት ያስጠነቅቃል።

«አሺ ጓዶች የደብዳቤውን ይዘት የሰማችሁት ነው። ዛሬ አቤታችን ድረስ ማስጠንቀቂያ ካመጡልን ነገ አንድ ባንድ ይለቅሙናል፡፡ እርምጃ መውሰድ ያለብን ሳንቀደም ነው፡፡ ነገሩን በጥልቀት አይታችሁት አብዮታችንን ላለማስቀልበስ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል መወያየት አለብን» አለ አስር አለቃ እንተነህ የተንጠሰጠለች ትንሽ በርጩን እያሻሸ፡፡ የደራ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ---የወረዳው አዘአኮ ዋና ሰብሳቢ---የወረዳው አብዮታዊ ጸጥታ አስጠባቂ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ ነው። ስልጣን ካቅሙ በላይ በዝቶበታል፡፡ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ የአስር አልቅና ማዕረጉን ማንም አንስቷት አያውቅም፡፡ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ እንደ ሀውልት ደርቅ ብሎ ቁጭ ብሏል፡፡ የወረዳው አስተዳደር ተላላኪ ደግሞ በወጥመድ እንደ ተያዘች አይጥ ዐይኖቹ ፈጠዋል፡፡ ፊት ለፊት ከተቀመጡት አንድ እጅ ወጣ፡፡ እንዲናገር ተፈቀደለት

«በሰላም እንዳንኖር የሚበጠብጡን ወጣቶች ናቸው፡፡ ዝም ካልናቸው ወረዳችን የፀረ-አብዮት ካምፕ ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ አስቀድመን የነቃንባቸው መሆኑን እንዲረዱት በሙሉ ታፍሰው ጣቢያ ይግቡ፡፡ ወንጀለኛው በምርመራ ይገኛል» አለ አንድ የወረዳው ካድሬ፡፡

«ለዚህ ሐሳብ ተጨማሪ ወይም ተቃውሞ አለ?» ሲል ሰብሳቢው ጠየቀ፡፡ አንድ እጅ ወደ ጥግ በኩል ወጣ፡፡

«እንድናገር እድሉ ስለ ተሰጠኝ አመሰግናለሁ» አለ ረጋ ያለ ሰው ነው። «በደም ፍላት የማይሆን እርምጃ ወስደን ነገሮች ይበልጥ እንዳይበላሹ ጥንቃቄ እንዲደርግ እሳሰባለሁ፡፡ በወረዳችን ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን በሙሉ ማሰር ማለት ነገ ፀረ-አብዮት ካምፕ እየሄደ





የሚቀላቀል አባል በራሳችን ፋቃድ አዘጋጀንላቸው ማለት ነው፡፡ ዛሬ ወጣቶችን በሙሉ ብናስር ነገ ወላጆቻቸው ፀረ-አብዮት ድርጅቶችን የማይደግፉበት ምን ምክንያት ይኖራል?» የሚል ጥያቄ አቀረበና ተሰብሳቢውን ሁሉ በገረፍታ ተመለከተ፡፡ «እንደ እኔ ሐሳብ ከሆን ወጣቱ ትውልድ የነገ አገር ተረካቢ ነው፡፡ ልንከባከበው ይገባል፡፡ በብልሃትና በዘዴ ይዘናቸው የአብዮቱ ደጋፊዎች ሊሆኑ የሚችሉ ወጣቶችን አሰበርግገን ማጣት ያለብን አይመስለኝም፡፡ የምንወስደው እርምጃ ሁሉ በስሜት ሳይሆን አብዮቱን ከመጥቀም አኳያ እየታየና እየተመዘነ ሊሆን ይገባል፡፡ ፀረ አብዮተኞችን ብቻ ለይተን የምንመታበት መንገድ በጥንቃቄ ተጠንቶ እርምጃው እንዲወሰድ እሳስባለሁ፡፡ አመሰግናለሁ» አለ፡፡ ፖሊስ አዛዡ ድንገት ከድንጋጤው እንደባነነ ሁሉ እጁን እንኳ ሳያወጣ

«ጓድ አብዮታዊ መሪያችን እንዳሉት አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ተሸጋግሯል፡፡ ለዚህ የበቃነው ፀረ-አብዮተኞችን በጉያችን ሸጉጠን አሽሩሩ እያልን አይደለም፡፡ አብዮቱ ባጎናጸፈን ዲሞክራሲያዊ መብት ተጠቀመን ስታሊናዊ ሰይፍ መዘንባቸው ነው! በአብዮት ሰይፍ ስለ ቀላናቸው ነው!» አለ ከላይ የቀረበውን ሐሳብ የሰጠውን ሰው እየገላመጠ፡፡ «የስንት ጓዶቻችን ደም የፈሰሰለት አብዮት ሲቀለበስ እጃችንን አጣጥፈን ቁጭ ልንቀመጥ አይገባም፡፡ የምናካሄደው አብዮት ነው፡፡ አብዮት ደግሞ ልጇን ትበላለች፡፡ ስለዚህ ሁሉም ወጣቶች ሊታሰሩና አብዮታዊ ምርመራ ሊካሄድባቸው ይገባል፡፡ ከወጣቶቹ በስተቀር ይህንን የፀረ--አብዮት ድርጊት በዚህ አካባቢ ሊሠራ የሚችል ሌላ ኃይል አይኖርም» ከመናደዱ የተነሳ ሲናገር እጁ ይንቀጠቀጣል። ያለበውን ሰፊ ፈጣጣ ግንባሩን ጭብጥብጥ ያለች መሀረም አውጥቶ ጠራረገ፡፡ የተለየ ሐሳብ እንደ አለ ሰብሳቢው ጠየቀ፡፡ ሌላ እጅ ከመሀል ወጣ፡፡

«የኔ አስተያየት የሚያተኩረው በተለይ ትምህርታቸውን አቋርጠው በመጡ ወጣቶች ላይ ይሆናል፡፡ ትምህርታቸውን ማቋረጣቸው በራሱ የመንግስት ፖሊሲ መቃወም ነው። በወረዳችን ተሰግስገው የሚገኙት እነዚህ ወጣቶች ትምህርታቸውን ያቋረጡት ለጤና አይመስለኝም፡፡ ይህንን የማስጠንቀቂያ ጽሑፍ ከነሱ ውጭ ሌላ ሰው ይጽፈዋል ብዬ አላምንም፡፡ ስለዚህ የትኩረት አቅጣጫችንን ወደነሱ ብናደርግ የተሻለ ውጤት እናገኛለን ብዬ አምናለሁ አመሰግናለሁ» አለ፡፡

«ጓድ ተዘራ ሐሳብህ ጥሩ ነበር፡፡ ነገር ግን በሌላ መልኩም ቢሆን የትምህርት ቤቶች መዘጋት ውስጥ ውስጡን የመንግሥት እጅም አለበት። እንደምታውቁት ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ከተገኙ ሰላም አይሰጡም፡፡ ለፀረ አብዮተኞች ደግሞ አንድ ላይ የተገኘን ኃይል ለማደራጀትና ለመቀሰቀስ ያመቻቸዋል። አብዮታችን ስር እስኪይዝና በሁለት እግሩ እስኪቆም ድረስ ጊዜ ለመግዛት የተማሪዎች መበታተን ተፈላጊና ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ መንግሥት እንደ መልካም አጋጣሚ ነው የቆጠረው፡፡ አሁን በደረሰው ጉዳይ ላይ ብቻ ተነጋግረን መወሰን የሚገባንን ወስነን እንለያይ» አለ ሰብሳቢው በመሰላቸት፡፡ የወረዳው መርማሪ ፖሊስ እጁን አወጣ፡፡

«ሁሉንም ወጣት አፍሶ ማሰር ከሕግ አኳያም ሲታይ አግባብነት የለውም:: በወረዳችን የሚገኙት ወጣቶች እስከ አሁን እንደ ሌላው አካባቢ ከቁጥጥር የወጣ ብዙ አስቸጋሪ ነገር አልፈጠሩብንም። ዛሬ ባጋጠመን ጉዳይ ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያመቸን እዚህ ከተማው ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች  በሙሉ በቀበሌ ጥሪ ይደረግላቸው» ብሎ እህ ህ! አለና ድምጹን አስተካክሎ ንግግሩን ቀጠለ:: «ሁሉም ወጣቶች የናሙና ጽሑፍ እና የእጅ አሻራ ይስጡ:: የናሙና ጽሑፉ እና የእጅ አሻራው ጎንደር ለዋናው ፖሊስ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ይላክ:: በዘመናዊ መሳርያ ምርመራ ይካሄድበት:: በምርመራው ውጤት መሰረት ወንጀለኛው ማን ሊሆን እንደሚችል ማወቅ እንችላለን:: በእርግጥ ከሥራ ብዛት የተነሳ የምርመራው ውጤት ቶሎ ላይሠራና ላይመጣ ይችላል:: ሆኖም ሁሉንም ወጣት አፍሶ ንጹሃንን ጭምር ከማሰር  ጊዜ ወስዶ  መረጃ መጠበቁ  ሳይሻል አይቀርም» አለ::

 በመጨረሻም ወጣቶቹ ብቻ ሳይሆኑ የመንግስት ሰራተኞችና እንዳንድ የከተማዋ ተጠርጣሪ ኗሪዎች ጭምር የእጅ ጽሑፎቻቸውንና አሻራ እንዲሰጡ ተወስኖ ስብሰባው ተበተነ:: በከተማው እየተዞረ ጥሪ የተደረገው ለዚሁ ተግባር ነው::

ትሩፋት ፖሊስ ጣቢያ ሄዳ የእጅ ጽሑፍ ናሙና እና አሻራ  ሰጥታ ስትመለስ መንገዱን ሁሉ በሐሳብ እየተብሰለሰለች ነበር:: መጀመሪያ ላይ የተካራየቻትን ቤት ወንድሟ ድልነሳና ጓደኞቹ ሲያጸዱ በወጣትነት ትኩስ ስሜት ተውጠው

«የወረዳው ተላላኪ እኮ ጀሮ ነው::»

«ሲያየን ደሙ የሚፈላው ለዚህ ነው? ግደላቸው ቢባል እኮ ሁላችንም ቢጨርሰን በወደደ::»

«ለምን ማስጠንቀቂያ አንሰጠውም.....» የተናገሩት ንግግር ሁሉ በእዝነ ህሊናዋ መጣ። ሁሉንም የወንድሟ ጓደኞች በዐይነ ህሊናዋ ተመለከተቻቸው። ሁሉንም አንድ በአንድ በልቧ ሚዛን መዘነቻቸው።

«ማን ጽፎት ይሆን?» እገሌ ነው ብላ  መልስ መስጠት አልቻለችም::  መቋጫ የሌለው ሐሳብ ይዞ ሲወዘውዛት በሆዷ ያለው ሽል ተገላበጠ፤ አቅለሸለሻት። እቤት ስትገባ ይነበብን አገኘችው:: ከመስከ ሥራ ገና መግባቱ ነበር:: ሲያገኛት ልክ ብዙ ጊዜ ተለይቷት እንደ ቆየ ሁሉ ሰፍሰፍ ብሎ እቅፍ አድርጎ ሳማት:: ምሳ ቀርቦ እየበሉ ሰለ ተፈጠረው ሁኔታ በሰፊው ተወያዩ:: በነዚህ ሁለት ሰዎች ተግባር የተናደዱ ወጣቶች በግብታዊነት በግላቸው የፈጸሙት መሆኑን አላጡትም:: ያለ መመሪያና ያለ እዝ ሰንሰለት ዝም ብሎ በደም ፍላት የሚሠራ ሥራ ሁሉ ለድርጅታቸው ሕልውና  አሰጊ ሊሆንም ይችላል:: እስቸኳይ ስብሰባና ውይይት ያስፈልጋል:: ይህን ተነጋግረው  ሲጨርሱ እሱም አሻራና የእጅ ፅሁፍ ናሙናውን ሊሰጥ ሄደ:: ሲመለስ ትሩፋት አልጋ ላይ ጋደም ብላ አገኛት::





«ትሩፌ አሁንስ ረፍት ያስፈልግሻል:: እዚሁ አካባቢ ያሉትን ሥራዎች ብቻ እንድታጠናክሪ ለበላይ አካል ማመልከት ይኖርብሻል። ከአንግዲህ ወድያ መሯሯጡና መጓጓዙ ቢበቃሽ ይሻላል:: ለአንቺም ለልጃችንም ጤንነት ሲባል» አለ ይነበብ በሰሰት ሆድ ሆዷን እያየ::

«ምን ማለትህ ነው ይነበብ! በዚህ በትግል ወቅት ራሳችንን ከምንም በላይ የወደድን አያሰመሰልብንም? ከድርጅቱ ደንብና መመሪያ ውጭ ትዳር መመሰረታችን ሳያንስ ሥራ እንዲሻሻልልኝ ልጠይቅ ደግሞ? በድርጅታችን ላይ የፈጸምነው በደል እኮ ባያሰገድለንም ቢያንስ ከአባልነት ሊያሰርዘን ይችል ነበር::»

«አውቃለሁ ትሩፌ ግን እኮ  ሁለት ነፍስ በአንድ ላይ--- ትንሽ ይከብዳል» አለ ይነበብ የሚለው ቢያጣ::

«ቢሆንስ እርግዣለሁና ከትግል ሜዳ ልሸሽ ብዬ ነው የምጠይቀው?  ሁላችንም የተመደብንበትና የምንሰራው አጣዳፊ የሥራ ድርሻ አለን» አለች ትሩፋት:: ምንም ሊል አልቻለም። እንደ ሸክላ የምትሰበር ይመስል እየተጠነቀቀ ወደ ራሱ ቀረብ አድርጎ አቀፋት። ጸጉሯን እየደባበሰ ግንባሯን ሳመ:: እሷም ታውቅበታለች አንገቱ ሰር ሽጉጥ አለች::

ከወር በፊት ጎንደር ደርሳ ስትመለስ ፍተሻ ከመቼውም ጊዜ በላይ አይሎ ነበር። በፊት እንኳን ነፍሰጡር የሆነች ይቅርና ሴቶች በሙሉ ከአውቶብሱ ውረዱ አይባሉም ነበር። ወንበራቸው ላይ እንደ ተቀመጡ ፍተሻው ይካሄዳል:: ያንጊዜ ግን ሁሉም እንዲወርዱ ትእዛዝ ሰጠ ወታደሩ:: ተናዶ ነበር:: አውቶብሱ ውስጥ ከአንድ ሰው በቀር የቀረ አልነበረም:: እሱም መለዮ የለበሰ ወታደር በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም:: ከሹፌሩ ጀርባ ቀጥሎ ካለው ወንበር  ላይ በኩራት ተኮፍሷል:: ትሩፋት በዘንቢል የያዘችውን ጽሑፍ በላዩ ላይ ጥጥ ጨምራ አሮጌ ጥቁር ሻሽ ጣል አድርጋበታለች። ሊሸኛት የመጣው ልጅ ከወታደሩ እግር ስር አስቀምጦላት በዐይኑ ምልክት ሰጥቷት ውልቅ አለ። ዘንቢሏን ለማየት እንዲያመቻት ወታደሩ ከተቀመጠበት ትይዩ ሦስተኛ ወንበር ላይ ሄዳ ተቀመጠች:: በተቻላት ሁሉ ነፍስጡር መሆኗ እንዲታወቅ እየጣረች:: አውቶብሱ ጎንደር ከተማን የለቀቀው ቼቼላ ላይ  ኃይለኛ ፍተሻ ተደርጎለት ነበር:: አዘዞ ላይ የነበረው ፍተሻ ደግሞ ይብሳል:: ሰጋቷ እየጨመረ መጣ:: ነፍሰጡር መሆኗ ከአውቶብሱ ወርዳ ከመፈተሽ አላዳናትም:: ለማንኛውም ዘንቢሏ  ወታደሩ ከተቀመጠበት ወንበር ስር መኖሩን እሰባ ደሰ አላት:: የወንዶች ፈተሻ ከማለቁ በፊት አንድ ልጅ እግር ሰው ከመኪናው ኋላ ውልብ ሲል አየችው። ተመልሶ ወደ ከተማው ገሰገሰ:: ባታውቀውም እነዚህ እንደ ግስላ የተቆጡ ወታደሮች እንዳያዩትና እንዳይከታተሉት ተመኘችለት:: ፍተሻው ሲጠናቀቅ ተሳፋሪ ሁሉ የይለፍ ደብዳቤውንና መታወቂያውን  እያሳየ  ገባ::

«ኧረ አንድ ሰው አልገባም» አለ ከተሳፋሪዎች አንዱ ጮክ ብሎ። እዳፉ ጋቢውን ትከሻው ላይ ነጠል ደረብ አድርጎ እያስተካከለ:: አውቶብሱ ጥሎት እንዳይሄድ አስቦ ነው::

«የት ነበር ቦታው? ምን ይመስላል? ወጣት ነው ሽማግሌ? ምን አይነት ልብስ ነው የለበሰው?» ባላገሩ ሰውዬ ሳይቸግረው ተናግሮ ወታደሮቹ እየተቀባበሉ በጥያቄ አጣደፉት::

«ኧረገኝ! ኧረ ካጠገቤ ሰው መጉደሉን ነው እንጂ የዚህን ያህልስ አስተውየም አላየሁት ኧረ!» አለ ባላገሩ ተደናግጦ።

«አንድ ወንበር ላይ ተቀምጣችሁ እንዴት ነው የማታየው?» አለ አንደኛው ወታደር ሰውየው ላይ አፍጦ::

«ኧረ እናንተ ሆዬ! ገና ጎንደርን መልቀቃችን መስሎኝ! የቱን ያህል ተጉዘን ነው የሰው ቁጥር መልክ እስተመለየት የምደርሰው» አለ ባላገሩ እየተጨነቀ::

«አንተው ራስህ ከመነዳትህ በፊት ያየኸውን በትክክል ተናገር!» አለ ሌላው ወታደር:: ጠቋሚ ጣቱን እያወዛወዘ እየዛተበት::

«አንዴው ስገምት ልጅ እግር ቢጤ ይመስለኛል» አለ ባላገሩ:: ዐይኑን ጠበብ አድርጎ ለማሰብ እየሞከረና ፈራ ተባ እየለ::

«ምን ዓይነት ልብስ ነው የለበሰው? መልኩስ ምን ይመስላል? ቀይ ነው ጥቁር? ቁመቱስ ረጅም ነው አጭር?» አሁንም ሁለት ሁነው በጥያቄ አዋከቡት ::

«ኧረ እግዚሀር ምስከሬ ነው! አጠገቤ ሰው መኖሩን ነው እንጂ እስተዚህም አላስተዋልኩትም» አለ ባላገሩ:: ተሳፋሪው ሁሉ ቢያዝንለትም ማንም ደፍሮ ሊረዳው የሞከረ የለም:: ሁሉም ዝም!--- ጭጭ! ብሎ የሚሆነውን ይመለከታል::

«ይህን እንቅልፋም ገልቱ ባላገር አባክህ ተወው! ይልቅ ብዙ እርቆ ሳይሸሽ ክትትል ብናደርግ ይሻላል:: ቶሎ እንውጣ ጊዜ አንግደል!» አለ የመጀመሪያው ወታደር:: እየተጣደፉ ከአውቶብሱ ወርደው በችኮላ አካባቢውን መቃኘት ጀመሩ::

«እስከ አሁን እርቆ ሄዶ ይሆናል» አለች ትሩፋት በውስጧ:: በአውቶብሱ ኋላ ውልብ ብሎ የሄደዉን ሰው አስባ። እነዚህ ደም የጠማቸው ወታደሮች እንዳያገኙት አጥብቃ ተመኘችለት:: አውቶብሱ ከግማሽ ሰዓት ቆይታ በኋላ እንዲንቀሳቀስ ተፈቀደለት፡፡ ዘንቢሏ በግርግር የአሁኑን ፍተሻ አልፎላታል:: ወታደሩ ከተቀመጠበት ወንበር ሥር በመሆኑ ብዙ ጥርጣሬ ሳይገጥመው ይችል ይሆናል:: ድንገት ቢያዝና የማን እንደ ሆነ ቢጠየቅ ግን የሷ እንደ ሆነ የሚመስክር እንድም ሰው አይገኝም:: ወታደሩ እግር ስር በፍጥነት አስቀምጦላት የሄደውን ልጅ ብልጠት አደነቀች:: እንደ ፈራችው ሳይሆን በዐይነ ቁራኛ





እየተቆጣጠረችው በሰላም ሀሙሲት ደረሰላት። ነገ በተፈለገው ቦታ ሁሉ ለማሰራጨት በደስታ ተውጣ አንድ ትንሽ ልጅ አሸከማ ገሰገሰች:: ደስታዋ ወሰን አልነበረውም::